ጆን ባፕቲስት ለቆንሲሉ ምስጋናውንና አክብሮቱን ለመግለፅ ቀረበ። ቆንሲሉም፣ ለአንደበተ ርቱዕነቱና ስለደስተኛ ስሜቱ እንኳን ደስ ያለህ አለው። በጠረጴዛው ዙሪያ የሚገኙ ተጋባዦችም ተጨማሪ ምስጋናቸውን አከሉ። ከዚህ በማስከተል ይህ አቢሲኒያዊ መልዕክተኛ፣ ቀደም ብሎ የመውጣት ልማድ ስላለው፣ አጅቦት ወደ ቤቱ ሊሄድ ይችል እንደሆነ መድሃኒት ቀማሚው ጠየቀ። ቆንሲሉ፣ ከዚህ ባለማቋረጥ ከሚያሣፍር ሰው ለመላቀቅ ሲል ሃሣቡን ወዲያውኑ ተቀበለ። ሠረገላውን እንዲጠቀሙበት ቢፈቅድም፣ አላስገደዳቸውም። በእንግዳ መቀበያው ክፍል፣ ሰው በለቀቀው አንድ ጥግ በኩል፣ አርመናዊው ባለመደገፊያ ወንበር ላይ እጥፍጥፍ ብሏል። የለበሰው ጃኬት በጥብስ ቅባት ተበክሏል። ምግብ በጣቶቹ ስለሚያነሣ እጆቹ በቅባት ወርዝተዋል። በዚህ ሁሉ የተነሣ አዲሱና ሃር መሳይ ሰማያዊ የመደገፊያ ትራስ ሊነገር ከሚችለው በላይ ተበላሽቷል። ፖንሴ፣ በእግር መጓዙ የተሻለ እንደሚሆን ገልፆ፣ አምባሣደሩን ጉትቶ ሲያነሣው፣ ሰውዬው በሁሉም አቅጣጫ እየተጥመለመለበት ያልተያያዘ ማጉመትመት አሰማ። በማዕድ ቤት ውስጥ እራታቸውን የበሉትን ሦስቱን አቢሲኒያውያን በመግቢያው በር ደረጃ ላይ አገኟቸው።

«ለተከበሩ አምባሣደር ባትሪ አምጡላቸው» ሲል፣ ሙሴ ዱ ማይሌ አዘዘ።

«በዚህ ትዕይንት ውስጥ ከሚያስፈልገው በላይ መብራት አለማብራት የተሻለ ይሆናል» ሲል፣ ጆን ባፕቲስት ሃሣብ አቀረበ።

ቆንሲሉም፣ የዚህን አስተያየት ትክክለኛነት በመገንዘብ በሸሽት ላይ እንደሚገኝ አንድ አነስተኛ ጉሣ በጭለማ እንዲሄዱ ፈቀደላቸው።

መንገድ ውስጥ ከገቡ በኋላ ለአንድ ሁለት መቶ ሜትሮች ያህል አብረው ተጓዙ። ከዚያ በኋላ ፖንሴ፣ የሙራድን ክንድ፣ ጠንካራ ለሆነውና አረቢኛ ለሚናገረው አቢሲኒያዊ ካስያዘው በኋላ ወደ ቬነስያውያን ቤት ይዞት እንዲሄድ አዘዘው። ጆን ባፕቲስት በበኩሉ ወደ ግራ ታጥፎ በሰፊው የቆንስላው መሬት ዙሪያ ተጉዞ፣ በሁለቱም ጎናቸው መስኮት በሌላቸው ቤቶች መሃል በሚገኝ አነስተኛ መንገድ ውስጥ ገባ። ከነዚህ ቤቶች አንዱ የሊጋሲዮኑን የማዕድ ቤት ግቢ የሚለይና ለቁሣቁስ አቅራቢዎች መግቢያ በር ያለው ነው። በዚያ ቦታ ፍራንቾይዝ ስትጠብቀው አገኛት።



# 8

ፖንሴ፣ እምክ እምክ በሚሸትት ቀጭን የጓሮ ደረጃ፣ ፍራንቾይዝን ተከትሏት ወጣ። ከዚያ በኋላ ብቻውን ወደ አንድ ጨለማ የመልበሻ ክፍል አመራ። ቀጥሎም መስኮቱ የሲሲቱን ከዋክብት በብዛት እንዲያሣይ ተብሎ በስፋት ወደተከፈተ የመኝታ ክፍል ገባ። ቀለል ያለ የሰሜን ነፋስ ከከተማው ዝቅ ብሎ ከሚገኘው የደለል ሥፍራ የአፈር ሽታ ተሸክሞ ያመጣል። ከምድር ቤቱ በኩል፣ ግራ የተጋቡት የእራት ግብዣው እንግዶች ውካታና ጫጫታ ይሰማል። ብዙዎቹ እስከዚህ ሰዓት ድረስ በሣቅ እያውካኩ ቆይተዋል። ጭል፣ ጭል የሚለው ሻማ፣ ከመቅረዙ ላይ ሆኖ፣ ቢጫ ብርሃኑን ፍቅረኛዋን በምትጠብቀው አሲስ ላይ ይረጫል። ጆን ባፕቲስት፣ በዝግታ ወደርስዋ ተራምዶ፣ በእቅፎቹ ውስጥ አስገባት። ልብሶችዋን አልቀየረቻቸውም ነበርና፣ ጆን ባፕቲስት ያንን እንግዳ ፀጉር፣ ጌጣጌጥና በተለይም ያንን በቅርቡ በአዕምሮው ውስጥ አትሞ ያቆየውን ውበት፣ ቀለሙንና የውበቱን ውህደት አጣምሮ የያዘውን አንፀባራቂ መልክ፣ በታላቁ የእንግዳ መቀበያ አዳራሽ ግዙፍ የመብራት ብርሃን ስር ተመለከተ። በአጭሩ፣ ሁለቱ ፍቅረኛሞች አንዳቸው ለሌላኛው በሕይወት ቆይተው ፣ይንትለት ለነበረው ጊዜ መድረሳቸውን በደስታ ለመገንዘብ ችለው ነበር። እዚህ ደረጃ ለመድረስ ብዙ መሰናክሎች ተደንቅረውባቸው ስለነበረ፣ በአሁኑ ጊዜ ያገኙትን ደስታ ለአመል ያህል እንኳ የሚያደናቅፍባቸው ነገር ቢኖር የማይቀበሉት ነው። ሁለቱም በስሜት ተውጠው በረኸርም መሣሣም ውስጥ ቀለጡ። በጨለማ ውስጥ በቆየው የኦፔራ አዳራሽ፣ ትዕይንቱ ሲያልቅ ሲል፣ ውብ ጥንዶች በመድረክ ላይ ዳግመኛ ሲገናኙ የሚሰማውን የድጋፍ እልልታ ዓይነት ድምፅ ከምድር ቤቱ በኩል ይሰማል።

ከአጠገባቸው አንድ አልጋ አለ። ብቸኝነታቸው፣ ከማንኛውም ዓይነት ሁከት ነፃ ሆነው፣ ምስጢራቸውም ፍፁም የግላቸውና የተሟላ ነበር። ይሁን እንጂ በዚህ የፍቅር ደረጃ ላይ እርስ በርሣቸው የመፈላለጋቸው ነገር፣ እጅ እንዲሰጡና እንዲሣሣቱ አድርጓቸዋል ብሎ ማመን እነርሱን አለመረዳት ነው። እስከዚህ ጊዜ ድረስ፣ አንድ ቀን ርስበርስ የመፋቀራቸውን የነፃነት ተስፋ በማጣፈጥ ያሣድጉታል። በዚህ የደስታ ተስፋቸው ላይ የተጋረጡትን ገደቦች ሁሉ ለማስወገድ ጊዜውን ይጠብቃሉ።

«ፍቅሬ፣ ፍቅረኛዬ» ስትል፣ የጆን ባፕቲስትን ፊት በመሣም እየሸፈነችው፣ አሊስ አጉተመተመች:: «ምን ያህል ደስተኛ እንደሆንኩ ብታውቅ፣ አፈቅርሃለሁ:: በዚህ ሁኔታም ሁል ጊዜ መሆንን እፈልጋለሁ»

የጊዜ መጉተት አስቸጋሪነት ሃሣብ በውስጥዋ በመኖሩ፣ ትጀምረውና መልሣም ከጆን ባፕቲስት ራስዋን በመጠኑ ትገታዋለች:: በእንባ በሚንፀባረቁ ውብ ዐይኖችዋ ተመለከተችውና ዝቅ ባለ ድምፅ አናገረችው::

«ወደ ሼርሣይለስ መቼ እደምትሄድ ከዚያም ደግሞ መቼ ተመልሰህ መጥተህ፣ ይዘኸኝ እደምትሄድ ንገረኝ»

«እሀ» አለ ጆን ባፕቲስት፣ ፊቱን በመጠኑ ኮር በማድረግ

«ምንድን ነው?»

« ሁሉም ነገር ተወሳስቧል:: ወደ ሼርሣይለስ የሚደረገውን ጉዞ ቱርኮች ይቃወሙታል በሚል፣ አባትሽ ወሬው እንዲነሣ አይፈልጉም:: በርግጥ፣ እኛም ነገሮች በትክክል እንዲሣኩ ያደረግነው ጥረት የለም:: ሙራድንም፣ ምን ዓይነት እንደሆነ አይተሸዋል»

« ይህ ማለት ታዲያ . . . ያ ሁሉ ተስፋችን ለዚሁ ፍሬ ቢስነት ነው?»

« አይደለም!» አለ ጆን ባፕቲስት እጆችዋን ጭምቅ እያደረጋቸው፣ «እኔ ተስፋ ካደረግሁበት ይልቅ አስቸጋሪና ረዘም ያለ ጊዜ ይወስዳል ማለቱ ነው»

ጆን ባፕቲስት፣ ዓላማቸው ሁሉ አለመሣካቱን በቀላሉ ለመቀበል አልፈለገም:: ተስፋ የሚያደርግበትን አቅጣጫ ሊለይ ባይችልም፣ በዚያች ሰዓት በአሊስ ፊት ቆሞ ተስፋ ቆርጦ መተው ማለት፣ ከመሸነፍ ይልቅ የባሰ ጥላቻና ተቀባይነትን ማጣት እንደሚሆን ተሰማው::

እነርሱ ካሉበት ቦታ በቀጥታ ከታች ካለው ምድር ቤት መውጫ መድረክ ላይ፣ ጥንዶች በብዙ ቁጥር እየሆኑ በመውጣት ላይ መሆናቸው፣ ደህና ሁኑ እያሉ ከፍ ባለ ድምፅ መሰናበታቸውና የማያቋርጥ የምስጋና ቃላቶቻቸው ድምፅ ይሰማል::

«ስማኝ» አለች አሊስ:: «ብዙ ጊዜ የለንም:: የመጨረሻው ሰረገላ ተጓዦን ሲያሣፍር አንተም መሄድ ይኖርብሃል»



ይህን ተናግራ እንደገና ሳመችውና ቀጠለች

«አንዳች አጣዳፊ ነገር በዚህ ጉዳይ ላይ እንደገባ ደግሞ እንድታውቅ»

«ምን ማለትሽ ነው?»

«አባቴ . . . ኦ! ይቅር፣ እንድታውቅ አልፈልግም:: ነገሮችን ማወሳሰብ ምንም ፋይዳ የለውም»

«ግዴለም፣ ንገሪኝ»

«ባለፉት ሦስት ቀናት አባቴ ባለማቋረጥ ከፈረንሣይ አንድ ሰው ተልኮለት እንደሚመጣ እየተናገረ ነበር:: ሰውዬው ዲፕሎማት ሲሆን ሮሴታ ወይም ዳሚየታ ውስጥ እንደሆነ ተረዳኝ እንጂ፣ የቆንሲል ሥልጣን የሚጠበው ነው»

«እናስ?»

«እናማ፣ አባቴ ስለዚህ ሰው ብዙ ጊዜ ይናገራል:: ስለ ትውልዱ ታላቅነት፣ ስለ አስተዳደጉ፣ ስለ ወደፊት ዕድሉ፣ ወደ እኔ በአትኩረት እየተመለከተ ያወራል:: በርግጥ እስከአሁን በግልፅ የተናገረው ነገር ባይኖርም፣ እናቴ እንደነገረችኝ ከሆነ ግን፣ አባቴ በሆነ ጊዜ ሊድረኝ እያሴረ ነው:: አባቴ፣ ዘመዳችን የሆነውን ሚኒስትር፣ እርሱ የሚፈልገውን ዓይነት የሆነ ጨዋ ሰው እንዲልክለትም ጠይቆታል::»

« ታዲያ . . . አንቺ ይህን ሁሉ እንዴት ታስቢዋለሽ?» አለ ፖንሴ::

«እኔ የማስበው፣ ፍቅረኛዬ፣እኔማ አንተንና አንተን ብቻ ነው የምፈልግህ:: ስለዚህ ለሚባለው እንግዳ ሰው ከአሁኑ ጥላቻ እያደረብኝ ነው»

«ለመሆኑ እዚህ መቼ ይደርሣል ተብሎ ነው የሚጠበቀው?»

«በአሁኑ ጊዜ በጉዞ ላይ እንደሆነ ነው የሚገባኝ»

ጆን ባፕቲስት ፊቱን ቋጠረ::

«ስሚኝ» አለ ስውነቱን ሰብሰብ እያደረገ

«ሁሉንም እስክናስተካክል ድረስ ጥቂት ጊዜ ይወስድብን ይሆናል። ይህ የምትይውም ሰው እኔ፣ አባትሽን ለማግኘት የምችልበትን ነገር በእጄ ከማድረጌ በፊት ሊደርስ ይችላል። እስከዚያው ድረስ ግን ለምንም ነገር ስምምነት አታድርጊ። ለምንም ነገር ቃል አትግቢ። አሻፈረኝ በይ። አንድ ሺህ አንድ ሰበቦችን አቅርቢ፣ የታመምሽ አስመስይ፣ ከፈለግሽም በፍራንቾይዝ በኩል እንዲያስልሽ ሊያደርግ፣ ወይም እንዲያስመልስሽ ወይም መልክሽ እንዲገረጣና እንዲያውም በርግጥ ካስፈለገ እንድትታመሚ ሊያደርግሽ የሚችል ፈሳሽ መድሃኒት ልልክልሽ እችላለሁ። ምንም አድርጊ ምንም፣ ለምንም ነገር ቃል አትግቢ»

«እስከዛሬ ድረስ ከልቤ ውስጥ መንጭቶ የገባሁት ቃል ቢኖር ሁልጊዜም ያንተ ብቻ መሆኔን ነው። ይህን ደግሞ አታስብ። አንተ የጠየቅኸኝን ሁሉንም ነገር እፈፅማለሁ። ይሁንና፣ አባቴንም በሚገባ አውቀዋለሁ። የምፈልገውን ነገር ሊከለክለኝ ይሞክር ይሆናል እንጂ ትዕዛዙን እንድፈፅም ግን ከቶም ሊያስገድደኝ አይችልም። ከአባቴ ጋር በጭራሽ መስማማት የማንችል ከሆነ፣ ማናችንም አሸናፊ የማንሆንበት ሁኔታ ይፈጠራል። እንዲህ ከሆነ ደግሞ ተቆራርጠን እንቀራለን»

የመጨረሻው ሠረገላ፣ ተሣፋሪዎችን ሊጭን ሲቀርብ እንደገና ተሣሣሙ። ከምድር ቤቱ አሁንም ጥቂት ድምፆች ይሰማሉ። የሚለዋወጧቸው መልዕክቶች ሁሉ በፍራንቾይዝ በኩል ይተላለፍላቸዋል። ፍራንቾይዝ እንድታስተላልፍላቸው የማያደርጉት ብቸኛው መልዕክታቸው፣ የስሜት ህዋሣቶቻቸውን እርካታ፣ በእጆቻቸውና በከንፈሮቻቸው ላይ ያሉትን ምልልሶች፣ የሁለቱን አካላት የመፈላለግ ጨዋታና አንዳቸው ለሌላቸው በከፋይና በሃር ልብሶቻቸው ውስጥ በሹክሹክታ የሚያስተላልፏቸውን መልሶች ይሆናል።

ከመልበሻው ክፍል የጨለማ ቦታ ምናልባት አንድ ሰው በማንኛውም ጊዜ ሊመጣ ይችላል የሚል የፍራንቾይዝ ዝቅ ያለ ድምፅ ተናገረ። አይኖቻቸውን እንባ እንደሞሏቸው ተለያዩ። በደረጃው ላይ የሚሰማው የእግር ዱካ ድምፅ እስኪጠፋ ድረስ፣ አሊስ ጠበቀች። ከዚያም፣ የመኝታ ክፍሏን በር ቀርቅራ፣ ሙሉ ልብሰዋን እንደለበሰች አልጋዋ ላይ በዝግታ ተጋደመች።



ፖንሴ መኖሪያ ቤቱ ሲደርስ፣ ሜትር ዠረሚ አንድ ፋኖስ ከእግሩ ስር አብርቶ፣ ደረጃው ላይ ተቀምጦ በአንድ ትንሽ ብርጭቆ የመንደሪን ጭማቂ ይጠጣ ነበር። ይህ ጭማቂ፣ የመድሃኒት መቀመሚያው በአገልግሎት ላይ ባልነበረበት ወቅት ከረዥም ጊዜ በፊት የተነጠረ ነበር።

«እሺ አቶ አፍቃሪ ፣ መጡ?» አለ ዠረሚ

ጆን ባፕቲስት አንዳችም ቃል ሣይወጣው ከጓደኛው ባሻገር ተቀመጠ።

«ኧረ... ኧረ... እንዲያው አንዳች ደስ የማይል ዜና ያለም ይመስላል። እስቲ ጨጓራህ ሞቅ እንዲለው ይህን ጠጣ»

ሜትር ዠረሚ፣ለጓደኛው አንዲት ትንሽ ብርጭቆ አቀበለው። ፖንሴ ተቀብሎ ሳይቀምሰው በደረጃው መደገፊያ ላይ አስቀመጠው።

«ጠንከር ማለት አልቻልክም ጓደኛዬ» አለ ዠረሚ ከተቀመጠበት እየተነሣ።

ቢመሽም እንኳ በጥሩ ስሜት ላይ ነበር። መልካም የምሽት ሰዓት ያሣለፈና ራሱን ለማነቃቃት የጓደኛውን መምጣት የሚጠባበቅም ይመስል ነበር። የበረንዳውን ደረጃ በረዥም ርምጃ አቋረጠ።

«ችግሩ ምንድን ነው? ከእንተነትህ የምትቀበልህ አንዳችም ክፍል የላትም?»

«ትቀበላለች» አለ ፖንሴ፣ ሃሣቡ በሌላ ጉዳይ ላይ ሆኖ እንደመጃጃል እያለ።

ሜትር ዠረሚ፣ ያስቀመጣትን ትንሽ አጥንት አንስቶ ድምፅ እስኪታሰማ ድረስ ይቆረጣጥማት ጀመር። ከዚያም፣ ይህ በጣም አስፈላጊው ነጥብ እንደሆነ፣ እርሱም ሲበዛ እድለኛ መሆኑን፣ ጋሬጣና እንቅፋቶችም እልም ብለው እንደሚጠፉና ስሜቱ ሁሉ ውለታ እንዲመልስ እንደሚቀሰቅሰው ነገረው፡

«ተነስና ሽምላህን ይዘህ ተፋለም! ልታደርገው የሚገባህም ይኸው ነው፡፡ እስቲ ያለህበትን ሁኔታ ተመልከት»

«ወደ ቬርሣይለስ እንሄድም» አለ ጆን ባፕቲስት፣ ትክዝ ብሎ «ንጉሡ የጀብዱ ማዕረግ አይሰጡኝም፡፡ በዚህም ሣቢያ እርሷን አላገባትም»

«እናም ምሽቱ ዘለዓለማዊ ይሆናል፣ ውሃውም ዳግም ሽቅብ በመፍሰስ ሳይረጭና ሳይሞላ ይቀራል፣ በመጨረሻ ላይ ጅቦቹ ሁላችንንም በመስገብገብ ይበሉናል፡፡ በል ተመለስ፣ ተመለስ! አንተ አሮጌ ጨለምተኛ! እስቲ ወኔህን አሣይ»

ሜትር ዠረሚ፣ ደረጃዎቹን በከባድ ርምጃዎች አቋረጣቸውና ወደ ፖንሴ ክፍል ውስጥ ገባ፡፡ ከዚያም ሁለት ጉራዴዎችንና የደረት መከላከያዎችን ከተሰቀሉበት ሜንጠ ላይ አንስቶ ወደ ጓደኛው ተመለሰ፡፡

«ይኸውልህ፣እንደጥንቱ ቀልጠፍ በል፡፡ እስቲ በአምስት ደቂቃ ውስጥ ያ የጥንቱ አንተ መሆንህን ወይም አለመሆንህን አረጋግጥ»

ጆን ባፕቲስት ከወንበሩ ላይ መነሣት ፍላጐት አልነበረውም፡፡ በዙሪያው፣ ፀጥ ባለው አየር ውስጥ፣ አሊስ በሰውነቱና በልብሶቹ ላይ የተወቻቸው የመጨረሻዎቹ ጠረኖችዋ እንደተቀቡ ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ፣ በልቡ ጥልቅ ሥፍራ ውስጥ፣ ጓደኛውን በዚያን ዕለት ምሽት የተወው መሰለውና ትንሽም ቢሆን ክፍተቱን ሊያጠብበው ፈለገ፡፡ ከወንበሩ ላይ ተነስቶ ቆመ፡፡ የቆዳውን ሰገባ ሳበና፣ የተከላካይ ቦታውን ያዘ፡፡ ሜትር ዠረሚ በጥቂት ሴኮንዶች ውስጥ በሽምላው ጫፍ ፖንሴን ነካ አደረገው፡፡ በድጋሜ በሽምላ ተዋጊነት ቦታ ራሣቸውን አዘጋጁ፡፡ ይህ ሁሉ ሲሆን ፖንሴ እንደቀድሞው አይደለም፡፡ ለጥቂት ጊዜ ያህል ደካማ መከላከል አደረገ፡፡ ሜትር ዠረሚ ለሁለተኛ ጊዜ ዘሎ አፈፍ በማድረግ ነካው፡፡

«በል ነቃ በል፣ ያዝ! እንዲህ ወዙን ያጣውን ሰዛህን ለመመለስ፣ መከርከር አለብኝ እንዴ?»

ማንኛውም ሰው የሽንፈት ድምፅ ሲሰማው፣ የተዋጊነትና የጠረኛነት መንፈሱ ከተኛበት ጥልቅ አዘቅት ሆኖ ያስቆጣዋል፡፡ አዕምሮው በሌሎች አስጨናቂ ጉዳዮች ፍፁም ተወጥሮ ባለበት ጊዜም እንኳ ቢሆን፣ የመጀመሪያው የሽምላ ጫፍ ሰውነቱን ሲጭረው፣ ጡንቻዎቹ



ተቆጥተውና አይኖቹ ተጉረጥርጠው፣ የፀበኛነት ስሜት የማይቀሰቀስበት ሰው ተሰምቶ አይታወቅም፡፡ ለሶስተኛ ጊዜ በጉራዴው ሲገጥመው ፖንሴ ወደ ህሊናው ተመለሰ፡፡ ሜትር ዠረሚ በሚገባም ባይሆን፣ በድጋሚ ነካ አደረገው፡፡ ከዚህ በኋላ ግን ረዘም ያለ፣ የሚመጣጠን ግጥሚያ አደረጉ፡፡ በከንድ ርቀት፣በተሟላ ስልትና ብልሀት፣ በሚያስደንቅ ቅልጥፍና፣ የታፈነ ፖኸትና ጉዳት እስኪሰማ ተፋለሙ፡፡ በመጨረሻም፣ ጆን ባፕቲስት በሽምላው ጫፍ ዠረሚን ነካ አደረገውና እስፈሪ ፖኸት አሰማ፡፡

«ጀስዊቶቹ!»

ሜትር ዠረሚ፣ ትንፋሹ ጠፍቶ፣ ጉራዴውን እንደመጣል አድርጐ፣ ዙሪያውን ግራ በመጋባት ተመለከተ፡፡

«የምን ጄስዊቶች ናቸው? የታሉስ?»

ጆን ባፕቲስት ወደ ኋላው ፈቅ ብሎ ለመከላከያ በተሠራው የብረት አጥር ላይ ደገፍ አለ፡፡ ከሃሣቡ ጋር ወዲያና ወዲህ እያለ ጉራዴውን በያዘው እጁ በሃሣቡ የፈጠረውን የአዋጅ ፊደላት በአየር ውስጥ ከተበ፡፡

«ጄስ-ዊ-ቶቹ፡፡ እውነቴን ነው ጀስዊቶቹ፡፡ በዚህ ጉዳይ ሊረዱን የሚችሉት እነርሱ ብቻ ናቸው»

«እንዴት ያለ ሰይጣናዊ ነገር ነው የምትናገረው?»

«ወደ ቬርሣይለስ ስለሚደረገው ጉዞ ነው፡፡ ታዳምጠኛለህ? ሊረዱን የሚችሉት እነርሱ ብቻ ናቸው፡፡ ወይኔ! ምነው ፈጠን ብዬ አላሰብኩትም? አዎን፣ቆንሲሉን በጉዳዩ ላይ እንዲቀርብ ሊያደርጉትና እኛም ንጉሡ ዘንድ መድረስ የሚያስችለንን መንገድ ሊረዱን የሚችሉት፣ ከሁሉም በፊት የንጉሡን ትዕዛዝ እዚህ ድረስ ማስተላለፍ የቻሉት ብቻ ናቸው፡፡ ምንም እንኳ የማይታመኑ መሆናቸውን ብናውቅም ሃይላቸውን መዘንጋት የለብንም»

«ነገር ግን» አለ ሜትር ዠረሚ በትካዜ፡፡ «አቢሲኒያ ውስጥ ጀስዊቶች ዳግመኛ ተመልሰው አይመጡም በማለት የገባነውን የጨዋ ቃል ኪዳን ረስተሃል፡፡ ወደ ቬርሣይለስ መሄድ ከፈለግን፣ እነዚህ የጀስዊት መልካም አባቶች የሚመግቡትን፣ ከንጉሡ ሃሣብ ጋር

በቀጥታ ተፃራሪ የሆነ መግለጫ ማረጋገጥ ብቻ ነው። በጉዞአችን ላይ በመጨረሻ ከኛው ጋር እንዲሆኑ የምንፈልጋቸው ሰዎች ደግሞ እነርሱ ናቸው።»

«ትክክል ነህ። ነገር ግን የዚህ ግትር ሃሣብህ መቋጫው ወደ ቬርሣይለስ አንሄድም፣ በቤተመንግስቱም አደባባይ የሚሰማው የጀስዊቶች ትርጉም ብቻ ነው የሚል ነው»

«የዚያን ሃሣብ ትርጓሜ የኛ ስምምነት ሳይኖርበት ብቻቸውን ቢያቀርቡት የሚሻላቸው ነው»

«አይደለም!» አለ ፖንሴ። «ወደ ቬርሣይለስ ለመሄድ ከጄስዊቶች ጋር መቀናጀታችን ከነርሱ ሰበቦች ጋር መስማማታችንን ሳይሆን፣ በንጉሡ ፊት መቅረብ ስንችል በጨዋ ሁኔታ ተቃርኖአችንን ለማሳየት ነው። አሁን የምንፈልጋቸው ልንጠቀምባቸው ስንል ብቻ ነው»

«እስከአሁን ድረስ የነርሱን ሃሣብ መርምረህ ሳታይ፣ የነርሱኑ ስልት የተቀበልክ ነው የምትመስለው»

«ታዲያ የጠላትህን ዓይነት የጦር መሣሪያ ከሌለህ እንዴት ትዋጋለህ? ለምሣሌ፣ እኔ በጐራዴ ባጠቃህ አንተ በማንኪያ ትከላከላለህ ወይ?»

«የባላጋራህን ድክመቶች መከረጅ ሽንፈትህን መቀበልና የጠላትህን ድል አድራጊነት ማመን ነው»

«ይህ ካልሆነ የተሻለው ነገር ፍፁም ነፃ ሆኖ መሞት ነው»

«አዎን፣ ከክህደት ይልቅ ሞት ይሻላል። ነገር ግን፣ አለ ሜትር ዠረሚ በዚያ ግዙፍ ቁመናው ዓይኖቹን እያጉረጠረጠ «ሣይረክሱ መቆየትና ማሸነፍም ይቻላል።.

«የውይይታችንን ፍሬ ሃሣብ መሠረት እየለቀቅን ነው» አለ ጆን ባፕቲስት በብልጣብልጥ ሁኔታ። «የንጉሡን መልዕክት ቬርሣይለስ እንዴት ማድረስ እንችላለን? ጥያቄው ይህ ነው። እውነተኛውም ጥያቄ ይህ ብቻ ነው። እኔ ሳስረዳህ የፈለግሁትና እየነገርኩህ ያለውም ይህን ተልዕኮአችንን በተአምር ከፍፃሜ ሊያደርሱልን የሚችሉት ጀስዊቶች ብቻ ናቸው»



ሜትር ዠረሚ ወደ ኋላው ዞረና ሦስት ርምጃ ወደ ግድግዳው ተራመደ። ከዚያም እንደገና ከጓደኛው ፊት ለፊት ሆነ።

«ጆን ባፕቲስት፣ ሁሉንም ነገር እያወሣሰብክ ነው። ይህ ጉዞ ላንተ ግላዊ ምክንያት ሲባል ጉዳይህ ነው። ስለዚህም ግላዊና ፍፁም የራስ ወዳድነት ፍላጐትህን ለማርካት ስትል ቃል ኪዳንህን ለማፍረስ ዝግጁ ነህ።»

«እንዲህ አትበል!» አለ ፖንሴ የመደገፊያውን የብረት አጥር በጐራዴው እጀታ እየገጨ።

«እንግዲያው ተሳስቻለሁ እንዴ?» ሲል ሜትር ዠረሚ በጥላው ጠርዝ ላይ እንደቆመ ጠየቀ።

«ትክክል ነህ፣ ትክክልም አይደለህም። አዎን፣ወደ ቬርሣይለስ በመሄድ የራሴን ጉዳይ ላመለክት እፈልጋለሁ። ይሁን እንጂ የአቢሲኒያውን ንጉስ በምንም አይነት አልክድም። ለነዚህ ሁለት ተልዕኮዎች ግን እኩል የሆነ አቅሜንና ችሎታዬን በማዋል፣ ሁለቱንም በስኬት መፈፀም እፈልጋለሁ»

ሜትር ዠረሚ ራሱን በጥላው ውስጥ ለመሸፈን አንድ ርምጃ ወደ ኋላ ተራመደ። ይህ የመደበቅ ሁኔታ፣ ሃሣቡን ያለ ውዴታ የመቀበል ምልክት እንደሆነ ፖንሴ ያውቃል።

«እስቲ ለኔ ተወው» አለ ጆን ባፕቲስት በተረጋጋ ድምፅ። «አጥብቄ የምጠይቅህ፣ አንተ ከዚህ ሁሉ ነገር ነፃ ሆነህ በኔ ግን እምነት እንዲኖርህ ነው። ለጀስዊቶቹ፣ እኔ ብቻዬን ጉዳዩን እነግራቸዋለሁ። ወደዕቅዳችንም ውስጥ የሚመጡበትን ሁኔታና የሚከተለውን አደጋም ብቻዬን እቀበላለሁ። በመጨረሻም፣ በንጉሡ ፊት እኔው ራሴ ማስተባበሉ የሚያስከትለውን አደጋ እቀበላለሁ»

«በኔ ሃይማኖት፣ የምንስብከው በምሣሌ ብቻ ነው» አለ ሜትር ዠረሚ ከጨለማው ውስጥ እየወጣ። «በአቅም ወይም በማሣመን ሃሣብህን ላስለውጥህ አልሞክርም። በግሌ ግን ወደ ጀስዊቶች ዘንድ አልሄድም። ሊጦኙ ይችላሉ ብዬ ለመቀበልም ይከብደኛል። አንተን ግን ባቀድከው ዓላማ ላይ እንቅፋት አልሆንብህም። እንዲያውም እንደሚሣካልህ ተስፋ አደርጋለሁ።»

ጆን ባፕቲስት በጓደኛው አስተያየት ተደስቶና እንደማይቃረነው በማወቅ፣ ወደ ሜትር ዠረሚ ራመድ አለ። ጓደኛውም ወደርሱ ተራመደ። ሁለቱም ለወዳጃዊ አስመግባባታቸው ፅዋቸውን አነሱ። ቬጋው እነርሱን ቁልቁል ሲመለከታቸው፣ የካይሮ ውሾች በከፍተኛ ድምፅ ይጮሃሉ።

ጺ

በቆንስላው ግቢ እራቱን ከበላ በኋላ፣ ሙራድ ከፋኛ የራስ ምታት አምሞት ነበር። ይህም በመጠጡ ሳቢያ ቢሆንም፣ እርሱ ግን በምግቡ ላይ ያሳብብ ነበር። ከያንዳንዱ የመጠጥ ዓይነት በዛ ያለ ናሙና በመቅዳት፣ በጠረጴዛው ዙሪያ የተቀመጡት ሁሉ አሣፋሪ ነው እስኪሉት ድረስ የሻምፖኝ፣ የባርጋንዲና የመራራ ቅልቅል በአንድ ብርጭቆ ውስጥ በመሥራት ጠጥቷል።

ከሁሉም ነገር በላይ፣ በየማለዳው ፀጉሩን በሰባራ መስተዋት የሚላጨው ኢትዮጵያዊው ባሪያ፣ የሙራድን አናት በምላጭ ሲላጨው ገሽልጦታል። ሙራድ፣ ለብረት ምላጭ ጥላቻ አለው። የደረቀ የደም ጠብታ በጥምጣሙ ስር ይታያል። ከጧቱ ሶስት ሰዓት ሲሆን፣ ፖንሴ ወደርሱ መጥቶ፣ የጀስዊቶች ቃል አቀባይ እንዲመጡ እንደላከባቸውና ከጥቂት ጊዜ በኋላም እንደሚደርሱ ነገረው። የንጉሠ ነገስቱን ቃል ያልረሣው ሙራድ በመጀመሪያ ላይ ተበሣጨ። በኋላ ግን ፖንሴ እቅዱን ሲያብራራለት የመፅናናት ስሜት ተሰማውና ስለ ሆድ ህመሙ ይጠተውት ጀመር።

አባ ፕላንቴይን፣ ከተባለው ሰዓት ጥቂት ቀደም ብለው ደረሱ። ከሙራድና ከፖንሴ ፊት ደርሰው እንደቆሙ፣ አምባሣደሩ ባመለከታቸው መሠረት፣ ልክ አንድ ግዙፍ በሬ ፍፁም እንክትክት ብሎ እንደሚወድቅ ዓይነት በምንባፉ ላይ ሰመጡ። ሙራድ፣ በጨዋ የሲቪል ባህርይ ቡናና ኬክ ጋበዛቸው። ጀስዊቱም ተቀበሉ። ግብዣውንም በስልፍ የቆሙት ሦስቱ ኢትዮጵያውያን ባሮች ከጥቂት ጊዜ በኋላ አቀረቡ።

አባ ፕላንቴይን፣ እነዚህን ሦስት ኢትዮጵያውያን ባሮች እንደተመለከቷቸው ወዲያውኑ በጉልበታቸው ቆሙ።



«አምላኬ ሆይ! እንዴት ቆንጆዎች ናቸው!»

ሦስቱን ይመራ የነበረው የሁሉም ታላቅና እግረ ቀልማማው ሲሆን፣ እርሱን ተከትሎ በዕድሜው ሁለተኛ የሚሆነውና በሚያስጠላ መልክ ጠንጋራ የነበረው ነበር። ከሦስቱ ወጣት የሆነውና የራስ ፀጉሩ ሁሉ በጭርት ሙልጭ ብሎ ያለቀበት ልጅ በመጨረሻ ነበር።

«እንደዚያ ነው የሚያስቡት?» አለ ሙራድ በረድፍ ያሉትን አሣዛኞች እየተመለከተ።

«መንፈሣቸው ይታየኛል» አሉ ቄሱ፣ ዓይኖቻው ረጥበው። ማርያም ድንግላዊት እንዲባረክ ለመረጠችውና በዋሻ ውስጥ ለነበረ የበግ እረኛ በርህራሄ እንደተገለጠችለት ዓይነት፣ ትኩር ብለው ተመለከቷቸው።

«እንዲህ ከሆነም መልካም። ንጉሱም እንደዚህ ያለ ዕይታ ስለነበራቸው ዕድለኛ ናቸው። እነዚህ ሦስት አገልጋዮች፣ ለንጉስ ሉዊስ 14ኛ ከታሰቡት ገፀ በረከቶች መሃል ናቸው» አለ ፖንሴ

ሦስቱ ባሮች እያነካከሱ ወደ ማድ ቤት እስኪመለሱ ድረስ፣ አባ ፕላንቴይን አይኖቻቸውን ከነርሱ ላይ አልነቀሉም።

«ንጉሠ ነገስቱ፣ ለፈረንሣይ ንጉስ ከላኳቸው ገፀበረከቶች መሃል ናቸው ነው የምትለኝ? ለመሆኑ ሌሎችም አሉ?»

«እንዴ፣ አባቴ፣ በርግጥ አሉ እንጂ። ያውም ግዙፍ የሆኑ ናቸዋ» አለ ጆን ባፕቲስት

ቄሱ የተመለከቱትን እንደዚህ ያለውን ስጦታ ሊያስንቅ የሚችል ገፀበረከት ለማሰብ ቸገራቸው። ፖንሴ የማወቅ ጉጉቱን እያጠናከረ፣ ቀስ ብሎ ኪሱን ከፈተና ደብዳቤ መዘዘ።

«እንደ ዕድል ሆኖ ይህ መልዕክት ከፓሻው ፖሊሶች ዕይታ አመለጠ»

«መልዕክት? መልዕክት ከፓሻው ፖሊሶች ዕይታ አመለጠ»

«በራሣቸው ፀሐፊ፣ እራሣቸው በቃላቸው እየነገሩት የተከተበና የታተመ ነው»

በሁለቱ ሰዎች መካከል የሚደረገውን ውይይት ሙራድ ይከታተላል። ፖንሴ፣ ከንጉሡ የተላከውን ደብዳቤ ጉዳይ ሲናገር በመስማቱ፣ ሙራድ ጭንቅላቱን በድንገት ወደርሱ ሲያዞር የራስ ምታቱን አባባሰው። አባ ፕላንቴይንን ይቅርታ ጠይቆ በመከዳው ላይ ከመዘርጋቱ በፊት፣ የመድሃኒት ቀማሚውን ሴረኛ የአይን ጥቅሻ ለማየት ጊዜ ነበረው። ቄሱ ደብዳቤውን ከፖንሴ እጅ ለመቀበል እጃቸውን ዘርግተዋል።

«ወይኔ» አለ ፖንሴ ወረቀቱን ወደ ኪሱ መልሶ እየከተተው። «ንጉሡ ነገስቱ፣ ይህ መልዕክት ለንጉሥ ሉዊስ 14ኛ በግላቸው ካልሆነ በስተቀር ለማንም ሰው እንዳይሰጥ በጥብቅ አዝዘዋል። ሌላው ቢከፈትም የሹመት ደብዳቤ ነው። ይህኛው ግን በማንም ሊታይ የሚችል አይደለም። እኔም ቃሌን በመሃላ ሰጥቻለሁ።»

«እና . . . መልዕክቱ የሚለው ምንድ ነው?» በማለት የማወቅ ጉጉት እያሰቃያቸው ጀስዊቱ ጠየቁ።

«አባቴ፣ ደብዳቢውና በውስጡ ያለው ሃሳብ አንድ ነው። ሁሉም ለንጉሥ ሉዊስ 14ኛ ናቸው»

«አዎን፣ ልክ ነህ፣ ዝርዝሩን አንተወውና መንፈሱን ምንድን ነው ማለቴ ነው?»

«ሙሉ በሙሉ የሚስማማ ነገር ነው። ይህን ያህል ልነግርዎ እችላለሁ። ንጉሠ ነገስቱ፣ ለፈረንሣዩ ንጉሥ ያላቸውን አክብሮት በመግለፅ በማንኛውም የሃይማኖት ጉዳይ ላይ ፈቃደኛ መሆናቸውን ይገልፃሉ»

«ጥሩ፣ በጣም ጥሩ፣ እና ንጉሠ ነገስቱ የክርስቶስን ሁለት ባህርያት እስከመቀበል ድረስ ፈቃደኛ ይሆናሉ?» በማለት ጀስዊቱ ጠየቁ።

አንድ ሰው ስለአንድ ነገር ብዙ ሲያውቅና ስለጉዳዩ የሚያስጨንቀውም ምንም ምክንያት ባለመኖሩ ምንም መናገር እንደማይችል፣ ፖንሴ ዐይኖቹን በግርምት በለጠጣቸው። አባ ፕላንቴይን፣ የተረዱና የተደሰቱ መሆናቸውን የሚገልፅ አይታ አሣዩ።

«እሺ . . . ሌሎቹ ገፀ በረከቶችስ?» ሲሉ ጠየቁ

«እዚሁ አሉ። ወርቅ፣ ዝባድ፣ ቅመማ ቅመም፣ የሃር ሻሾችና ንጉሡ ባሉበት ቦታ ብቻ እንድንከፍታቸው የተፈቀዱልን ሻንጣዎች ናቸው።»



«እጅግ በጣም ጥሩ . . . እጅግ በጣም ጥሩ!። ተልዕኮህ በጣም ጥሩ ነበር»

«ምን ያደርጋል! አባ ብሬቬደንት ግን ይህን ውጤት ማየት አልቻሉም። በታላቅ አክብሮት የምናስታውሣቸው ሰው ናቸው። ተልዕኮአችንን እርሣቸው በመካከላችን ቢሆኑ ኖሮ ግን በተሣካ ሁኔታ አሟልተን ማከናወን እንደማንችል ግን ይመኑኝ»

«ነው እንዴ፣ ገባኝ! የንጉሡ የንስሃ አባት ማህበር፣ ያለ አባ ዴ ላ ቼይዝ ንቁ ተሣትፎ ሊሣካ አይችልም ነበር። የዚህን ታላቅ ሥራ ውጤት ምክንያቶች በርግጥ ለንጉሡ ማቅረብ ይኖርብሃል።.

«እኔም አስቤ ነበር። ነገር ግን እንደማይሣካ እኮ እርስዎም ያወቁታል» አለ ፖንሴ እያጉነበሰ

«አዎን፣ቱርኮችን አይደል»

«አባቴ፣ ቱርኮች ቀላል ኢላማዎ ናቸው»

«ምን ማለትህ ነው ታዲያ?»

ባሮቹ መጥተው፣ መለኪያዎቻቸውን እንዲሞሉላቸው ፖንሴ አጨበጨበላቸው። ቄሱ እንደና የአግራሞት ስሜታቸውን ከፍ እንዲል በማሰብ፣ ባሮቹ በፍጥነት ገብተው እንዲወጡ አደረገ። ባሮቹ እንደወጡ አባ ፕላንቴይን ጥያቄአቸውን ቀጠሉ።

«ስለ ቱርኮች የሆነ ነገር ስትናገር ነበር» አሉት አቋሙን ዳግም ለማረጋገጥ

«አይደለም፣ አባቴ። ስለነርሱ የምትናገሩት እናንተ ናችሁ። እኔ የምገልፀው ጥርጣሬዬን ነው»

«ምን፣ፓሻው ወደ ፈርንሣይ እንዳትገዝ ሊከለክልህ መቻሉን አታምንም?»

«መሃመት ቤይን አላውቀውም። ከርሱ በፊት ለነበረው ፓሻ ለብዙ ዓመት ሃኪሙ ነበርኩ። ምንም ያህል አክራሪ ቢሆኑም፣ በተለይ ይህኛው ፓሻ በግርጥም አክራሪ ነው። ይሁንና አቶማኖች ግን ከኛ ጋር ባላቸው ግንኙነት ላይ ከተወሰነ መጠን በላይ ሄደው አያውቁም»

«ምን ማለትህ ነው?»

«የምለውማ፣ ቱርኮች የቆንሲሉን የቅድሚያ ይሁንታ ሣያገኙ በማህበረሰቡ ውስጥ የሚገኝ ቤት እንዲበረበር ፈፅሞ አያዝዙም»

«ስታስበው . . »

«. . . የቱርኮች ፓሻና መሴ ዴ ማይሌ በዚህ ሥራ ላይ እንግዳና አዲስ የሆነ ህብረት በኛ ላይ ፈጥረዋል::»

ጀስዊቱ በመጀመሪያ ጆሮ ግንዳቸውን የተጮሉ መሰላቸው:: የባሰ የማታለያ ማጣጣፍ መግለጫ እሰቡ:: ዓይኖቻቸው ከሽፋሽፍቶቻቸውና ከቅንድቦቻቸው አጥንት ጀርባ በጥልቁ ዋሻዎቻቸው ውስጥ እንስቅቃሴ አልባ ሲሆኑ ከንፈሮቻቸውም ተሰበሰቡ::

«ሙሴ ፖንሴ፣ ስሞታህ እጅግ አሳሳቢ ነው:: የንጉሡን ፍላጐት ለማገድ አስቀድሞ የታቀደ እቅድ እንዳለ እንዳምንህ የፈለግህ ይመስለኛል»

«አባቴ፣ ንጉሡ አንድ ፍላጐት ብቻ እንዳላቸው ማሰብ የሚፈልጉ ይመስላል:: ባልሣሣት፣ ንጉሡ በአቅራቢያችሁ ባሉ ሰዎች የሚገለፁ ብዙ ፍላጐቶች አሏቸው:: አንዱ የንጉሡን ከአደጋ የመጠበቅ ሃላፊነት ያለባቸው አሉ:: ሌላው የንጉሡን ፖለቲካ የሚመሩት ናቸው»

አባ ፕላንቴይን በጥልቅ ተመስጦ ውስጥ ገቡ::

«በኛ በኩል፣ በአባ ቬርሣው በኩል የመጡትን ትዕዛዞች አብረን ተቀብለናቸዋል:: ንጉሡም ከኛ የጠበቁትን ሁሉ በትክክል አከናውነናል:: የፈጠርነውን ግንኙነት በወሳኝነት ለመጠበቅና ለንጉሡ ያለንን ተጠያቂነት ለማከናወን፣ የንጉሡም አምባሣደር፣ የንጉሡ መልዕክት ለሉዊስ 14ኛ መድረሱን እንዲያረጋግጥና መልስ ይዞ መመለስ እንደሚገባው እምናለሁ:: ነገር ግን ይህ ሃሣብ ፈረንሣይ የክርስትና ተልዕኮዋን ማሟላት ይገባታል ከሚሉት ይልቅ፣ ከቱርኮች ጋር ያለንን ሕብረት ጠብቀን ማቆየት ይገባናል በሚለው አቋም ላይ ይበልጥ አጥብቀው ከሚጠይቁ ጋር በርግጥ ይቃረናል::

ጀስዊቱ በመከራ ተነስተው ቆሙ::

«በፍጥነት የዚህን ጉዳይ ሥረ መሠረት እጀምራለሁ» አሉ::

ለብዙ ደቂቃዎች ሲያንከራፉ የነበረውን ሙራድን እንዳይቀሰቅሰው በመምከር፣ ፖንሴን ተሰናብተው፣ በፍጥነት ብድግ ብለው ተንቀሣቀሱ:: ሃጢአት ውስጥ ለመዘፈቅ እንደሚዘጋጅና፣ ቢዋጋውም እንኳ መልካም እንደሆነ እንደሚያምን የተደሰተ ሰው መልክ ነበራቸው:



# 9

ለሦስት ቀናት ያህል ፖንሴ ምንም ወሬ ሳይሰማ ቆየ:: በነዚህ ረዥምም ሦስት ቀናት ውስጥ ወደውጭም አልወጣም ነበር:: ምክንያቱም ለእራት ሲጋብዙት የሚሹ ሁሉ በያንዳንዱ ነጥብ ላይ ትኩረት ነበራቸው:: ወቅቱ ደግሞ ሞቃት ነበር:: ከአባይ በኩል የሚነፍሰው ነፋስ ደስ የማይልና ቀፋፊ ሞገድ ከደለሉ አካባቢ ተሸክሞ ይመጣል:: ፖንሴ፣ ለምን ጠፋህ እንዳይሉት ታምሜአለሁ ሲል አስታወቀ:: ብዙም ሳይቆይ በርግጥ ታመመ:: መላው ሰውነቱ በትኩሣት ተቃጠለ:: በአጠቃላይ ሰውነቱም እልፎ እልፎ ድንገተኛ የመሸማቀቅ ሕመም በጉልበቱና በክንዱ ላይ ይሰማው ነበር:: ሰውነቱ ልፍስፍስ ስለሚልበት ቀኑን ሙሉ በተንጠልጣይ አልጋው ላይ ያልተያያዙ ሕልሞች እየታዩት፣ሲነቃ እየጠፋበትና የሃዘን ስሜት እየሳደሩበት ተጋድሞ እንዲውል አደረገው:: በየዕለቱ ልታየው የምትመጣው ፍራንቾይዝ የፍቅር ሕመም እንደያዘው እየሣቀች ትነግረዋለች:: ይህን ንግግር ፖንሴ እውነት ነው ብሎ ለመቀበል ዝግጁ የነበር ቢሆንም ሕመሙ ግን አልተሻለውም:: በሁለተኛው ቀን ከአሊስ የተላከለትን ደብዳቤ አመጣችለት:: ፖንሴም ደብዳቤውን ደግሞ ደጋግሞ ለአንድ መቶ ጊዜ አነበበው::

ደብዳቤው ምንም አልነበረውም:: ጥቂት የመውደድ ቃላት፣ ምናልባት በመሃል ሳንካ ቢገጥማቸው እንኳ ብዙም የማያደራድሩ ቢሆኑም ጽፋቸዋለች:: የጽሁፉን መስመሮች ተመለከታቸው:: ደብዘዝ ያሉ ቢሆኑም፣ ቅጥልጥሎቹ ግን አካላዊ እንቅስቃሴዋን፣ የፃፉትን እጆችዋንና ብዕሯን የመሩትን መላው አካሏን የሚያሣዩበት ይመስላሉ:: በሦስተኛው ዕለትም ሌላ ማስታወሻ መጣ:: ይህኛውም የመውደድ ቃላቶችን የያዘ ሲሆን፣ ወደ መጨረሻው ላይ ከርዕሱ ወጣ ያለ ነገር አክላበታለች:: ነገሩ ከፍቅራቸው ጉዳይ ወጣ ያለ በመሆኑ ጥረት እንዳደረገች ያረጋግጣል::

*አስተውለኸው እንደሆነ እርግጠኛ አይደለሁም:: ውድ ፍራንቾይዛችን ልታውቀው ባልቻለችው ፍቅር ውስጥ ጭልጥ ብላ አይገቡ ገብታለች:: ከንደኛህ ከዠረሚ ጋር በፍቅር ጠፋለች:: አመጣጡ ሁሉ አደጋ የበዛበት ስለሆነ ከርሷ ማመንታት ጋር*

*ሙሉ በሙሉ እስማማለሁ። በሚገባ ስለምታውቀው ምናልባት እንዲታቀብ ልትነግረው ትችላለህ።*

ወደ አቢሲኒያ መንዙ በማንም የማይታወቅበት ሜትር ዝረሚ፣ ወደ ማህበረሰቡ ሰፈርና ወደ ከተማው በነፃ መመላለስ አብዝቷል። ምንም እንኳ እርሱ ራሱ ማንንም ባያክምም ሕመምተኞችን መጥራት ጀምሯል። የፖንሴን ደንበኞችም በቀድሞው ትዕዛዝ መሠረት ትኩስ መድሃኒቶች እንዲሰጣቸው ስለሚለምኑ፣ ፕሮቴስታንቱ፣ ጉንፋን ለሚያስቃያቸውም በስኳር እንዲጣፍጡ የተደረጉ እንክብሎችንና የሆድ ድርቀት ለሚያስቸግራቸው የካሎሜል መድሃኒት በመስጠት ሥራ ተጠምዶ ነበር። ለጊዜውም ቢሆን በሰላም ለመሰንበት የሚፈልግ በሚመስለው በሙራድም ላይ ዓይኑን እንደጣለ ነው።

ሜትር ዝረሚ በሶስተኛው ቀን ሲመለስ አብሮት እንዲሆን ጆን ባፕቲስት ጠየቀው። ውስጣዊ የልብ ጉዳዮች በሚሆኑ ነገሮች ላይ ጓደኛው ቁጥብ መሆኑን ስለሚያውቅ፣ ሁኔታውን በማለሳለስ አነሣበት። ሕመሙ መጠነኛ ሃዘን ቢያሣድርበትም፣ ፖንሴ ያለፈውን የአብሮነት ቆይታቸውን በትዝታ ቅላፄ ጀመረው። አብረው ተጉዘዋል። ይህ ሁሉ ሆኖ ስለሜትር ዝረሚ ሕይወት ጆን ባፕቲስት የማያውቃቸው ብዙ ነገሮች አሉት።

«አንድ ጊዜ ትዳር ይዘህ እንደነበረ ነግረኸኝ ነበር?» በማለት በትውስታ በሚወያዩበት ዝርዝር ጉዳይ ላይ እግረ መንገዱን ጠየቀው።

«አዎን» አለ የፖሊስ መኮንን የነበረው ሰው እንደ መተከዝ ብሎ

«ታዲያ እስከአሁን በሰማንያህ እንዳለህ ነህ?»

«ይሆናል»

«ምን? አታውቅም ማለት ነው?»

ፕሮቴስታንቱ እርግጠኛ መሆንን አልወደደም። ጆን ባፕቲስት ደግሞ ጉተጉተው፡

«ያው፣ ያው ነው። በሰማንያ ስለመሆንና ስለርሱም አለማወቅን በተመለከተ አስገራሚ ነገር አለ»



«ኦ፣ አውቃለሁ፣ ግን እኮ ሕይወት . . . »

«በል፣ በል፣ እስቲ እንዴት እንደሆነ ንገረኝ። ምናልባት እጅግ ስለምፈልገው፣ ሕመሜን ያረሣሣኝ ይሆናል።»

«ጉዳዩ በጣም ቀላል ነው። ነገር ግን ሊያስደስትህ የሚችል ነገር በውስጡ የምታገኝበት አይመስለኝም። ከዚህ በፊት እንደነገርኩህ አባቴ ከዩዜሽ ከተማ ወጣ ብሎ በሚገኝ ቦታ ቀጥቃጭ ነበር። የቤተሰባችን ምንጭ ከኢጣሊያ ነው። ባለፈው ምዕት ዓመት አንድ ጊዜ ቅድመ አያቶቼ ፕሮቴስታንቶች ሆኑ። አስራ ስምንት ዓመት እስኪሆነኝ ድረስ ስለዚህ ጉዳይ ምንም አስተውሎት አልነበረኝም። ምክንያቱም በዙሪያችን በብዛት የሚኖሩት ፕሮቴስታንቶች ብቻ ነበሩ። የአባቴን ሙያ እያወቅሁ ስመጣ፣ እርሱም በዚያ ዘርፍ እንድቀጥል ዕቅድ ነበረው። በሃያ አምስት ዓመቴ አንዲት የአካባቢውን ልጃገረድ አገባሁ። ስሟ ማሪን ይባል ነበር። እነዚያ ዘመናት እንዴት ያሉ እንደነበሩ ብነግርህ ልትገምት እንኳ አትችልም። ይህ ሁሉ ከሃያ አምስት ዓመት በፊት የሆነ ነው። ምንም እንኳ ድሆች ቢሆኑም በአገሬ የነበሩት ሰዎች በጣም ይተሣሰቡ ነበር። እርስ በርሣቸው ይረዳዳሉ፣ በትንሽ ሰበብ ድንቅ በዓል ያከብራሉ። ፕሮስታንቶች ይተባበሩ ነበር። ምናልባት በቁጥራቸው ብዙ ስላልነበሩ መሰባሰባቸው የቡድን አቅማቸውን ስለሚያረጋግጥላቸው ይሆናል። ማሪን እና እኔ በተጋባንበት ዕለት ጧት ከቤተክርስቲያኑ ውጭ መጠነኛ የሕዝብ ክምችት ነበር። የወይን ጠጅ ነበረ። የቫዮሊን ተጫዋቾችም ነበሩ። ከዚያም አንድ ሣምንት ቆይቶ፣ ያለማጋነን ልክ ከአንድ ሣምንት በኋላ ንጉሡ የናንቴስን አዋጅ ሠረዙ። ይህ ሁኔታ ፕሮቴስታንቶች እምነታቸውን በፈረንሣይ ውስጥ በቃለ ምህላ እንዲያረጋግጡ የሚያስገድድ ነገር ነበር። እጅግ የከፋ ነገር እየመጣ መሆኑን ሁላችንም አወቅን። የንጉሡ የጦር ሚኒስቴር የነበረው ዱቮይስ፣ ፈረሠኛ ወታደሮቹ በዚህ አካባቢ እንዲሰፍሩ ይልካል። በዚያን ሰሞን የኛ እምነት ተከታዮች ስብሰባ ስለነበራቸው፣ ከሣምንት በፊት በኛ ሠርግ ላይ ከተገኘው ሕዝብ የበለጠ ቁጥር ያለው ሰው ነበር። የቤተሰቦች መሪዎች የሆኑ ሁሉ ከበግ ቆዳ የተሠሩ ኮቶቻቸውን ለብሰው ትልልቅ ጥቋቁር ባርኔጣዎቻቸውን አድርገውና መፅሐፍ ቅዱሶቻቸውን ይዘው ተገኝተው ነበር። እነርሱም ሁኔታው የከፋ አቅጣጫ ከመያዙ በፊት ዕድሜአቸው በሃያና በሠላሣ አምስት መካከል ያሉ ወጣቶች ከቦታው ዞር ብለው እንዲቆዩ ይወስናሉ።

«አንተም ከጋብቻህ አንድ ሣምንት በኋላ ቦታውን ለቀቅህ?»

«በትክክል ከዘጠኝ ቀን በኋላ ነው። ውሣኔው የተላለፈው በቅሬታ አልነበረም። ማህበረሰቡ ደካሞችን ለመከላከል ሣይፈልግ፣ ተዋጊ ሃይሎቻችንን ብቻ ከጠላት ራቅ ለማድረግ ነበር የፈለገው። ሴቶችን፣ ሕፃናትንና ሽማግሌዎችን ባሉበት ተውናቸው። ወጣቶችንና፣ የመዋጋት አቅም የነበራቸውን ብቻ ከጉዳቱ አቅጣጫ እንዲወጡ ተደረገ። የሆነው ሁሉ እንዲህ ነበር። እኔም ተራሮችንና የካውስስን ሸለቆዎች አቋርጬ በየመንገዱ ላይ እየተደበቅሁ አኩይቴይን ደረስኩ። ከዚያም በአንድ አሣ አጥማጅ ጀልባ ላይ ሥራ አገኘሁ። ከዚያ በኋላ በዊሊያም ስር ሆኖ ጠንካራ ይዞታ ወደነበረው የተባበሩት ግዛቶች አቀናሁ። በዊሊያም ሠራዊት ውስጥ ሆኜ እንግሊዝ ውስጥ ተዋጋሁ። ከዚያም ወደ ቅዱስ የሮማ ንጉሠ ነገስት ግዛት ተመልሼ መጣሁ። ካንተም ጋር ቬነስ ውስጥ የፖሊስ መኮንን ሆኜ እያለሁ ተገናኘን።

«ባለቤትህስ?»

«ስለርሷ ዕጣ ፈንታ ምንም የማውቀው ነገር የለም» አለ ፕሮቴስታንቱ ዐይኖቹን ሰብሮ።

«ታፈቅራት ነበር?»

«ሚስቴ እኮ ነች»

«ያው ነው!» አለ ፖንሴ። «ዘጠኝ ቀናት!»

«ነገር ግን በእግዚአብሔር ፊት የተገባ ቃል ኪዳን እስከዘለዓለም ያስርሃል»

«ሞታ ቢሆንስ ምን ይሆናል?»

«ያን ጊዜማ ነፃ እሆናለሁ»

«እንዲያው የሚገፋፋህ ነገር አጋጥሞህ አታውቅም»

«ብርግጥ የሚገፋፋ ነገር ገጥሞኝ ነበር» አለ ሜትር ዠረሚ ጭንቅላቱን በመነቅነቅ። «እንደምታውቀው የሥጋ ፈቃድ ያሸንፈኛል። ነገር ግን ሚስት ማግባት ሌላ ጉዳይ ይሆንብኛል። በዚህም ላይ ለንስሃ የሚሆን ተገቢው ተቋም የለንም። በዚህ ሣቢያ ይህን ጉዳይ በተመለከተ መሃላዬን አላፈረስኩም»

«ጋርድ ውስጥ ቀበሌህ ማን ይባል ነበር?»

«ሶው ቢይራን»



ከዚህ በኋላ ስለዚህ ጉዳይ አላወሩም። በዚያን ዕለት ምሽት ፖንሴ ለአሊስ ደብዳቤ ፃፈላት። በደብዳቤውም ውስጥ ሜትር ዠረሚ ነፃ እንዳልሆነና በሆነ ዕድል ፈረንሣይ መድረስ ቢችል፣ ስለጉዳዩ እንደሚያስብበት ገልፆላት ስለዚህ ነገር ለፍራንቾይዝ ምንም እንዳትላት አሳሰባት።

የራሳቸውን ምርመራ ካደረጉ በኋላ በአራተኛው ቀን ላይ አባ ፕላንቴይን ወደ ቆንስላው ሄዱ።

«ክቡር ሆይ፣ ዛሬ ጠዋት ከቁስጥንጢንያ በጣም አስቸኳይ ዜና ተቀበልኩ» አሉ ጀስቲቱ ይበልጥ የወታደር በሚመስል ቅላፄ።

ሙሴ ዴ ማይሌ ጆሮዎቹን አቆመ።

«ከአባ ቬርሣው ጋር እንደሚተዋወቁ አምናለሁ» ሲሉ ቄሱ ቀጠሉ።

«ባለፈው ዓመት ካይሮ ነበሩ»

«አዎን፣ ከመርከባቸው መሠባበርና ሌላም ሌላም ብዙ መጥፎ ዕድሎች በኋላ»

«በሚገባ አስታውሳለሁ»

«እንግዲያውማ፣ የአቢሲኒያን ተልዕኮ በሚመለከት፣ የንጉሡን ፍላጐት እርስዎ እንዲያውቁት የማድረጉ ሃላፊነት የርሣቸው እንደነበረም ያስታውሳሉ ማለት ነው»

«በርግጥ»

«የዚያን የኤምባሲ መመለስ እንዲያውቁት ለማድረግ ጽፈላቸው ነበር»

«በመጀመሪያ የተጠቀሙት ቃል ትክክል ነበር። ማለቱ መልዕክተኛ ነበር እንጂ፣ ኤምባሲ አልነበረም»

«እንደፈለጉት ይበሉት፣ይህ ለውጥ አያመጣም። እኔ ደብዳቤዬን በአስቸኳይ መልዕክት የላክሁት አሁን በንጉሡ መልዕክተኛ ዕጅ የሚገኙትን ንብረቶች እንዲበረበሩ ፓሻው ትዕዛዝ ከሰጠ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ነበር። የዚህን ችግር በአጋጣሚ ስጠቅስ፣ የቱርክ ባለሥልጣናትም የኢትዮጵያ አምባሳደር ወደ ቬርሣይለስ እንዳይጓዝ መቃወማቸውንም ገልጬላቸዋለሁ»

«ምን ግንኙነት አለው?» ሙሴ ማይሌ ፊቱ መገርጣት ጀመረ

«አባ ቬርሣው፣ ቁጣቸውን እንድገልፅላቸው ፅፈውልኛል። ምንም እንኳ እኔ በጣም በተለሣለሰ ሁኔታ ጉዳዩን ብገልፅላቸውም፣ እርሣቸው ግን እያንዳንዷን ነጥብ ሲሰልቁት ነበር። እንደገፋልኝ ከሆነ፣ ፓሻው አሁን እንዳደረገው በዚህ ጉዳይ ላይ ጣልቃ የመግባት ምንም መብት የለውም። ከዚህም ባሻገር፣ የተከበሩ ሙራድንና የስር ፖንሴን ወደ ፈረንሣይ መጓዝ መቃወም መብት የለውም። ወደ አቢሲኒያ የተደረገው የመጀመሪያው የተልዕኮ ጉዞ የተከናወነው በንጉሡ ፈቃድ ሲሆን፣ በዚሁ ፈቃድ አማካይነት የአቢሲኒያው ንጉሥ መልስም፣ ለሉዊስ አሥራ አራተኛ ሊደርሣቸው ይገባል»

ቆንሲሉ በንዴት ሲቦር፣ ጥቅል ፀጉሩ አንገቱ ላይ ወደቀ።

«ስለዚህም» አሉ ጀስዊቱ፣ ልክ ውሣኔ የሚያሰሙ በሚመስል አነጋገር « አባ ቬርሣው ይህን ጉዳይ በተመለከተ እያንዳንዱን ዝርዝር ጉዳይ እንድገልፅላቸው ሲጠይቁኝ ይህን በተመለከተ ተቃውሟቸውን ለሙሴ ፌሪኦል በማስታወሻ ለመፃፍ አስበዋል። ሙሴ ፌሪኦልን እንደማስበው . . . »

«አዎን፣ አዎን . . . በኦቶማን ዙፋን የፈረንሣይ አምባሣደር ናቸው»

በምሥራቅ ሜዲተራኒያን ዙሪያ ያሉት ቆንስላዎች ሁሉ ሪፖርት የሚያደርጉት ለሙሴ ፌሪኦል ስለሆነ፣ ሙሴ ፌሪኦል፣ የሙሴ ዴ ማይሌ የቅርብ አለቃው ነው።

«የዚህ ማስታወሻ አብይ ጉዳይ ምን ሊሆን ይችላል?» ሲል ቆንሲሉ ጠየቀ።

«የአባ ቬርሣው ታላቅ ተፅዕኖ ያለበት አምባሣደር፣ ይህን ጉዳይ የያዘውን ሱልጣን አስቀድሞ ያሣውቃል ብዬ አምናለሁ። ይህን በመሣሰሉ ጉዳዮች ከፓሻዎች አንዱ ከስልጣኑ በላይ ከተራመደ፣ ታላቁ ሲኞር ችግር ወደተፈጠረበት ቦታ ምርመራ እንዲያደርግ የቃዲዎች መልዕክተኛ በመላክ አስፈላጊውን ቅጣት ይወስናል። የቱርክ አገረ ገዥዎች፣ እንደ ጥንቱ የፐርሺያ ገዥዎች እንዲሰሩ አልተፈቀደላቸውም። እነዚህ ፓሻዎች ስልጣናቸውን አለአግባብ ከተጠቀሙበት በተገቢው መንገድ ይቀጣሉ»

መጭውን ጊዜ ከማንም ባላነሰ አስቀድሞ መገንዘብ የሚችለው ሙሴ ዴ ማይሌ፣ እነዚህ እንደ ታላቅ የማዕበል ደመና የተነገሩ የማስጠንቀቂያ ቃላት በርቀት ላይ እንዳልሆኑ አውቋል።



«የለም፣ የለም፣ የለም፣ አባ ቤርሳው ምንም አይነት ችግር ውስጥ መግባት የለባቸውም» አለ

«ምን? እና ከምዕተ ዓመት በላይ አስተሣሰረውን የቆዩትን ስምምነቶች፣ ቱርኮች በእግራቸው ሥር ጥለው እንዲረጋግጡት ሊፈቅዱ ነው። ይህን ከተቀበልንማ ስምምነቱ ምንም ማለት አይደለም። በዚህም፣ በዚህ አገር የሚገኙ ክርስቲያኖች እጅግ የከፋ ደም አፋሳሽ የመከራ አይነት ይቀበላሉ ማለት ነው»

«ልክ ነዎት አባቴ፣ ቢሆንም ይህ ተራ ነገር ስለሆነ መፍትሄው እዚሁ መገኘት ይኖርበታል። ቁስጥንጢንያን እዚህ ውስጥ ባንጨምራት?»

«ወይኔ፣ ተከናወነ እኮ። በተሻለ መልኩ ባስረዳ፣ ፓሻው ከሃይል በስተቀር ሌላ ነገር የማይረዳ ይመስላል።»

«ደህና አድርገው አያውቁትም»

«ከዚህ በተለየ መንገድ ላውቀው አልሻም»

«በርግጥ ቱርካዊ ነው፣ በዚህም ላይ ወታደር ነው። ፀበኛ አይነት ሰው ነው። አንዳንዴ ነካ ያደርገዋል። ቢሆንም ምክንያታዊ ነገሮችን ለመስማት ፈቃደኛ ነው»

«መልካም። እንዲያ ከሆነ ምክንያታዊ ነገሮችን ከሱልጣኑ ለመስማት ፈቃደኛ ይሆናል።»

«ይስሙ፣ ከርሱ ጋር ስምምነት ላይ ለመድረስ፣ እኔ ሙከራ እንዳደርግ ይፍቀዱልኝ። ለአባ ቬርሣውም ፈጥነው አይፃፉላቸው። ለፓሻው ለራሱ የተቃውሞ አቤቱታዬን አቀርባለሁ» አለ ከመቀመጫው እየተነሣና እየቆመ።

«እንዲያ ከሆነ ሁላታችንም በጋራ እናነጋግረው»

«አብረን !»

«እምን፣ ምክንያቱም የተጐጂውን ወገን በአንድ በሆነ ስሜት የምወክለው እኔ ነ? ተልዕኮው በኛ የሃይማኖት ማህበር ላይ የተጣለ ሃላፊነትና እምነት ነበር:: እናም ይህ ቱርነ ይህን ተልዕኮና ሃላፊነት እንዳንወጣው እንቅፋት እየሆነብን ነው»

«ሆኖም ጠንካራ ሙስሊም መሆኑን ያውቁ የለ:: የማያስደስተንን ነገር ለመፍቀ ብቻዬን ስሆን ወይም ከርስዎ ጋር ስሆን በተመሣሣይ ሁኔታ አያየንም»

«እንዲህ ከሆነ ከሱልጣኑ ጋር በቀጥታ እንነጋገር:: ቢያንስ እርሱ በሁለታችንም ላ መጥፎ ስሜት የለውም:: ለማንኛውም ደብዳቤዩ ዝግጁ ነው:: የሚጐድለው ነገር ቢና ዝርዝሩ ጉዳይ ነው:: ይህን ደግሞ እርስዎ ያክሉበታል:: ከዘገየም ነገ እልከዋለሁ»

ሙሴ ዴ ማይሌ ያልበው ጀመር:: ከዚህ አጣብቂኝ የሚያመልጥበት መንገድ አልታያ አለው:: ልክ ሁለት አይነት የመሰቃያ ስልቶች ያፈጠጡበት ሰው ይመስል፣ ቀለለ ያለ ስቃ ይኖረዋል ብሎ የገመተውን መረጠ::

«እንግዲያው ይሁን:: ፓሻውን እናነጋግረው»

«ይህን ከተስማማን ወደ ቆስጥንጢንያ የሚላከው ፖስታ ሊዘገይ ስለማይችል አሁኑ መሄድ አለብን»

ቆንሲሉ በዚህ በመጨረሻው አማራጭ ሃሣብ ስለተስማማ፣ የከተማውን ጠባ እንደሚያነጋግር መልዕክት ላከ:: የተላከውም ዘበኛ ከግማሽ ሰዓት በኋላ ሳይዘገይ መደረ ያለበት ከሆነ፣ የስብሰባ አባላት ይጠራሉ የሚል መልስ ይዞ መጣ:: በዚሁ መሠረት፣ ሙ ዴ ማይሌና አባ ፕላንቴይን እንደአስተርጓሚ ሙሴ ማቼን ይዘው፣ በቆንሲሉ ሠረገላ ወጡ: ጀስዊቱ፣ በግልፅ ላለማሣየት ቢችሉም፣ በከፍተኛ ጉጉት ውስጥ ነበሩ:: ቆንሲሉ ደግሞ እጅጌውን ነፋስ እያውለበለበበት በመስኮት ወደ ውጭ ይመለከታል::

ከፍተኛዎቹ መልዕክተኞች ወደ ስብሰባው ቦታ ከደረሱበት ቅፅበት ጀምሮ፣ አንዳች ከባድ የሥራ ጉዳይ እንደተደቀነ ገመተ:: ሥነስርዓታዊውን ሰላምታ በአጭሩ አከናውኖ፣ ቆንሲሉ ይህን አስቸኳይ ጉብኝት የጠየቁበትን ምክንያት እንዲያብራሩለት ጠየቀው::



በጣም ቅር እያለው፣ ጠበቅ ባለና የአስታራቂነት ቃና በተላበሰ፣ ነገር ግን የማመንታትና የውሸት ዜማ በተቀላቀለበት ድምፅ «ጉዳዩ የሚከተለው ነው:: ከታላቅነትዎ ዘንድ የመጣሁት ተቃውሞዬን ላቀርብ ነው»

መሃመት ቤይ መልስ አልሰጠም:: አንዴ ጀስዊቱን፣ ቀጥሎም ቆንሲሉን ተመለከተ:: ከዲፕሎማቱ ጋር ባደረጉት ሕብረት ላይ ቅሬታ እየተማሰው እንደነበረ እያሰበ፣ በዚህ ስምምነታቸው ላይ አንዳች አስቸጋሪ ውጤት መከሰቱን ገመተ:: ሙሴ ማቼ ያስተረጉማል:: ቆንሲሉም ንግግሩን ቀጥሏል::

«በሁለቱ አገሮቻችን መካከል በተፈረመው ስምምነት መሠረት፣ እዚህ የሚገኙት ክርስቲያኖች ሁሉ በፈረንሣይ ንጉሥ ጥበቃ ሥር ናቸው::»

ፓሻው እንደ እነር አይኖቹን በዝግታ ከድኖና ከፍት አደረጋቸው::

«በዚህም ምክንያት የፈረንሣይ ቆንሲል በቅድሚያ ሳያውቀው በፊት የአንድን ክርስቲያን መኖሪያ ሊገቡበት አይችሉም፣ ከዚህም በላይ በሕግ በፈረንሣይ ንጉሥ ጥበቃ ሥር የሚገኝ ሰው ወደ ፈረንሣይ ግዛት የሚያደርገውን ጉዞና ለዚህም ባለሙብት የሆነውን ሰው እንቅስቃሴ ሊያግዱ አይችሉም»

ይህን ተናግሮ ልክ ያቀባጠለው ባልቦላ ደማሚቱን ሲያነድደው ላለማየት እንደፈለገ ሰው ሙሴ ማይሌ ዓይኖቹን ጨፈናቸው::

«ማንን በሚመለከት ነው የሚናገሩት?» አለ ፓሻው በመጨረሻ በቁጣ::

«በማህበረሰቡ ውስጥ ካለ ከአንድ ፈረንሣይ ሐኪም ጋር ከአቢሲኒያ ስለመጣው አርመናዊ»

«እኒህ ከዚህ ሰው ጋር ምን ጉዳይ አላቸው?» ሲል ፓሻው ወደ አባ ፕላንቴይን እያመለከተ ጠየቀ::

ቆንሲሉ በላብ ተጠመቀ:: እንዲያውም ሀሊናውን የሣተም መሰለው:: በሰፊው ክፍል መሃል ላይ ቆሞ፣ ግድግዳዎቹ በአደገኛ ሁኔታ በዙሪያው የሚሽሩ መሰለው::

«ምንም፣ አባ ፕላንቴይን በቅርቡ ወደ ቁስጥንጢንያ ይሄዳሉ። የምንነጋገርበት ጉዳ ውጤቱ አስደሳች የማይሆን ከሆነ የዚህን ስብሰባ ጉዳይ ለአምባሣደሩ ይገልፃሉ» አለ።

አቋሙን ጥብቅ ለማድረግ በሚመስል ሁኔታ፣ መሃመት ቤይ በጉን በኩል ባለው መከ ላይ እጆቹን አሣረፋቸው።

«የናንተን የፈረንሣውያን ሁኔታ መረዳት አልቻልኩም። ምንም ስለሚያውቁት ነገር ምን ፍለጋ ይመጣሉ? ይቃወማሉ? ስለምን? እነዚያን ደብዳቤዎች የወሰድኳቸው እርስ፤ ስለጠየቁኝ ነኝ። ከዘያም ለርስዎ ሰጠሁዎ። አርመናዊውን በተመለከተ እርሱ ነፃ ነው ወደፈለጉበት ቦታ ሊወስዱት ይችላሉ። እርሱ ክርስቲያን ስለሆነ ዕጣ ፈንታው የሚያገባ አይደለም። ይሁንና ለርስዎ ማስጠንቀቂያ አለኝ። ቁስጥንጢኒያ ውስጥ የምትናገሩት ታሪ ካላችሁ የራሴን አንድ ወይም ሁለት ቃላት ልጥልላችሁ እችላለሁ። ከተማዋ ልታስተዳድራቸው ከምትችላቸው ጥቂት ካቶሊኮች በላይ፣ በአሁኑ ጊዜ እዚህ የሚገኙት ፈረንሳውያን ሰባኪዎች ቁጥራቸው በጣም ብዙ ሲሆን፣ በጣም በከፍተኛ ሁኔታ የሚንቀሣቀሱ ናቸው። ጊዜያቸውንም ሴራ ሲጐነጉኑ እንደሚያሣልፉ እናውቃለን። ሱልጣኑም ከነዚ አንዳንዶቹን በዝርዝር ለመስማት በእርግጥ ይፈልጋሉ። ማብራሪያዬ አጥጋቢ ነው?»

«ታላቅነትዎ ሙሉ በሙሉ እንድንቀበል አድርጐናል» ሲል ሙሴ ዱ ማይሌ ወደፊት ጐንበስ የማለቱን ግዴታ ሳይፈፅም ጭንቅላቱን በጨዋ ሁኔታ ዘንበል አደረገ።

ከዚያም ወጥተው ሄዱ።

ሲመለሱ በመንገዱ ላይ ይሰማ ከነበረው ጫጫታና ግርግርታ ጋር ሲነፃፀር፣ የሠረገላው ውስጥ ጉዞ በከባድ ዝምታ የተዋጠ ነበረ። ቆንሲሉ፣ በዚህች አነስተኛ የወንጀል ሕብረታቸው የተነሣ እስከ መጨረሻው ድረስ ቀልዳቸውን እንደሚነፋበትና፣ ሁሉንም ተጠያቂነት ጋሻው ይቀበላል የሚል፣ በተስፋ ላይ ተቃራኒ ተስፋ ነበረው። ይህ ደግሞ አደጋ ያሰበት ስልት ስለነበረ ከሸፈ። አባ ፕላንቴይን በበኩላቸው የምርመራቸው ውጤት መረጋገጡን አይተዋል። ሁሉንም ነገር በሃሰት የፈጠረው ዲፕሎማቱ ነበር። ቁሱ፣ በተቻላቸው ሁሉ ቁጡ ሆነው ለመታየት ሞከሩ። ውስጣቸው ግን በደስታ ይፈላ ነበር። ምክንያቱም፣ ከእንግዲህ በኋላ ሙሴ ዱ ማይሌ ሊከለክላቸው የሚችለው አንድም ነገር አይኖረም። ድላቸውን ያገኙት፣



ጋሻው በራሱ ቀስት ላይ ባስወነጨፈው ተኩስ መሆኑ ርግጥ ነው። ይህ እንኳ እርሣቸውን አላሳሰባቸውም። ቆንስላው ግቢ ሲደርሱ፣ ሙሴ ዱ ማይሌ የቢሮውን በር በነርሱ ላይ ዘግቶ ተቀመጠ። ከዚያም ቄሱ ተመልሰው መሄዳቸውን ለመጠየቅ ሳይጨነቅ፣ ሰው ሰራሹን ፀጉሩን አወለቀው።

«ስለጉብኝቱ ማብራሪያ ልስጥህ ግድ ይሆንብኛል። በእውነቱ፣ የተከበሩ ሙራድን ጉዞ በመቃወም የተነሣብን፣ ጋሻው ሳይሆን፣ የኛው ሚኒስትር ሙሴ ዱ ፖንቻርትሬይን ነው። ስለዚህ ጉዳይ የማያወላውል ማረጋገጫ እዚሁ አለኝ»

ጠረጴዛውን በአመልካች ጣታቸው ጠበጠቡ።

«የፖለቲካ ምክንያቶች ይሆኑ ብዬ አሰባለሁ?» አሉ ጀሰዊቱ።

«የለም፣ የለም፣ የለም!» በማለት ተማሪው የሚፈፅመውን ተመሣሣይ ስህተት ለማረም ባለማቋረጥ እንደሚያስተካክል መምህር ከፍ ባለ ድምፅ ቆንሲሉ ተናገረ። «ይህ የፖለቲካ ጥያቄ ጉዳይ ሣይሆን ከሕይወት ተሞክሮ የሚገኝ የጥሩ ስሜት ጉዳይ ነው። ሌላው ቀርቶ ተገቢነት የሚኖረው ባህርይ ጉዳይ ነው፣ አባቴ። ይህን ሙራድ የሚባል ሰው ደህና አድርገው አይተውታል? ራሱን እንደ መጨረሻው ዝቅተኛ ወዛደር የሚያደርግ ነው። የሴቶችን አይን አፋርነት ይሣደባል። በገበታ ላይ ይሠክራል። እጆቹን በመጋረጃ ጨርቆች ላይ የሚጠርግ ነው . . . እስቲ በእውነት ከልብዎ ይንገሩኝ፣ ይህን አይነት ሰው ለአፍታ እንኳ ቬርሣይለስ ውስጥ እንዲሆን ያስቡታል? ከንጉሡ ፊት ሲቀርብ ሊታይዎት ይችላል?»

ከበላዮቸው ወዳለው የቀለም ቅብ ስዕል አመለከተ።

«በዓለማችን ላይ እጅግ የጠራ የቤተመንግስት ንጉስ፣ ማንም ከዚህ የበለጠ አሣማኝ ሊሆን አይችልም። የሚኒስትሩ መመሪያ ከዚህ የበለጠ ግልፅ ሊሆን አይችልም። ከማን ጋር እንደሚሰሩ አውቀው፣ ሁኔታው ተገቢ ስለመሆኑ የራስዎን ፍርድ ይስጡ። እኔ ግን ልንገርዎ፣ የሚሆን አይደለም»

«ስለዚህ ጥያቄ የሆነው፣ ርዕስ የሆነው ሰው ጉዳይ ነው። በመሠረተ ሃሣቡ ላይ እርስዎም አይቃወሙም።»

«የለም»

«ከዚያ ፖንሴና እኔ ወደ ቬርሣይለስ እንሄዳለን፡፡»

ቆንሲሉ ለአፍታ ያህል አባ ፕላንቱይን በመመርመር አሰበ፡፡ ጀስዊቶች በዚህ ጉዳይ ላ በድጋሜ መሣተፋቸው አላስደሰተውም፡፡ ንጉሡ፣ የራሱን የጅማሮ ሃሣብ እንዲደራደርበ ለማድረግ ተፅዕኗቸውን ሊያሳድሩበት ይችላሉ፡፡ ይሁንና ይህ ከሁለት መጥፎ ነገሮች አነስተ ው ነው፡፡ ጀስዊቶች፣ ቁስጥንጢኒያ ውስጥ የሰዎችን አመለካከት እንዲያስቆጡ ቢፈቀድላቸ እስፈሪ አሉባልታ ይከተል ነበር፡፡ ከዚህም ሌላ፣ ቆንሲሉም፣ ጀስዊቱንና ፖንሴ ከፈረንሣ ከመመለሳቸው በፊት የራሱን የንግድ ድርጅት የመፍጠር ዕድል ይኖረዋል፡፡

«ሃሣቡ እጅግ በጣም ጥሩ ነው» አለ ሙሴ ዱ ማይሌ በመጨረሻ፡፡ «ፍሌሀውት ጠቅላይ ሚኒስትሩ ያጅብዎታል» ፡፡

«እርስዎ በፓሻው ላይ ያለዎትን ተፅዕኖ ተጠቅመው ሦስቱ አቢሲኒያውያን ከኛ ጋ መጓዛቸውን ያረጋግጡልናል»

«ይህን ለማድረግ ቃል እገባለሁ»

«እንግዲያውስ ከፈቀዱ፣ ይህንን ሁሉ አሁኑኑ በጽሁፍ እናስፍረው፡፡ በዚህም፣ ቬርሣይለስ እኛን መጠበቅዎን ትረዳለች፡፡ ነገ ወደ ቁስጥንጢንያ የሚንቀሣቀሰው መርከብ ይህን መልዕክት እስከ አሌክሣንደሪያ ሊያደርሰው ይችላል፡፡ ከዚያም በቤተመንግስቱ የጦር መርከብ ተሣፍሮ በአሥራ ሦስት ማርሴይ ይደርሣል፡፡ በሚቀጥለው ወር መጀመሪያ ላይ ፖሪስ ይገባል፡፡»

«በትክክል፡፡ ነገር ግን፣ ይህ ሁሉ ሲሆን ሁሉም ነገር ከወዲሁ መጠናቀቁን በመግለፅ አባ ቬርሣው በበኩላቸው ምንም እንዳይደክሙ የሚያስረዳ ደብዳቤ ይፃፉላቸው»

«በአንድ ሰዓት ውስጥ እፅፋለሁ፣ ክቡር ሆይ»

ይህ አንድ ስምምነት ይመስላል፡፡ ቢያንስ ይህ ዲፕሎማሲ ነው፡፡ ቆንሲሉ፣ በመጨረሻ ላይ ወደ እውኑ የመመለስ ስሜት ነበረው፡፡ ይህን ከመሰለ ጠንካራ የንግድ ሕይወት ሽታናዮ ይዞት ከሄደው የክርክር ጉዳይ መንቃት ጀመረ፡፡ ከመሽኑፉ በስተቀር ዳግም በሰላም መተንፈስ ጀመረ፡፡



# 10

ሰዎች የወደፊቱን ዕጣ ፈንታቸውን ለማወቅ የኮከብ ቆጠራ ማድረጋቸው የሚያስደንቅ ጉዳይ አይደለም፡፡ የሰማይ ከዋክብት፣ ከሰው ልጅ ጉዳይ ጋር በቅርበት የሚመሣሰል፣ ያልታሰበና የተስተካከለ እንቅስቃሴ አላቸው፡፡ ቆንሲሉ አንድ ጊዜ ከተጋሰጠ በኋላ፣ ሁሉም ነገር ተሰጠጠ፡፡ በዚያን ዕለት ምሽትም፣ ፔጋሰስ የሚባለው ኮከብ ወደ አንድ ወገን ሲሰምጥና እሪዮን የተባለውን ኮከብ ደግሞ ፕሌይዴስና ሌሎች ከዋክብቶች ሁሉ ተከትለውት በሌላው ወገን ከፍ ሲሉ ታየ፡፡

ጆን ባፕቲስት፣ ካልታመመበት ህመሙ በአጭር ጊዜ ውስጥ ዳነ፡፡ ከአራት ቀናት በኋላ ይጀመራል ለተባለው የጉዞ እንቅስቃሴው ዝግጅት በማድረግ ስራ ላይም ተጠመደ፡፡ አስፈላጊ የነበሩ ዝግጅቶች በሙሉ በፍጥነት ተከናወኑ፡፡ ሙራድም፣ በቬኒስያውያኑ ቤት ብቻውን ይሰነብታል፡፡ ቆንሲሉም፣ መልዕክተኞቹ እስኪመለሱ ድረስ ቀለል ያሉ ወጭዎችን ይሸፍንለታል፡፡ ከዚያ በኋላ፣ ከፈረንሣይ ንጉሥ መልስ እንደመጣ ተደርጎ፣ ሙራድ ወደ ኢትዮጵያ እንዲመለስ ይነገረዋል፡፡

ወደ ቬርሣይለስ በሚሄዱ ገፀበረከቶች ላይ አጠቃላይ ምዝገባ ተደረገ፡፡ ከጉንደር በተነሱበት ጊዜ፣ ተንገሮቹ፣ ሃብታሞችና ከባድ ሸክም ያላቸው መስሏቸው ነበር፡፡ ይሁን እንጂ የጉዞው ወጭ፣ ከቱርኮች የዘረፉ ታክስና የአንዳንድ ቀሣቀሶችም መበላሸት ንብረቱን በእጅጉ ቀንሶታል፡፡ ፖንሴና ሸሪኩ፣ ንጉሠ ነገስቱ ከሰጧቸው እንቁና አልማዞች ሌላ እያንዳንዳቸው አንዳንድ ከረጢት የወርቅ ዱቄት ነበራቸው፡፡ ወደ ፈረንሣይ በሚደረገው ጉዞ መሣካት የተጠመደው ፖንሴ፣ለንጉሡ የሚቀርበው ገፀ በረከት በቂ የማይሆን ቢሆን በሚል የራሱን ከረጢት ሊጨምርበት ዳድቶ ነበር፡፡ የሙራድ ሻንጣ በጣም ትንሽ ነበረች፡፡ በርግጥ ሦስት አቢሲኒያውያን አሉ፡፡ የሙስሊሞቹን በንቃት መጠበቅ በሚገባ ስለሚያውቅ እነዚህን አቢሲኒያውያን ይዞ መጓዝ የሚለው ሃሣብ ፖንሴን አላስደሰተውም፡፡ ጀስዊቱ ግን፣ ቀሪዎቹ ገፀ በረከቶች የሚያሣዝኑና ተመጣጣኝ ስላልሆኑ በሚል ምንም ክርክር ሳይደረግበት ቁርጥ ያለ አቋም ይዘው ነበር፡፡ ገፀ በረከቶቹም አራት ፖውንድ የጥርኝ ዝባድ፣ በተሰጣቸው ምክር በኪሣራ ለትምባሆ የለወጡት መጥፎ ሽታ ተቀርቅቧል፡፡ ከዚህም ሌላ በወርቀ ዘቦ የተጠለፉ የሃር ሻሾች አሉ፡፡ ሻሾቹ፣ ጉንደር ውስጥ ከነጭ ካቦርት ጨርቅ አንፃር ቢታዩ፣ እሰም አቀፋዊ

አድናቆትን ያገኙ ነበር። ካይሮ ውስጥ፣ ይበልጥ ደግሞ ቬርሣይለስ ውስጥ፣ በአውሮፖውያን ዕይታ ከአስቀያሚ ቁራጭ ጨርቅ የሚበልጡ አይደሉም። ሲነሱ ይዘዋቸው የነበሩት እንስሳት፣ ፈረሶችና ዝሆኖች በመንገድ ላይ ሞተው አልቀዋል። የቀራቸው ነገር ቢኖር የደረቀውን የዝሆን ቆዳ የያዘው ትልቅ የእንጨት ሣጥን ብቻ ነው። እነዚህ ነገሮች ደህና ተደርገው መጫናቸውን ፖንሴና ሙራድ አረጋገጡ። በይበልጥም ሙራድ፣ እጁን ልቡ ላይ አሳርፎ ልክ ነው አለ። የደከሙ ፈረሶች እየገዛ የሚያርደው ሰውዬ፣ የዝሆኑን ሥጋ ቅርጫ ጉትቶ ሲወስደው፣ ሙራድ የእንስሳውን ጆሮ ምን ሊያደርገው እንዳሰበ ስላወቀ በጨው ውሃ ውስጥ ዘፈዘፈው። ከዚህም በኋላ፣ ከተቀመጡበት የርብራብ ሣጥን ውስጥ ሲወጡ በቀላሉ እጥፍጥፍ የሚሉ ለስላሦችና ልክ በሕይወት ባለው እውሬ ላይ ተጣብቀው ያሉ ይመስላሉ።

አሣፋሪ ማብራሪያና፣ በመደጋገማቸው የሚያዋርዱ ይቅርታዎችን በመጠየቅ የጋለ ቃለምልልስ ከፓሻው ጋር በግል ካደረገ በኋላ፣ ቆንሲሉ፣ አቢሲኒያውያኑ ወደ ፈረንሣይ ለመሄድ እንዲችሉ አስፈላጊውን ሥልጣን እንዳገኘ ለአባ ፕላንቴይን ገለፁላቸው። ጥንቃቄ የሚያስፈልገው፣ የአሌክሣንደሪያ ሙፍቲዎች ስለዚህ ጉዳይ ምንም አለመስማታቸውን ማረጋገጥ ብቻ ነው። እነዚህ ሰዎች አክራሪዎች ስለሆኑ ማንኛውም አፍሪካዊ ወደ ክርስቲያን አገር የሚያደርገውን ጉዞ ይቃወማሉ።

የመሰነባበቻው ጊዜ ደረሰ። ሙሴ ዴ ማይሌ በፈገግታ ተሞልቶ መንገደኞቹን፣ ማለትም ፖንሴን፣ አባ ፕላንቴይን እና ቻንስለር ፍሌሃውትን በቆንስላው ውስጥ እራት ጋበዛቸው። ጆን ባፕቲስት፣ ፍፁም ድኖ መጣ። ቆንሲሉ፣ በአሁኑ ጊዜ ከፖንሴ ጋር በጥሩ ሁኔታ ላይ ለመቆየት ጥንቃቄ በመውሰድ ላይ ነው። ምክንያቱም ከዚህ በኋላ በከፍተኛዎቹ ደረጃዎች ላይ ችግር ሊፈጥርበት ይችል ይሆናል። የእራት ግብዣው የሥራ ጉዳይ ያለበት ስለነበረ ሴቶችን አላካተተም። ሴቶቹ የተፈቀደላቸው ባለፈው ልዩ በዓል ጊዜ ጆን ባፕቲስት ባየው አነስተኛ የሙዚቃ ክፍል ውስጥ ለቡና ብቻ ነበር። ሙሴ ዴ ማይሌም ይሁን ባለቤቱ፣ በአንዲት በጣም አነስተኛ በሆነች ክፍል ውስጥ እምጥተዋቸው፣ እርስ በእርሣቸው በድንገት እንደሆነ በማስመሰል፣ አስር ጊዜ ሲተሻሹ፣ በሁለቱ ፍቅረኛሞች ልቦች ውስጥ የጫሩትን ሃሴትና ግራ መጋባት በሚመለከት ምንም ዓይነት ፍንጭ አላገኙም ነበር። በአባቷ አስገዳጅነት፣ ማዳሞዜል ዴ ማይሌ፣ በፒያኖው አጠገብ ተቀምጣ ጥቂት ጣዕመ ዜማዎችን ተጫወተች። የከር የሙዚቃ መሣሪያዎች ያላቸውን ሃይል ለማውጣት እንዲችሉ፣ እንደሚታኙ ሁሉ፣ ልቦችም በሚገባ መቃኘት ይኖርባቸዋል። በዚያ ምሽት፣ በአጭር ጊዜ ውስጥ ከሚለያዩት ከሁለቱ



ወጣቶች ልቦች በስተቀር በዚያ ክፍል ውስጥ የነበሩት ብዙዎቹ አድማጮች ልቦቻቸው በሚገባ የተቃኙ አልነበሩም። አሲድ፣ የመዳብን ሠሃን አልፎ አልፎ በሰም ባልተሸፈነበት ቦታ ላይ ቅርፅ እንደሚያወጣበት ሁሉ፣ የፒያኖው ጣዕመ ዜማ በጆሰዊቱና በሙሴ ዴ ማይሌ፣ ወይም ለማዳመጥ ፍፁም ፈቃደኛ በነበረው በሙሴ ማቼና በግብዙ ፈሪ በፍሌሃውት፣ መካከል የነበረውን ወሬ አላስተጓጎለባቸውም። ከዚህ ይልቅ ጣዕመ ዜማው በጥልቀት ዘልቆ የገባው በጨቅላዎቹ የአሊስና የጆን ባፕቲስት ልቦች ውስጥ ነበር። ምክንያቱም እጅግ ጣፋጭ የሆነውና የማይታየው የፍቅር ስቃይ በነርሱ ልቦች ውስጥ ካልሆነ በስተቀር በሌሎች ሊታሰብ የማይችል ነው።

ሁለቱም ስሜቶቻቸውን በፅናት ለመቆጣጠር ችለዋል። ነገር ግን የእርስ በርሣቸው የመፈላለግ ረሃብ እጅግ አደገኛ የሆነ ቸልተኝነት እንዲፈፅሙ ሲገፋፋቸው ነበር።

ፖንሴ፣ ወደ ቤት ገና እንደተመለሰ፣ ፍራንቾይዝ፣ በከፍተኛ ጥድፊያ ስትመጣ አያት። የመጣችውም እንደባለፈው ጊዜ፣ አሊስ እኩለ ለሊት ጥቂት እንዳለፈ በአትክልቱ ስፍራ እንደምትጠብቀው የላከችለትን መልዕክት ይዛ ነው። ምሽቱ ጨረቃ ያለችበት ስለሆነ ሊታዩ ይችላሉ። ይህ ደግሞ አደጋውን ከባድ ያደርገዋል። ጆን ባፕቲስት፣ ሀሳቡን ሲቃወመው፣ ስለጨረቃዋ መኖር እንደሚያውቁ ፍራንቾይዝ አስረዳችው። ከዚህ በኋላ፣ ጀግንነት ምኑ ላይ ነው? ሲል ጆን ባፕቲስት አሰበ። ለደህንነታቸው ሲሉ ዕቅዳቸውን መሰረዝ፣ ወይም የድፍረትና የሀሴት ፍላጐታቸውን መምረጥ? እስከ አሁን ድረስ ፍቅራቸው በብዙ እንቅፋቶች የተሞላ ነው። ይህ ደግሞ ተገቢነት በሌለው ማነቆ፣ የግዴለሽነት ወይም የስሜት ቀዝቃዛነት ተደርጐ ሲተረጐም ነበር። በርግጥ ጆን ባፕቲስት የሚችለው አንድ ነገር ነበረ። በቀጠሮው ቦታ፣ እንደሚገኝ መልስ ሰጥቷል።

በቀጠሮው ሰዓት፣ እርሱ በኢደባባዩ ውስጥ ተደብቆ ሳለ በርቀት የሁለቱ ሴቶች ቅርጽ በጨረቃዋ ብርሃን ደምቆ ወደርሱ ሲጣደፉ ተመለከተ። በፍርግርጉ የብረት በር ዘንድ ሲደርሱ፣ ሌላ የሰው ጥላ ከአንድ ወጥ ዛፍ ወደሌላው በድንገት ሽው ብሎ ሲያልፍ ጆን ባፕቲስት አስተዋለ። አሊስ ወደ ፍቅርኛዋ መጥታ ተጠመጠመችበት። ደረቱ ላይ ልጥፍ አድርጉ ያዟት፣ ዝም እንድትል አስጠነቀቃት። ዓይኖቹን፣ ሲንቀሳቀስ ወዳየውና ወደተሰወረበት ነገር አትጣጡ በጨለማው ውስጥ ላከቸው። ከዚያም፣ ያ ጥላ፣ በሁለት ዛፎች መካከል ወደ አትክልቱ ሥፍራ ተንሸራትቶ ሲገባ በድጋሜ ተመለከተው።

«የሚከታተሏችሁ ነበሩ» ሲል ጆን ባፕቲስት ለአሊስ ሹክ አላት::

እነዚህ ቃላት በልቧ ውስጥ ሹበር ነዙባት:: በበሩ አጠገብ ትጠባበቅ የነበረችው ፍራንቾይዝም፣ ያንን ጥላ ተመልክታዋለች:: ከዚያም፣ ወደጥንዶቹ ስትቀርብ ጆን ባፕቲስት ሲያስጠነቅቅ ሰማችው:: ምናልባት ክፉ ነገር ቢያጋጥመኝ እከላከልበታለሁ በማለት አስቦ፣ ፖንሴ ከቤቱ ሲወጣ በቀበቶው ላይ ጋቤ ታጥቆ ነበር:: የጋቤውን እጀታ በፍጥነት ይዞ፣ ያቀደውን፣ ለሁለቱ ሴቶች ነገራቸው::

«ሲከታተላችሁ የነበረውን ሰው ተጋፍጬ ማንነቱን አጋልጣለሁ:: ሁለታችሁም ወደ ቆንስላው በፍጥነት ተመለሱ:: ነገር ግን እንዳትታዩ እየተጠነቀቃችሁ እንጂ እየሮጣችሁ እንዳትሄዱ:: ለመሆኑ የጓሮውን በር ቁልፍ ይዛችኋል?»

«አዎን» አለች ፍራንቾይዝ

«እንግዲያው በጓሮ በኩል ዞራችሁ ሂዱ:: ከዚህ በበለጠ ዋናው ቁምነገር ልክ እቤት ከገባችሁ በኋላ፣ ጭልጥ ያለ እንቅልፍ የወሰዳችሁ ለማስመሰል ሞክሩ:: ምናልባት ነገሮች. . .»

«ሂድ፣ ሰለሌላው አትጨነቅ» አለች ፍራንቾይዝ

ጆን ባፕቲስት፣ አሊስን በችኮላ ሳማት:: የከንፈሮችዋን ጣዕም፣ ልስላሴያቸውን፣ በዓይኖችዋ ውሃዎች ውስጥ የነበሩትን ዕይታዎች በጥልቁ ማስታወሻው ውስጥ ጠብቆ ሊያቆያቸው እንዲችል አጥብቆ፣ ቀመሳቸው:: ከነገ በኋላ ለሚቀጥሉት ረዥም ወራት ጠብቆ የሚያቆየው፣ ይህን ብቻ ነው:: ከዚያም፣ ራሱን ከርስዋ ለይቶ ጨለማው በጣም ከባድ ወደነበረበት የአትክልት ሥፍራ አቅጣጫ ሮጠ:: በፍርግርጉ በር ዞሮ በአንድ የእንጨት በር መግቢያ በኩል ዘለቀ:: በዝግታ ወደ ሰፊው ጎዳና ጥግ በማምራት፣ በአንድ ነጠላ ዛፍ ኋላ ተደበቀ:: የሁለቱ ሴቶች ብርማ ቅርጽ፣ ቆንስላውን በምታዋስነው በትንሿ የእግር መንገድ ላይ ሲሯሯጥ በግልጽ ማየት ቻለ:: የሚያሳድዳቸው ነገር ጥላ፣ መንገዱን አቋርጦ እንደገና በዛፎቹ ጀርባ ከተሰወረ በኋላ፣ ፖንሴ፣ ይህ ጥላ የፈረንሳውያንን የአለባበስ ዘዴ የተከተለ፣ መካከለኛ ቁመት ያለውና ግልጽ ባይሆንም መሣሪያ ያልታጠቀ ወንድ ሰው መሆኑን ለመለየት ጊዜ አግኝቷል:: ይህን ሰው ለመያዝ ከተደበቀበት መውጣት እንዳለበትም አውቋል:: ለዚህ ደግሞ የተሻለው ዘዴ፣ ሰውዬው ላይ ከኋላው በኩል መድረስ ነው:: ምክንያቱም የሰውዬው አትኩሮት በመሸሽ ላይ ወደሚገኙት ሴቶች ነው:: ፖንሴ በበኩሉ፣ በርሱና በፊት ለፊቱ ባሉት ሁለት ዛፎች መካከል ያለውን ርቀት በፍጥነት ሸፈነ:: ወዲያውኑ ሰውዬው መንገዱን



ከማቋረጡ በፊት ተደብቆበት ከነበረው ዛፍ ሥር ደረሰ:: ይህ ማለት ደግሞ ጆን ባንቲስት በትክክል ከሰውዬው ባሻገር በተቃራኒው አቅጣጫ፣ ሰውዬው አትኩሮ ከሚመለከትበት አኳያ ይሆናል::

ሰጥቂት ጊዜ ጠበቀና፣ እንጣጥ ብሎ ዘሎ መንገዱን በማቋረጥ በጨለማው ውስጥ ሲንቀሳቀስ የነበረውን ቅርጽ አፈፍ አደረገው:: ወዲያውኑ የሰውዬውን እንቅስቃሴ በመግታት ጋቤውን አንገቱ ሥር አስጠግቶ ያዘ:: ሊነገር የሚችል ትግል አልተካሄደም:: በጨለማው ውስጥ እንደተነካኩ ሁለቱም መሬት ላይ ወድቀው ተንከባለሉ:: ጆን ባንቲስት በቀላሉ የበላይነትን አገኘ:: በአንፃሩ ባላንጣው ጉልበት ያልነበረው ወይም የፍልሚያ ችሎታ ያልነበረው ስለነበረ ጋቤው አንገቱ ስር እንደተጠጋ ወደብርሃኑ እየተጐተተ በቀላሉ ተወሰደ::

«ድረሱልኝ፣ ድረሱልኝ፣ ጥበቃዎች፣ ጥቃት እየደረሰብኝ ነው»

በፖንሴ የይቅርታ ፈቃድ ስር የተያዘው ሰው በሀይል መጮኽ ጀመረ

«ማቼ!» አለ ጆን ባንቲስት

ማቼ ይብልጥ በሀይል ጮኸ:: ቆንስላው በርቀት ላይ ስላልሆነ፣ በመግቢያው በኩል የቅጭልጭልታ ድምጽ መሰማት ጀመረ:: ይህ፣ ምናልባት የጥበቃ ሠራተኞች መሣሪያዎቻቸውን ሲወስዱ የተፈጠረ ድምጽ ይሆናል:: በየመስኮቶቹ ብርሃን ታየ:: ሦስት ሰዎችም መንገዱ ላይ ወጡ:: ማቼ አሁንም ይጮሃል:: የመጀመሪያው ጋኸት በድንጋጤ ምክንያት እንደተፈጠረ ፖንሴ ያውቃል:: የአሁኑ ጋኸት ግን፣ ሊያድኑት የመጡትን የጥበቃ ሰዎች እርዳታ ለመሣብና አጥቂው እንዲያዝለት ለማድረግ ነው:: እየጮኸ እያለ፣ ጆን ባንቲስትን ተመለከተው:: ጋቤው ጉረሮው ስር በመሆኑ ያለበት ሁኔታ የማያስተማምን ደረጃ ላይ ቢሆንም የፌዝ ሣቅና የዝቅተኛነት ፈገግታ አሣየ::

በርግጥ አሁን የያዝከኝ አንተ እንደሆንክ ታስባለህ? ብሎ የሚናገረው መሠለው::

የጥበቃ ሠራተኞች በሩጫ እየተቃረቡ ነው:: ጆን ባፕቲስት ምርኮኛውን ለቅቆ እግሬ አውጭኝ አለ:: ሦስቱ ተረኛ ዘቦች፣ ማቼ መሬት ላይ ተቀምጦ ጉረሮውን ሲያሻሽ ሲያገኙት፣ የአግራሞትና የመደነቅ ሕምምታ አሰሙ:: እርሱ በበኩሉ፣ አጥቂውን እንዳይከታተሉ ትዕዛዝ ሰጣቸው::

የቀረው ለሊት እንደተለመደው በሰላም አለፈ። ይሁን እንጂ፣ እንቅልፍ በአይናቸው ሣይዞር ያደሩ ሦስት ሰዎች ነበሩ። ጆን ባፕቲስት፣ በሰላምና በጊዜ አንዳችም ችግር ሳያጋጥማት መመለስ ችላ ፈጥናም አልጋዋ ውስጥ ገብታ ይሆንን እያለ እንደተጋደመ ነቅቶ ስለ ፍቅረኛው አሊስ ሲያስብ አነጋ። አሊስ፣ በክፍሏ ትኑር ወይም አትኑር ብሎ የማጣራት ሃሣብ ያደረበት ሰው አልነበረም። እርሷ በበኩሏ የመጀመሪያውን የፀብ ድምፅና የሰውዬውን ፖኸት ብቻ ስለሰማች ለጆን ባፕቲስት የተሰፋ መቁረጥ ፍርሃት ፈርታለች ነበር። በመጨረሻም፣ እንቅልፍ ሳይተኛ ያነጋው፣ ሙሴ ማቼ ነበር። ሙሉ ልብሱን እንደለበሰ፣ በጠባብዋ የብረት አልጋው ላይ ተንጋልሎ፣ በሚቀጥለው ዕለት ምን ዘዴ ሊፈጥር እንደሚችል ሲያስብ ነበር። በሆነ ሰው፣ ጥቃት እንደደረሰበት ቆንሲሉ ማወቁ አይቀርም። እርሱ ደግሞ፣ ይህን የፈፀመበት ማን እንደሆነ መናገር ይኖርበታል። የፖንሴን ስም ማጥፋት በተለይ ለርሱ ጣፋጭ ይሆንለታል። አሊስንና ሴት አገልጋይዋን ይጠብቃቸው ከሆነ ደግሞ፣ ሲያደርገው የነበረና ቀደም ሲል በማየቱ፣ ፖንሴን ለማሣሣት ነው ሊል ይችላል። ከዚህ ቀጥሎ ግን በሕይወቱ ላይ የተቃጣውን ጥቃት እንዴት ማስረዳት ይችላል? ፖንሴ ለምን ሲል ጥቃት ይሰነዝርበታል? በጣም በቀላሉ የሁለቱን ፍቅረኛሞች ድብቅ የፍቅር ግንኙነት መናገር ብቻ ነው። በምንም መልኩ ዋናው ቁም ነገር ይህ ሃሣብ ይሆናል። ቆንሲሉ በበኩሉ፣ ልጁ ወደ ውርደትዋ እየተጣደፈች መሆንዋን እስኪያረጋግጥ የተቻኮለ ነገር አይሠራም። ይህን የመሰለ ከባድ ውንጀላ፣ አንዳችም ማስረጃ ሳይኖረው፣ ማቼ እንዴት ሰው ላይ መደፍደፍ ይችላል? ፖንሴም የዋዛ ሰው አይደለም። ብልጣብልጥ ተንኮለኛ ስለሆነ፣ ሁሉንም ነገር በራሱ በማቼ ላይ በማዞር ለውንጀላውና ምናልባትም ነገሩን በግልግል ለመጨረስ ዘዴ ይፈጥር ይሆናል። ፍቅረኛሞቹን በሌላ አጋጣሚ አግኝቷቸው የሚያስደነግጠበት ጊዜና ዕድል ደግሞ አያገኝም። ምክንያቱም በሚቀጥለው ቀን ፖንሴ ወደ ቬርሣይለስ ጉዞ ይጀምራል። በመጨረሻም ከንጋቱ አሥራ አንድ ሰዓት ሊሆን አካባቢ፣ በተለይ በዚህ ሁኔታ ላይ ሊያከናውን የሚችለውን ጉዳይ ሲወስን እፎይታ አግኝቶ ተኛ።

እንደዚሁም ደግሞ፣ እንቅልፍ ሳይተኛ ያደረው ጆን ባፕቲስት፣ ንጋት ላይ ከአልጋው ወርዶ ሻንጣውን እንደገና ማየት ጀመረ። በተለይም በጉዞው ላይ የማይለየውን የመድሃኒት ሳጥኑን ፈተሸ። ከዚህ በኋላ ጀስዊቱን ሊጠራቸው ወጣ። አባ ፕላንቴይን ገና ቅዳሴአቸውን



መጨረሳቸው ነበርና እስኪያጠናቅቁ ድረስ፣ ጆን ባፕቲስት በመስበኪያው ቦታ ፊት ወዲያና ወዲህ ሲል ቆየ። ቀጥሎ፣ ሁለቱ ሰዎች ቆንሲሉን ሊሰናበቱ ተያይዘው ሄዱ። ፖንሴ፣ በቆንሲሉ ከመጠራቱና ብቻውንም ወደዚያ ከመሄድ ይልቅ አሁን ከቄሱ ጋር መሄዱን በጣም ፈልጐታል።

ሙሴ ዴ ማይሌ፣ ከግማሽ ሰዓት በኋላ በፅህፈት ቤቱ ውስጥ ፒጃማውን እንደለበሰና ሰው ሰራሹን ፀጉሩን ሳያጠልቅ ተቀበላቸው። ማስረጃ ስለሌለው፣ ሊናገረው ባለመቻሉ ቅር እንዳለው፣ ከንፈሮቹን ዘግቶ ፈገግ አለ። በመቀጠልም፣ በተልዕኳቸው ላይ መልካሙን ሁሉ እንዲገጥማቸው ተመኝቶላቸው፣ ጀስዊቱ ምናልባት ክቡር ዴ ፖንቻርትሬይን የማግኘት ዕድልና ክብር ካጋጠማቸው፣ ሰላምታውን እንዲያቀርቡለት ጠየቃቸው። ቻንስለር ፍሌሃውት፣ የጉዞ ልምድ የሌላቸው ስለሆኑ ብርቱ ጥንቃቄና እንክብካቤ እንዲያደርጉላቸውም ጠየቃቸው። በመጨረሻም ክሰር ፖንሴ ጋር ጥቂት ጉዳዮችን ለብቻ እንዲነጋገሩ እንዲፈቅዱለት አባ ፕላንቴይንን ጠየቃቸው።

ቆንሲሉ፣ ከመቀመጫው ላይ ተነስቶ መድሃኒት ቀማሚው ወደ ሚቀጥለው ረዥም ክፍል ተከትሎት እንዲገባ፣ በእንቅስቃሴ አመለከተው። ዝቅ ካለው አድማስ ላይ የተንጠለጠለችው የማለዳ ፀሃይ፣ አቧራ የሞላበትን የጨረር ቀስቷን በጭለማው ክፍል ውስጥ በሰላች ስትልከው፣ ግድግዳውን በሚሸፍነውና ቀለሙ በማይለቀቀው ሐምራዊ መጋረጃ አንፃር ሁለቱን ሰዎች የወየበ አይነ ርግብ በመሰለ መልክ ሸፈነቻቸው።

«በምሽት ፀሐፊዬን ማጥቃትህ ተነገረኝ!» አለው ቆንሲሉ ቀረብ ባለ የማንሾካሾክ ንግግር።

«ይከታተለኝ ነበር። ማን እንደነበረ አላወቅሁም»

«ይከታተልህ የነበረው፣ ሊያጋልጥህ በማለት ነበር። አንተም አንዲት ወጣት ሴትን ከነክብርዋ ስትቀማ በግልፅ ታይተሃል»

«የማህበረሰቡን ታላላቅ እሴቶች መጠበቅ የርሱ ግዴታ ነው?»

«ይህን ለመከላከል ያንተም ድርሻ አይደለም»

ቆንሲሉ የመለሰው ሞቅ ባለ ድምፅ ነበር። ወደ ጀስዊቱ ተመለከተ። ከአስር እርምጃዎች ርቀት ላይ ሆነው እጆቻቸውን በፍቅር የሚመለከቱት ካህን አልተንቀሣቀሱም።

«አንድም ቤተሰብ የቅሬታ አቤቱታ ቢያቀርብልኝ፣ ሌላው ቀርቶ ከሄድክም በኋላ ቢሆን፣ ማዕቀብ ጥዬብህ ይህንኑ እንዲያስፈፅሙ ወደ ፈረንሣይ እንደምፅፍብህ እመን»

መልካም፣ ምንም አያውቅም ማለት ነው፣ ሲል ጆን ባፕቲስት አሰበ። በአክብሮት ጐንበስ አለ።

«ከዚህም ሌላ» ሲል ቆንሲሉ በመጠኑም እንደማፈር ብሎ ቀጠለ። «በዚህ ግዛት ውስጥ ያለውን የግንኙነት ደረጃና መጠን ጨርሶ በማለፍ ከሴት ልጄ ጋር ቃለ ምልልስ ለማድረግ ትፈልግ እንደነበረም ተነግሮኛል»

«አ! ጌታዬ፣ ከልጅዎ ጋር፣ ፍፁም የተለየ ጉዳይ ነው»

«እና ይህ የምትለው ጉዳይ ምንድን ነው? በፈጠረህ ንገረኝ»

በያንዳንዱ የሃሣብ መነሻ ላይ፣ ለፍቅረኛው በመታሰቢያነት ያስቀመጠውን የድፍረትና የጀግንነት ነገር ለቆንሲሉ ሊነግረው ይገፋፋ ነበር። ሁል ጊዜም ቢሆን፣ እንዲህ ያለው ነገር አስቀድሞ ታስቦበት ሳይሆን በድንገትና ባወጣ ያውጣው ተብሎ የሚፈፀም ነው። ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ኢትዮጵያ ለመሄድ፣ ካይሮን ሳይለቅ በፊት፣ ቤቱን እርስዋ እንድትጠብቅለት ሃሳብ ነበረው። አሁን ደግሞ በዚያው ተመሣሣይ የሹክሹክታ ድምፅ ሲከናወን የነበረውን ጭውውት፣ እርሱ ራሱ ሲናገረው በጣም ደነገጠ።

«ደህና፣ ከርስዋማ ጋር በቀላሉ ፍቅር ነው»

ቆንሲሉ፣ በአንድ ቅጥር ነፍስ ገዳይ ፖቤ ጀርባው ላይ የተወጋ ያህል ስቅጥጥ አለው።

«አፈቅራታለሁ» ሲል ጆን ባፕቲስት አይኖቹን ሳይሰብራቸው ቀጠለ «እርስዋም እንዲሁ ብዬ ለማመን በርግጥ መሞኘት ይሆንብኝ . . . »

«ዝም በል! ደግሞ ይህን ሃሳብህን እርግፍ አድርገህ አሁኑኑ ጣለው» አለው ቆንሲሉ ኮስተር ብሎ።

«ይህ እኮ ሃሣብ አይደለም»

«በቃህ አልኩህ! እንደዚህ ያለ ዕቅድ ኖሮህ ስታንሻብብ እንደነበረ ከረዥም ጊዜ በፊት አወቄአለሁ። ግን እንዲህ ያለውን የማይመስል ህልም ይዘህ፣ ስታጠናክረው ትቆያለህ የሚል ተስፋ አልነበረኝም»



«እኔ አጠናክረዋለሁ፣ እርሱም ያጠናክረኛል»

«ደግ እንግዲያው ስታልም ኑር። ሆኖም ግን ከዚህ በላይ አትውሰደው። ለልጄ፣ እኔ ሌላ እቅድ አለኝ»

«እንግዲያው፣ ለርስዋ ከመንገርዎ በፊት፣ እኔ ደግሞ የእርስዋን እጅ እንዲሰጡኝ ለመጠየቅ ማሰቤን ማወቅ ይኖርብዎታል»

ሙሴ ዴ ማይሌ፣ እየደጋገመ ሁለት ወይም ሦስት ጊዜ በሃይል ሣቀ። ድምፁ፣ በትልቁ ክፍል ውስጥ አስተጋባ። ከዚያ በኋላ በማንሾካሾክ ድምፅ ጭውውታቸውን ቀጠሉ።

«ጉዞ ከመጀመሩ ከአስር ደቂቃዎች ቀደም ብሎ፣ ከአንድ ተራ ቤተሰብ ከተወለደ መድሃኒት ቀማሚ እንዲህ ያለ ነገር በአንድ እና ቤት ውስጥ መስማት፣ እንደእውነቱ ከሆነ ማንም የሚጠብቀው አዋጅ ነው»

ቆንሲሉ በፊቱ ላይ መደበኛውን ፈገግታ ፈገግ በማለት፣ ፊቱን በማጨማደድ፣ የሚያስቅ ተዋናይ ላይ የሚያፈጥጥ ይመስል በተደናገረ የንቀት እይታ ተመለከተው።

«ይህ አዋጅ አይደለም» አለ ጆን ባፕቲስት ኮስተር ብሎ። «ማስጠንቀቂያ ነው። እኔ የንጉሡን ፍቅርና የክብር ማዕረግ ይዤ ከርስዎ ጋር ሊያወዳድሩት እንዲችሉ ተመልሼ እመጣለሁ። ታዲያ ያን ጊዜ፣ ያን ጊዜ ብቻ በይፋ እገልፀዋለሁ። ይሁን እንጂ ከአሁን በኋላ ያ ጊዜ እስኪደርስ ድረስ ፅሰርሷ ተብሎ የሚገባ ቃል ኪዳን አይኖርም»

እነዚህን ቃላት መናገሩ፣ ለጆን ባፕቲስት እፎይታና እርካታ ሰጡት። ብልግናና ተበቃይነት፣ ሁልጊዜም ይሣካላቸዋል። ይህ ሁሉ ሲሆን ደግሞ፣ መጥፎ ርምጃ በመውሰዱ የበደለኛነት ስሜት ተሰማው። ባላሸነፈው ጠላቱ ላይ፣ ራሱን እንደዚህ ግልፅ አድርጎ ማውጣት፣ የድል አድራጊነትን ትዕግስት ለጠላት ማሣየት፣ ይቅር የማይባል ስህተት ነው። ምክንያቱም፣ ባላጋራው አሁንም ቢሆን ድባቅ ሊመታው የሚችልበት ጊዜ አለው። አንድ ሰው፣ ተሞክሮና ብስለት እያገኘ ሲመጣ፣ እንዲህ ያሉ የጅል ስህተቶችን ወዲያውኑ የመሰየግ ችሎታ አለው። በርግጥ በትዝታ ስለሚያስበው ጊዜ፣ በፍጥነትና በትክክል፣ ስሜት ሊሰ የሚችል ውሣኔ ለመስጠት፣ ተጠንቅቆ ሊፈፅመው ሲችል፣ ይህን የሚያስጥለው የስሜቱ ሃይል ሊያይልበት አይገባም።

«ይህን ማስጠንቀቂያ በሚገባ መስማቴን ርግጠኛ ልትሆን ትችላለህ» አለ ሙሴ ዴ ማይሌ በሰይጣናዊ ፈገግታ። ከዚያም ጆን ባፕቲስት፣ ከጆስዊቱ ጋር እንዲሆን በዐይኑ ጠቀሰው።

ஃ

በዚያኑ ዕለት ከሰዓት በኋላ፣ ለዚሁ በዓል ሲባል፣ ቆንስላው በተከራየላቸው በአራት ፈረሶች በሚጎተት ሠረገላ ተሣፍረው ለቀቁ። ከነርሱ በኋላ፣ የጣሪያ ከፈኑ እነርሱን ለመደበቅ ሲባል ዝቅ በተደረገበት ጋሪ፣ ሦስቱ አቢሲኒያውያን ትከሻ ለትከሻ ገጥመው፣ ከሸማግሌው አረባዊ ጋሪ ነጅ በስተኋላ ተቀምጠዋል። የጉዞው ሰልፍ፣ ሻንጣዎች ከሚጫኑበት ከሙራድ ቤት ፊት ለፊት ተሰበሰቦ፣ አርመናዊው፣ ፖንሴን በሃዘን ተሰናበተው። ሙራድ፣ ይህን አደገኛ ጉዞ ባለማድረጉ፣ ካይሮም ውስጥ ምንም የነቃ ተሣትፎ የሚያደርግበት ሃላፊነት ስለሌለው፣ ይህንኑም ስለለመደው፣ ቆይታውም ስለሚራዘምለት ደስተኛ ነው።

ሜትር ዠረሚና ጆን ባፕቲስት እንደተለመደው ከወንድማማችነት መተቃቀፍ በስተቀር የተለየ ስሜታዊነት ሳይታይባቸው ተለያዩ። በዚህ ሰዐት፣ ፕሮቴስታንቱ ከካይሮ እንደማይንቀሣቀስ፣ ጆን ባፕቲስት እርግጠኛ ነው። ለርሱም ቢሆን፣ በቬርሣይለስ ዙሪያ እንደፖሰቲካ ሰደተኛ፣ በንጉሡና በጆስዊቶች ዙሪያ ከሚያንዣብብ፣ ወደ አቢሲኒያ ያደረገው የአሥሣ ጉዞ አደጋ በጣም አነስተኛ ነው። ሜትር ዠረሚ፣ ሙራድን እንደሚጠብቀው፣ ስለ እሱም የሚያገኘውን ዜና እንደሚልክለት፣ ፖንስ ሠረገላው ላይ ሲሣፈር ሲል፣ ቃል ገባለት። ከዚያም ጆን ባፕቲስት ጓደኛውን ለብቻው ወሰደው። ማንም ሰው፣ ወደደውም፣ አልወደደውም፣ ጉዞ፣ ተጓዡን ርግጠኛ ባልሆነ ዕጣ ፈንታ ላይ ያደርሰዋል። ሁለት ሰዎችን ለያይቶ የሚያቆይ ሰው፣ ምንም እንኳ በመልካም ባህርይ ቢጠቀስ፣ ለራሱ ይቅርታ አይኖረውም።

«ከፍራንቾይዝ ጋር ጨዋ ሁን፣ እንደማስበው ታፈቅርሃለች» ከሁለቱ አንዳቸውም እንዲህ አይነቱን በራስ መተማመን ልማድ አድርገው አያውቁም። ግዙፉ ሰውዬ፣ ጆን ባፕቲስትን በጅላጅልነት አመለካከት አይኖቹን ሰብሮ ተመለከተው። በመለያየት ጉዳይ የጥድፊያ እንቅስቃሴ ላይ ባይሆኑ ኖሮ፣ ግዙፉ ሰውዬ ግራ መጋባቱን ለመደበቅ በጣም ዓቸግረው ነበር።



«ፖንሴ፣ ምንድን ነው ወደ ኋላ የሚጐትትህ? ዘሆን እኮ» አሉ ጆስዊቱ።

የሠረገላው በሮች በሚገባ መዘጋታቸውን ለማረጋገጥ ሜትር ዠረሚ ከአንዱ ወገን ወደ ሌላው ተሯሯጠና በመጨረሻም የመልዕክተኛው ቡድን ሲንቀሣቀስ ቆሞ ተመለከተ።

ሠረገላዎቹ በቆንስላው ፊት አለፉ። በዚያን ጊዜ ግራጫ የሱፍ ቀሚስ ለብሳ፣ ለባሏ እጇን እያውለበለበችና ቀጥሎም በማጨብጨብ ፖኪቷን ለማፈን እጆችዋን በአፏ ላይ ያደረገችው ማዳም ፍሌሃውት ብቻ ነበረች። ለሁለተኛ ጊዜ ወደሚያፈቅራት ሴት ራሱን ደብልጥ ለማቅረብ ጆን ባፕቲስት ተነስቶ ሲሄድ አሁንም ልበ ሙሉነት ነበረበት።

# 4

# የንጉሡ ጆሮ

# 1

ሲጠቀስ የሚችል የረባ ችግር ሳያጋጥማቸው፣ አሌክሳንደሪያ ደረሱ። ጀስዊቱ፣ የሰስቱን አቢሲኒያውያን ተሰፋና ምኞታቸውን ሁሉ ይከታተላሉ። እነዚህ ሦስቱ አንዳችም ቃል ባይተነፍሱም፣ ይህ ሰው እንዲህ በድንገት ለምን ባሪያቸው እንደሆነና በእንፃሩ ደግሞ፣ እነርሱ የርሱ ጌታ ለምን እንዳልሆኑ እያሰቡ የሚገረሙ ይመስሉ ነበር። ቻንስለር ፍሌሃውትን በተመለከተ ሰውዬው በየዕለቱ በነበራቸው ዕረፍት ላይ ፍፁም አፋቸውን ከፍተው አያውቁም። ይሁን እንጂ፣ የምግብ ሰዓት ትንሽ እንኳ ከዘገየ ሞትኩ እያሉ አንድ ሺህ ጊዜ ይወተውታሉ።

በጉዟቸው ላይ የመጀመሪያው አደጋ ያጋጠማቸው አሌክሳንደሪያ ውስጥ ነበር። ሁለቱ ሰረገላዎች ባህሩ ዳር የደረሱት ከመሸ ስለነበረ፣ ሪጉት በሚባል ፈረንሣዊ ወደ ሆቴልነት የተቀየረው፣ ጥንት የመዝናኛ ቦታ ወደነበረው ፈረሶቻቸውን እየሳቡ ሄዱ። ይህ ቦታ የተመረጠላቸው በሙሴ ዴ ማይሌ ነበር። የሆቴሉም ባለቤት፣ ከቆንሲሉ ለሚያገኘው ድጋፍና ጥበቃ ሲል ሁልጊዜም ሪፖርት ያቀርባል። ሰውዬው፣ መንገደኞቹን ተቀብሎ፣ ራትም አቅርቦላቸው በሁለት የተለያዩ የማረፊያ ክፍሎች ውስጥ እንዲያርፉ በማድረግ፣ ራሱ አስተናገዳቸው። እንደአለመታደልም ሆኖ አቢሲኒያውያኑ የተጫኑበትን ሰረገላ ይነዳ የነበረው የአሌክሳንደሪያው ሽማግሌ ሌሊቱን በመኖሪያ ቤቱ ለማሣለፍ ይወስናል። ወደ ቤቱም ሲሄድ የእጐቱን ልጅ በመንገድ ላይ ያገኘዋል። ይህ የአጐት ልጅ፣ በዚህ የሠራተኞች ሠፈር ውስጥ በጣም አክራሪ ከሆኑት ሙፍቲዎች አንዱ ነው። ሽማግሌው ጋሬ ነጅ፣ ስለ አቢሲኒያውያኑና ስለሚያጅቧቸው ፈረንሣውያን ይነግረዋል። ይህ የአጐት ልጅ ተብዬው፣የሰማውን አስደሣች ትንሽ ዜና በጀለቢያው ውስጥ ደብቆ ይዞ ሄደ።

የቤተመንግስቱ ጀልባ በሚቀጥለው ዕለት ከወደብ ይለቅቃል። ወደቡም ደግሞ ሊታመን ከሚችለው በላይ ሽርጉድና ትርምስ የበዛበት ነው። በጭንቅላታቸው ላይ ሚዛኑን ጠብቀው የተሸከሙትን ዕቃ ይዘው በመሸጋገሪያው ላይ የሚወጡና የሚወርዱ ተሸካሚዎች ክምችት ያበዛል። እነዚህ ኩሊዎች ሲጯጯሁ የሚሰማው የገደል ማሚቶ፣ በመርከቡ ወለልና በመርከቡ ማቆሚያ መካከል ይስተጋባል። ለመርከቡ ቀዛፊዎች ከተያዘው ከታችኛው ጨለማ ወለል በኩልም የሰዎች ድምፅ ይሰማል። ፀሐይዋ ቁልቁል በቀጥታ ስለምትመታ፣ ሁሉም ነገር ያንፀባርቃል። ነጭ ቀለም የተቀቡት የወደቡ ሕንፃዎች፣ የፍራፍሬ ሳጥኖችና ሌላው

ቀርቶ በእንጨት ማንጠልጠያዎች ነፋስ ላይ የተዘረሩት ከርዳዳ የጆንያ ጨርቆች ሣይቀሩ ያንፀባርቃሉ። ጆን ባፕቲስትን፣ አባ ፕላንቴይንና ፍሌሃውትን የጫነው ሰረገላ በትርምሱ ውስጥ ቀስ በማለት አለፈ። ሕፃናት ልጆች የሰረገላውን ትልቅ ተሽከርካሪ የእንጨት ጉማ ይዘው በመንጠልጠል ጉማው ሙሉ ዙር እስኪያከናውን አብረው ይሽከረከራሉ። አንዳንድ ጊዜ ሰረገላው ሲቆም ከሕፃናቱ አንዱ በጭንቅላቱ ሲተከል፣ ሣቅ በሣቅ ይሆናሉ። ከነርሱ በኋላ፣ ብሩህ ሰማያዊ ጣሪያው በፀሐይዋ እየጋመ ያለው የአቢሲኒያውያን ሠረገላ ተከትሏቸዋል። በሕዝብ ከመጨናነቁ የተነሣ ይህ ሁለተኛው ሠረገላ ከቀደመው ጥቂት ርቀት ወደ ኋላ ነው። ጆስዊቱ፣ የመጀመሪያውን ጋሪ የኋላ መሰኮት ከፊት አድርገው አነስተኛ የጭንቀትና የድንጋጤ ድምፅ አሰሙ። ነገሮች ሁሉ ሳይታሰቡ ወደ አመፅ ሲቀየሩ የጉዞው አጀብ ከጀልባው ሃምሣ ጫማ ያህል ይርቅ ነበር። ለፊ ሰማያዊ ካባና የዳንቴል ቆብ የለበሰ አንድ ወፍራም ግብፃዊ፣ እምብዛም ወደ ማይንቀሣቀሰው ሠረገላ በመሄድ የሰረገላውን ሹፌን እንደነገሩ ወደ ኋላ አጠፈው። በዚያ የፀሐይ ብርሃን ውስጥ ሦስት አቢሲኒያውያን በፍርሃትና በጭንቀት ታፍነው ተቀምጠዋል። ወዲያውኑ ከጋሪ ነጅው ቀጥሎ የነበረው ሰው ሰረገላውን እንዲያቆመው አዘዘው። ሽማግሌው አረባዊ፣ የአጉቱን ልጅ ሲመለከተው ትዕዛዙን ወዲያውኑ ተቀበለ። ይህ የአጉት ልጅ፣ ከዚህ በመቀጠል በወደቡ ውስጥ ያሉት ሁሉ ሥራቸውን አቋርጠው እስኪያዳምጡት ድረስ በከፍተኛ የሙኤዚን ድምፅ ጮሆ ተጣራ። በቀጭን የጥጥ ሻሽ ሰውነታቸውን ጠምጥመው ወደ ተቀመጡት ወደ ሦስቱ አቢሲኒያውያንም እያመለከተ፣ የተሰበሰበው ሕዝብ ላይ በሃይለ ቃል ጮኸ። ቀስ በቀስም ሃይለ ቃሉ ወደ መጀመሪያው ሠረገላ አቅጣጫ የክስ ዛቻ እያሰማ ቀጠለ።

«ወደዚያ ተመልሼ መሄዱ ነው» አሉ አባ ፕላንቴይን የሠረገላውን በር እጀታ እየያዙ።

ጆን ባፕቲስት ገታቸው

«ከዚህ ሠረገላ እግርዎ ይወጣና ሞተው ያርፋሉ» አላቸው

ከዚያም ለሠረገላ ነጅው በቀዳዳ በኩል በሚችለው ፍጥነት ሁሉ ፈረሶቹን እንዲያስጋልባቸው፣ ፖንሴ ትዕዛዝ ሰጠው። በፈረንሣይ ማህበረሰብ ውስጥ ነዋሪ የሆነው ጀርመናዊ የሠረገላ ነጂ፣ ሁኔታውን በቅፅበት ተረዳ። ፈረሶቹን እያቻኰላቸው፣ በሚጮኸው የሕዝብ ክምችት መሃል አስፈተለካቸው። ጀልባው አጠገብ ሲደርሱ ሠረገላው ወዲያውኑ



ቆመ። ፖንሴ፣ የሚንቀጠቀጠውን ፍሌሃውትን፣ ከፊት ለፊቱ እየገፈተረውና ከኋላው ሆነው በሌለ አቅሙ እየጐተታቸው ወደ ጀልባው መሣፈሪያ ሮጠ። መንገደኞቹ ከመጣደፋቸውና ከመፍራታቸው የተነሣ ከዋናው ቃዲ ጋር በጀልባው መግቢያ በር ላይ ሆኖ ይጠብቃቸው ከነበረው የመርከቧ አዛዥ ጋር ተጋጭተው ወደቁበት። ሽማግሌው ቃዲ፣ የፓሻውን ትዕዛዝ ለማስፈፀም ያለ ሰው ቢሆንም፣ ጠቀም ያለ ማንቲም ካገኘ ውሳኔውን ጠበቅ እንደማያደርግ መንገደኞቹ ባለፈው ምሽት መረጃ አግኝተዋል። ቃዲው ግን፣ ሌላው ቀርቶ የካሊፋው ወኪል እንኳ ቢፈቅዱ፣ አፍሪካዊ ክርስቲያኖች ከአሌክሣንደሪያ ላይ መሣፈር ፈፅሞ እንደማይችሉ አስጠንቅቋቸዋል። ስለዚህ ሌላው ቀርቶ ዝቅተኛው ሙስሊም እንኳ ቢቃወመው ተስሚነት ስለሚኖረው፣ አቢሲኒያውያኑን የማሣፈሩ ጉዳይ በጣም ደካማ ነው። በዚህም የተነሣ ሊጠገን የማይችል ሁኔታ ተፈጠረ። ባለሥልጣኑ የእጆቹን መዳፎች ወደ ሰማይ ዘርግቶ ሊያደርገው የሚችለው ምንም ነገር አለመኖሩን ተናገረ።

የሠረገላ መኪናው ከዕይታ ተሰወረ። በስሜት የተንጨረጨሩ ሰዎች አጥቅተውታል። አባ ፕላንቴይን እጆቻቸውን አሻሹ። ፊታቸው በሕመም ተጨማደደ። ውስጣቸው ጨሰ።

ጆን ባፕቲስት፣ ጊዜ ሳያጠፋ፣ ሁለት መርከበኞችን ጠርቶ ሻንጣዎችን እንዲጭኑለት ርዳታቸውን ጠየቃቸው። የመጨረሻዎቹ ሻንጣዎች ብድግ እንደተደረጉ የተሰበሰበው ሕዝብ ከሰረገላው መኪና ውስጥ ሦስቱን አቢሲኒያውያን ይዞ ተፈተለከ። እልፍ አእላፍ የነጭ ጨርቅ ቁራጭ ውልብልብታ ካልሆነ በስተቀር ምናቸውም የነዚህ ያልታደሉ ፍጡሮች አይታይም ነበር። ጥቃቱን የመራው ሙፍቲ፣ የቁጣ ዛቻውን በሌላው ሰረገላ ላይ ሲያዞር፣ ከሕዝቡ ከፊሉም ወደዚያው ገሰገሰ። ጀርመናዊው ለመሄድ ነፃ መሆኑን ፖንሴ እጁን በማውለብለብ አሣየው። የሠረገላ ነጅው አለንጋውን በማጮህ ፈረሶቹን ሽምጥ እንዲጋልቡ በማስገደድ በፖኸት ትርምሱ መሃል፣ የሀብሀብ ፍራፍሬዎችና በመንገዱ ዳር የሚገኙ የቸርቻሪ ነጋዴዎችን ዱቄት እየደፋና እየገለበጠ ተፈተለከ። በማምለጡ የተቆጣው ሕዝብ ወደ ጀልባዋ ማመልከት ጀመረ። ብዛት ያላቸውና ከደረታቸው በላይ ርቃናቸውን የሆኑ ወንዶች፣ መርከቡ ጠርዝ ላይ ዘለለው በመውጣት ጀልባው ላይ ለመድረስ እጅ በእጅ ላይ እየተነባበረ ሙከራ አደረጉ።

ሦስቱ ፈረንሳውያን በዋናው ጓደኛቸው አማካይነት በጀልባው ኋላ በሚገኝ ጨለማ ክፍል ውስጥ ገብተው ተቀለፈባቸው። ይህ እየሆነ እያለ፣ የጀልባዋ አዛዥና ሌሎች መርከበኞች ሕዝቡን አገዱት። ብዙ ሺህ የሚሆኑ ድምፆች በጀልባዋ መድረክ ላይ አፍሪካውያንን እየዘረፉ የሚወስዱትን ሰዎች፣ ለበቀል ቅጣት አሳልፈው እንዲሰጧቸው በጉኸት ይጠይቃሉ።

በመጨረሻም የተሰበሰበው ሕዝብ ተበተነ። ጀልባዋም ከወደቡ ጋር የታሠረችበትን ገመድ ፈትታ በባህሩ ላይ መንሳፈፍ ቻለች። ጀልባዋ፣ በባህሩ ላይ መሆንዋ ሲረጋገጥ፣ አዛዡ ራሱ መጥቶ መንገደኞቹን ከነበሩበት ሥፍራ በማውጣት አክብሮቱን ገለፀላቸው።

«ለመሆኑ አቢሲኒያውያኑ ምን አጋጠማቸው?» ሲሉ አባ ኝላንቴይን የኔ ልጆች ቢሆኑ ኖሮ በሚል ስሜት ሳይሆን ለወሬው ጓግተው ጠየቁ።

«በአሁኑ ሰዓት ምናልባት ሁሉም ቁርካውያን ሆነዋል» አለ ካፒቴኑ በትህትና። በርግጥ ለነዚህ ሰዎች ይህ ሁኔታ በጣም መጥፎ እድል ሊሆን ይችላል። የሆነ ሆኖ፣ የፈረንሳይ ንጉሥ ሦስት ዜጎቻቸውን ከማጣት ድነዋልና አሁን ልንደሰት ይገባናል።

የካፒቴኑ ስም፣ ዴ ሁች ሲባል፣ ቤልጂየም ውስጥ ከሚገኙ የፍላንደር ብሔረሰቦች፣ ዲፔ መንደር የተወለደ ነው። ፖንሴንና ጀስዊቱን በፈገግታ እጆቻቸውን ይዞ ከፍሌህውት ጋር እየመራቸው ወደ ክፍሉ ወሰዳቸው። ሦስቱ መንገደኞች ባህሩን በሚያቋርጡበት ጊዜ ሁሉ የዚህ ባህረኛ አስደሣች ለዛ፣ ተጭኗቸው የነበረውን ሀዘንና ትካዜ ሊያስወግድላቸው አልቻለም።

ጊዜው ወርሃ ጥቅምት በመሆኑ፣በወደቡ ዳር የሚጋረፍ የባህር ንፋስ ነበረ። የመርከቧ ቀዛፊ ባሮችም መቅዘፊያቸውን ለማስቀመጥ ችለው ነበር። ከሌሎቹ የጀልባዋ ተሣፋሪዎች ፍፁም ተለይተው ከነበሩት ቀዛፊዎች ሌላ፣ መንገደኞቹ በሙሉ ማለት ይቻላል፣ ወታደሮች ነበሩ። እነዚህ ሰዎች ደግሞ ስለራሳቸው የሚናገሩት ምንም የሌላቸው ናቸው። የግብጽ የወደብ መሬት ከአይናቸው እንደተሰወረ፣ ፍሌህውት በራሣቸው ክፍል ውስጥ ዘግተው በመቀመጥ፣ ጠኔ እስኪጥላቸው ድረስ ምንም አይነት ምግብ አልቀበልም አሉ። ፖንሴ፣ ከሾርባ ውስጥ መድሀኒት በመቀላቀል ምግብ ይልክላቸዋል ቢባልም፣ እንደእውነቱ ግን ምንም ነገር አይጨምርበትም ነበር። ቻንስለሩ፣ የዳኑት በምግቡ ሳቢያ መሆኑን ስላልጠረጠሩ ሐኪሙ ለሚያደርግላቸው ጥሩ ጥንቃቄ አመሰገኑት።



ጀስዊቱ ጥሩ የጉዞ ጓደኛ አልነበሩም። ለረጅም ሰዓታት ያለማቋረጥ አጉንብሰው ይፀልያሉ። ክፍሉን የሚወለውለው ልጅ፣ በቁሉ ዙሪያ ያለውን ቦታ እርሣቸውን ሳለመረበሽ በሚል ሣይወለውለው ይተወዋል። አባ ኝላንቴይን፣ በአቢሲኒያውያን ባሮች ላይ ለሚፈፀሙ በደል እግዚአብሔር ይቅር እንዲል የሚጠይቁ እንደሆነ ፖንሴ ይገምታል። ቄሱ በጣም ስለፈሩ፣ እግዚአብሔርን፣ ስላለፈው ሳይሆን ስለመጪው እያዩ ይለምኑታል። በባህሩ ውሃ ውስጥ እንዳይሰምጡ ብቻ ይፈልጋሉ።

ጆን ባፕቲስት፣ በነፃነትና በደስታ የሚጫወተው ከካፒቴን ዴ ሁች ጋር ነበር። ካፒቴን ዴ ሁች፣ የአንድ ባህረኛ ልጅ ሲሆን፣ በደች ጦርነት ጊዜ በጀግንነት የተዋጋ ኩሩ ወታደር ነው። በጊዜው የአንድ መርከብ ምክትል አዛዥ በመሆኑ፣ ከኮምቴ ዴ ቶርቪል ሥር በታላቁ የቤቺ ሄድ ድል ላይ የውጊያ ተካፋይ ነበር። ዴ ሁች ለንጉሥ ሉዊስ 14ኛ ከልብ የመነጨ ፍቅር ነበረው። ይሁንና፣ ንጉሡን፣ ያየው አንድ ጊዜ ብቻ ሲሆን፣ ለዚያውም ከርቀት ነበር። ስለንጉሡ ብዙ ታሪኮችን ያውቃል። የፈረንሣውያንን ልብ በሚነካው፣ በፍሮንዴ ዘመን ስለነበረው የንጉሡ የሕፃንነት ዘመን፣ ስለዝናው፣ ስላደረጋቸው ውጊያዎች፣ ስለጋብቻውና ስላከናወናቸው ስምምነቶች ያውቃል። ከዚህም በተረፈ በየዋህነት ስላከናወነው የተቃራኒ ፆታ ፍቅር፣ ስለቁባቶቹ የቅብ ስዕሎችና ስለዲቃላው ልጁ የሚያወሱ ታሪኮችም ነበሩ። ባለፉት አምስት አመቶች ውስጥ ወደ ምስራቅ ሲያደርጋቸው በነበሩ ጉዞዎች የተነሣ፣ ዴ ሁች ብዙ የቅርብ ጊዜ ታሪኮች አምልጠውታል። በርግጥ አሁን አፈ-ታሪክ እየሆኑ ያሉትንና እርሱ የአይን ምስክር በመሆን የመጀመሪያ ማስረጃ የሚሆንባቸው፣ በሉዊስ የመጀመሪያዎቹ የንግስና ጊዜያት ላይ ሰፋ ያለ ነገር ያውቃል። ፖንሴ፣ ባለፉት ጥቂት አመታት ውስጥ በአውሮፓ ውስጥ ኖሮ ቢሆን ኖሮ፣ ዴ ሁች ማንኛውም ተራ ፈረንሣዊ ስለንጉሡ ከሚያውቀው የበለጠ እንደማያውቅ ይገነዘብ ነበር። ይሁን እንጂ በዚያ አረንጓዴና ሃምራዊ መዓት መስሎ በሚበጥበጠው ባህርና ከደመናው መሀል በሰያፍ፡ ሸንቁሮ በመጣው ብርሃን ውስጥ፣ በመረከበኛው ሲነገር የነበረው የሉዊስ 14ኛ የሕይወት ታሪክ፣ የግሪኮችን አስደናቂና አስገራሚ የሰዎችንና የድርጊቶችን ጉዳይ የሚናገር አስመስሎታል። በሌላ በኩል ይህ ባህረኛ ምስጋና ይግባውና፣ በንጉሡ ሕይወት ዙሪያ የሚነገሩ በጣም የሚታወቁ ወይም ዝነኛ ድርጊቶችን በዝርዝር ያስታውሣቸዋል። በአቪደስ የትረካ ግጥም ውስጥ ያለው የበግ እረኛ፣ አሸልቦት በነበረበት ሰዓት ከዜውስ የጣኦት አምላክ ጋር በተለመደው ቋንቋ የሚነጋገር ያህል የተሰማውን ስሜት ዓይነት፣ ጆን ባፕቲስትም፣ ከአማልክት ጋር ይስተካከላል ተብሎ ከሚነገርለት ሉዊስ 14ኛ

ሕይወት ውስጥ የገባ ያህል ስሜት ተሰማው። በመሆኑም፣ ጆን ባፕቲስት ስለአገሩ ልጅ፣ ስለፀሐዩ ንጉስ ያለው አድናቆት ከዕለት ዕለት እየጨመረ፣ ልክ በልጆቻቸው ፊት በጥምቀቱ ባህሩ ውስጥ እንደሚነከሩ አዛውንቶች፣ እርሱም በቤተመንግስት ልማድና ወግ ውስጥ በአንድ ጊዜ ተዘፈቀ። በአጭሩ እንደገና ፈረንሣዊ መሆን ጀመረ።

መርከቡ፣ አግሪጀንቶ ወደብ ላይ ለአምስት ቀናት ቆየ። ከዕለታት አንድ ምሽት ላይ ካፒቴኑ፣ አባ ፕላንቴይንና ፖንሴ በኮረብታው ውስጥ በሚገኝ ትንሽ ሆቴል ውስጥ እራታቸውን ለመብላት ሄዱ። በኮረብታው እርከኖች ላይ ተቀምጠው ወደቡን ቁልቁል እንዳያዩት ጊዜው ሞቃት ነበር። የሐረግ አትክልቶችን የደገፉ እንጨቶች በሃይለኛ የመኸር ወቅት ነፋስ ይናወጣሉ። ወደ መርከባቸው ሲመለሱ ለንጉሡ ከሚቀርቡት ገፀበረከቶች መሃል የሆነው ትምባሆ ተሰርቆ ደረሱ። ከዕቃ ቤቱ ቀጥሎ ባለው ክፍል ውስጥ የተኛው ፍሌሃውት፣ ሚስቱ በማንም ላይ ጣቱን እንዳይቀስር መክራው ካልሆነ በስተቀር፣ ምንም ነገር አልሰማም። ካፒቴኑ፣ በጥበቃ ላይ የነበሩትን ሰዎች ጠየቃቸው። እነርሱም፣ ሕፃናት በመርከብ መቆሚያው አካባቢ ሲንሸራተቱ እንደነበረ በአንድ ቃል ተናገሩ። እዚህም፣ እዚያም ቅጣት ቢፈፀምም፣ የንጉሥ ሉዊስ 14ኛ ትምባሆ፣ ወደቡን በከበቡት አረንጓዴና ግራጫ ተራሮች ውስጥ እንዳ ዘንድ ተጢሷል።

ከዕለታት አንድ ቀን ከንጋቱ በአሥራ አንድ ሰዓት ላይ ተንቀሣቀሱ። በዚህ ጊዜ ነፋሱ በአንፃራዊነት ስለሚመጣባቸው፣ መርከቡ ከማዕበል ጋር ሲጋጭ፣ ቢጫ አረፋ መተፋት ጀመረ። ይዘንብም ስለነበረ፣ የመርከቡ ሽራዎች አልተወጠሩምና ቀዛፊዎችም ለብዙ ሰዓታት ከፍተኛ ሥራ መሥራት ነበረባቸው። እንዲህ ባለው ጊዜ፣ የመርከቧ ቀዛፊዎች በምን ዓይነት መከራ ውስጥ እንደሚቆዩ፣ በምን አይነት አሰቃቂ ሁኔታ ላይ እንደሚሆኑና ይህን ሁልጊዜም ችለውት የመኖራቸውን ነገር ትክክለኛ ሥዕል ለማየት እንዲችል ቢጠይቅ ይሻል ይሆን? ወይስ ደግሞ ሁለት ወለል ዝቅ ብሎ በሚገኝ ቦታ ላይ የደከመው ሰውነታቸው ከእግዳሚ መቀመጫዎቹ ላይ በሰንሰለት ታስሮ የሚገኘውን አካላቸውን በዓይነ ህሊናው እየተመለከተ እያንዳንዱን የዕረፍት ጊዜውን በጥፋተኝነት ስሜት እንዲበጠብጠው ቢያደርግ ይሻል እንደሆነ ፖንሴ በትክክል ማወቅ አልቻለም። ለጊዜውም ቢሆን ከሁለት አጫጭር ሰርጦች በኋላ የመርከቧ ስቃይ አብቅቶ ማርሴይ ወደብ ደረሱ። ከመርከቧ ፊት ላይ ሆኖ ጆን ባፕቲስት እሮጌውን የመርከብ መቆሚያ ቦታ እየቀረበ ሲመጣ በትዕግስት ማጣት ተመለከተው።



መርከቧ፣ ወደቡ ላይ በሚገባ ከታሠረች በኋላ፣ ካፒቴኑን ደህና ሁን ብሎት በዝግታ ወደ ዳርቻው ዘለለ።

ባህሩን በማቋረጥ ላይ በነበሩት ጊዜ ያሣዩት በነበረው ነፃነት እምነት አድሮበት፣ ጄስዊቶቹ በርሱ ላይ ያላቸው ቁጥጥር የላላ ይሆናል ብሎ አስቦ ነበር። አባ ፕላንቴይን፣ ጠንቃቃ ሰው ሲሆኑ፣ በማንኛውም ሁኔታ በባህሩ ላይ በነበራቸው ፍርሃት ተወጥረው ያሉ ናቸው። ነገር ግን በማርሴይ ወደብ እንደደረሱ የሚያጠራጥሩ ነገሮች ተወገዱ። አምስት፣ ጥቋቁር ቀሚሶች የለበሱና ሦስት ተመሣሣይ ቀለማት ያላቸው ሠረገላዎች ከመርከብ መቆሚያው ስፍራ ላይ ቆመው ይጠብቋቸዋል። በኦክሲጆንና በእንቅልፍ እጦት ደክምክም በማለት ከክፍሉ በቃሬዛ የወጣው ፍሌሃውት ብቻ ሲሆን፣ ትዕይንቱንም የቀብር ስነስርዓት ነው ተብሎ ቢነገር የሚታመን ዓይነት ነበር። አባ ፕላንቴይን፣ እግራቸው መሬቱን ከነካበት ቅፅበት ጀምሮ፣ ሕይወታቸው ለምልሞ ባልደረቦቻቸው የሚያቀርቡላቸውን እንኳን ደስ ያለዎት አቀባበል በመቀበል አንደኛው ሠረገላ ውስጥ ገብተው ተቀመጡ። ፖንሴ፣ ቀዩን ከፋይ ሙሉ ልብሱን እንደለበሰ ውስን ደስታና ነፃነት ይሰማዋል። እርሱም፣ የሬሣ መጫኛ ከሚመስሉት ሠረገላዎች ውስጥ ገብቶ ከሌሎች ጋር እንዲቀመጥ ግድ ሆነበት። ዙሪያውንም አመዳምና የጆንያ ልብስ የመሰለ ፊት ባላቸው አዲስ የጥበቃ ወታደሮች ተከበበ። ወዲያውም፣ ጀስዊቶች ወዳላቸው ማረፊያ፣ ወደ ፋርስ አቅጣጫ አመሩ። ማረፊያው፣ ሮም ውስጥ በሚገኘው በዝነኛው ኢል ጌሱ ሞዴል ከደፍጣጣው ቤተክርስቲያን ቀጥሎ ወደታንፀውና ታላላቅ የነጭ ድንጋይ ጥርብ ቅርፆች ኖረውት በዝርግ የሮማ የጣሪያ ሸክላ የተሠራ ነው። ጆን ባፕቲስት፣ በሦስተኛው ፎቅ ላይ የምትገኝ ጠባብ ክፍል ተሰጠችው። የክፍሏ መስኮቶች ወደ ክፍሳተ ሃገራት ሁሉ ማሣየት የሚችሉ ናቸው።

በአንድ ጐን ወደማርሴይ አቅጣጫ የሚያመሩ ቤቶች ሲኖሩ በሌላው በኩል ደግሞ የሚያማምሩ የባላገር የእርሻ ሥፍራዎች፣ጥድ መሠል ዛፎች በሰልፍ የተተከሉበትና በየመሃላቸው የጥድና የሰውዝ አይነት ዛፎች የተደባለቁባቸው ይታያል። ራቅ ባሰው አድማስ ጠመልማላ ነጭ መስመር፣ የአልፕስ የበረዶ ቁንጮ የመጀመሪያው ጉብታ፣ ደመና ካንገላታው ፍፁም ቢጊ መሬትና ዝናብ ካጠበው ሰማይ ለይቷቸው ይታያል። በዚህ ጊዜ ራሱን በክፍሉ ውስጥ ለይቶ ያቆየው ፖንሴ ነበር። ይህን ያደረገው ከጀስዊት ካህናቱ ጋር በመሆን ከሌሎች ጋር የመጫወቱን ጉዳይ ለማምለጥ ሲል ነበር።

ከሁለት ቀናት በኋላ ተጓዦቹ በሌላ ጥቁር ሠረገላ ላይ ተሳፈሩ። ይህ ሠረገላ ለመንቀሳቀስ እንኳ ደካማ የነበረ ሲሆን፣ ጋሪ ነጂውም እጅግ ዝቅተኛ ክፍያ የሚያገኝ ተቀጣሪ መሆኑ የማያጠራጥር፣ ለቀጣሪ ጌቶቹ አውጥቶ ሊገልፅላቸው ያልቻለውን ተስፋ መቁረጥና ብስጭት ለተሳፋሪዎች የሚወተውት ነበር። ይህ ምስኪን፣ በመንገዱ ላይ በሚገኙት የተቦረቦሩ ቦታዎች ሁሉ ላይ ሆን ብሎ ፈረሶቹን በሙሉ ሀይላቸው እንዲጋልቡ በማድረግ ተሳፋሪዎቹ ከአንድ ጊዜ በላይ አንዳቸው በሌላኛው ላይ እንዲወድቁ የሚያደርግ ይመስላል። በዚህ የተነሳ ያገኙትን ሁሉ በመጨበጥ ሲዋከቡ ተጉድተውና ከፍቷቸው ስለነበረ፣ በመንገዳቸው ላይ ምንም ነገር ማየት ሳይችሉ፣ ሶስቱ የመንግስት መልዕክተኞች እንዲቀዩበት በማለት ጂስዊት ካህናት ወዳዘጋጁላቸው ቻቴ ዴ ሲሚአኔ በድቅድቅ ጨለማ ደረሱ።

ከበርቴው ዴ ሲሚአኔ፣ ግዙፍና ደስ የሚል ጨዋ ሰው ሲሆን፣ የሚያስደስት የክፍለ ሃገር ቅላፄ ይናገራል። ይህ ከበርቴ እንግዶቹን እስከሚቀጥለው ሁለት ቀን ድረስ ይመጣሉ ብሎ አይጠብቃቸውም ነበር። በተፈጠረው አለመግባባት በጣም ቅር ቢለውም የአደን ልብሱን እንደለበሰና በሚያደርገው ተግባር እንግዶቹ እንዳያዝኑበት በቀላል አቀራረብ ሰላምታ ሰጥቶ ከተቀበላቸው በኋላ ባለቤቱንና ሁለት ወንዶች ልጆቹን አስተዋወቃቸው። ልጆቹ በሚደንቅ ሁኔታ ቁርጥ እናታቸውን ናቸው። ረዣዥምና ሹል አፍንጫ፣ ጥቁር ፀጉርና ክብ ፊት ያላቸው ናቸው። በትዳር ብዙ በመቆየት ብዙ ያተጉዳችና ድቅቅ ያለችው ይህች ሴት በስጦቻቸው ወጣትነትና ቁንጅና ሳቢያ በነዚህ ሁለት ጠንካራ ልጆችዋ ተደግፋ፣ ባልተቋረጠ ሁኔታ በሚሰጧት አትኩሮት እየታደሰች ያለች መሆኗ ሲታይ ያኮራል። በዚያን ዕለት ምሽት ከአደን የተገኘ ምግብ በቢጫ ሰማያዊ የሸክላ ገበታ ላይ ቀርቦላቸው ተመገቡ።

«አያችሁ፣ እንዲህ የተደረገው ልክ እንደቤታችሁ እንዲሰማችሁ ነው» አለ አስተናጋጃቸው እየሳቀ።

ክብ፣ ግዙፍና በጣም በሚያብረቀርቀው ሳህን ጀርባ ላይ የቱርካውያንን ሁኔታ የሚገልፀውን የጌጥ ቅርፅ አሳያቸው። በዚህ ቅርፅ ላይ ሰጉን የሚያድኑ ቱርኮች፣ በአንድ የፏፏቴ ምንጭ አጠገብ ቁርአን ሲቀሩና በረዥም ረድፍ ገብተው ፈረስ ሲጋልቡ የሚያሳይ አለበት።

በሚቀጥለው ዕለት ያህንኑ ከበርቴ ለአደን አብሮት ሊወጣ ይችል እንደሆነ ፖንሴ ጠየቀው። የአስተናጋጁ ልጆችም ተጨመሩና አራት ሆኑ። ደኑ፣ በሞቃት ጭጋግ ተሸፍኖ፣



ወርቃማ ቅጠሎችም ውሃ ያንጠባጥባሉ። በዚህ ወቅት እሾሃማ ቅርፊት ባለው የሰውዝ አይነት የተሸፈነው ወፍራም ብስባሽ፣ የፈረሶቻቸውን የኮቴ ድምፅ ያፍነዋል። ከሌልኸስ ተራራ በረዷማ ነፋስ አፍንጫዎቻቸውን ሲወጋው የጥድ ደንና የጥድ ሽታ መዓዛ ይደርሳቸዋል።

ከመሸ በኋላ ደረሱ። ማዳም ዴ ሲሚአኔን ከጨፍጋጋዎቹ ከፍሊሀውትና ከአባ ኻላንቴይን ጋር የአራት ሰዓት እስኪያልፍ ድረስ ለብቻዋ ትተዋት በመሄዳቸው አፈሩ። ይሁንና በአደናቸው ተደስተው፣ ደክሟቸው ነበር የተመለሱት። ምንም እንኳ ሶስት ቃላት እንኳ በመነጋገር ባይለዋወጡም፣ በአደናቸው ላይ እርስ በርሳቸው ጣዕማቸውን የተዋወቁ ወዳጆች ሆነው በመቆየታቸውም ተደስተው ነበር።

አዳኞቹ ልብሶቻቸውን ለውጠው ቀለል ያለ ዕራት በሉ። የቀሩት ቀደም ሲል ወደየመኝታቸው ሄደዋል። ፖንሴ በሚቀጥለው ቀን በዚሁ መንገድ፣ በዚያው ጥቁር የወፍ ጉጆና የቁራ አሞራ ያለበትን ቦታ ተከትሎ የመሄዱ ሃሳብ ስጋት ቢያሳድርበትም፣ ሙሴ ዴ ሲሚአኔ፣ ፈረስ ከነኮርቻው ቢሸጥለትና በዚያ ሊጓዝ ይችል እንደሆነ ጠየቀው። በርግጥ በዚያ መንገድ በቀን ብርሃን በሠረገላ ሊጓዝ ይችላል።

«ሙሉ በሙሉ እገነዘባለሁ። ወደ ፈረንሳይ ገና መመለስህ ነው። ስለዚህም በታላቅ ደስታ ልትለማመደውና በነፋሱ ውስጥ ልትንሸራሸር ፈልገሃል። እኔ ራሴም ብሆን በቤት ውስጥ መዋል በጭራሽ አልችልም ነበር። ለዚህም ነው በየአደባባዩ የማልገኘው። አሁን ለሽርሽርህ ፈረስ ያስፈልግሃል። ይህንንም ነገ ታገኘዋለህ። ወርቅህን ለሌላ ጉዳይ ስለምትጠቀምበት ያዘው። እግዚአብሔር ፈቃዱ ሆኖ ስትመለስ ይህን ፈረስ መልሰህ ታመጣልኛለህ። ወይም ሌላ ወይም ጭራሽም አታመጣልኝም። አንተን እዚህ ቤት ሁልጊዜም ልንቀበልህ ዝግጁ ነን» አለው ከበርቴው።

አራቱም ሰዎች በእሳት ማንደጃው ዙሪያ በአንድ ትልቅ ባለመከዳ መቀመጫ ላይ ተቀምጠው ሳሉ፣ ሙሴ ዴ ሲሚአኔ፣ ስለአቢሲኒያ ጥቂት ነገር እንዲነግራቸው ፖንሴን ጠየቀው። ፖንሴም ሊተርክላቸው ከሚችላቸው ሁሉ አቢሲኒያውያን ዝሆንን እንዴት እንደሚያድኑ ሊነግራቸው መረጠ።

የፖንሴ ትረካ ማረካቸው። ሙሴ ዴ ሲሚአኔ፣ ሌላ ታሪክ እንዲነግራቸውም ለመነው። በመጨረሻም የአቢሲኒያ ጉዞው ታሪክ ከስሊቱ ረዥሙን ጊዜ ነቅተው እንዲቆዩ አደረጋቸው። እንዲያውም ፖንሴ የግድ መተኛት እንዳለበት ባይናገር ኖሮ እነርሱ እስከ ንጋት ድረስ ሊያዳምጡት ዝግጁ ነበሩ።

የትረካው ስኬት የጥሩ ጎድ ምልክት እንደሆነ ሀኪሙ ታየው። ስለጉዞው ሲተርክ ይህ የመጀመሪያው ሲሆን በሰዎች ላይ ባሳደረውም ጥሩ ስሜት ተደፋፈረ። ንጉሡም ተመሳሳይ ስሜት ካሳቸው ያለችግር እማርካቸዋለሁ ሲል አሰበ።

በማግስቱ ጧት ጆን ባፕቲስት በቁንጥንጥ ሽክላ ፈረስ ላይ ተቀምጦ ከቻቲው ዴ ሲሚአኔ ወጣ። ወደ ቫሌንስ በሚወስደው ጉዳና ላይ ከሠረገላዎች ፍጥነት ጋር በዝግታ ሲሰግር ተሳፋሪዎቹ ሲንገጫገጮ አይቶ እጅግ ተደሰተ። ሰማዩ፣ ቱርካዊ የማይታይበት፣ሰማያዊና ግራጫ ዘይት የተቀባ ሳህን ይመስላል ሲል ጆን ባፕቲስት አሰበ።



# 2

ከጆን ባፕቲስት ጋር ለመጨረሻ ጊዜ በሌሊት ከተገናኙ በኋላ፣ አሊስ ስለርሱ በጣም ትሰጋ ነበር። በማግስቱ ጠዋት ግን፣ ደህና መሆኑን ፍራንቾይዝ አረጋገጠችላት። ከሰዓት በኋላ በወይን ተክሉ ውስጥ ከሚያገለግለው ሠራተኛ፣ እናቷ «ምስኪን ሙሴ ማቼ» ብላ የምትጠራው ሰው በሌሊት ጥቃት እንደደረሰበት ሰማች። ሁሉንም ነገር ስላወቀች ተናደደች። ነገር ግን ቁጣዋን ብዙም ሃዘኔታ በማይሰማት «በምስኪኑ ሙሴ ማቼ» ላይ አላነጣጠረችም። ቀደም ባለው ጊዜ ይህን ከመሰለው ሰው ጋር እንዴት ጓደኛ ለመሆን እንደበቃች ስታስብ ይገርማታል። አሁን ግን በሚገባ እያየችውና እንደምታምነውም በሚገባ እየመዘነችው ነው። እርሱን ከጆን ባፕቲስት ጋር ማወዳደሩም ፍርደገምድልነት ነው። በርግጥ በአሁኑ ሰዓት የዚህ ሰው አድርባይነት፣ ወኔ ቢስነት፣ ተፈጥሮአዊ ቅሌቱ፣ ምንም እንኳ በርሱ ላይ ሙሉ በሙሉ ባትደፈድፍበትም፣ ቁልጭ ብሎ ታያት። የቁጣዋን ነበልባል ሙሉ በሙሉ ያሳረፈችው በአባቷ ላይ ሆነ። በጣም በርግጠኝነት ሙሴ ማቼ ትዕዛዝ በመቀበል እርሷን ለቆንሲሉ እንደሚሰልላት አውቃለች።

አሁን በቅርቡ የተገነዘበችው እውነታ ቢሆንም፣ አሊስ በአስተሳሰብዋና በተግባርዋ፣ ምክንያታዊና ፅንፈኛ ሰው አልነበረችም ማለት አይደለም። ሳቅ፣ ጨዋታና ቀልዶችን ሳለማወቅዋና ሳለማሟላትዋ ሃላፊነቱን በሙሉ በአባትዋ ላይ ከመረችበት። በአሁኑ ጊዜ ከጆን ባፕቲስት ጋር የመለያየትዋንና የግል አስተሳሰብዋንም በአባቷ ላይ አመካኘች። ፍቅረኛዋን ለመጀመሪያ ጊዜ ስታውቀው እርሱ አስቀድሞ ወደ አቢሲኒያ ለመጓዝ ውል ፈፅሞ ነበር። ያ የማንም ጥፋት አልነበረም። በአሁኑ ጊዜ ግን ጆን ባፕቲስት የሄደው በአባቷ ምክንያት ነው። ይህ ሁሉ የሆነው በአባቷ ሃሳብ ግትርነት፣ ሀሳበ ውሱንነትና ለሌሎች ሰዎች በተለይም ለሴት ልጁ ሕይወት ባለው ግዴለሽነት የተነሳ በጋብቻዋ ሂደት ላይ ደንቃራ እያስቀመጠበት ነው። በተጨማሪም፣ ከጆን ባፕቲስት ጋር ሊኖራት የነበረውን የመጨረሻ ጊዜ ለማበላሸት፣ ቆንሲሉ አባትዋ ተከታታይ ሰላይ ስለላከባት ከነነችው። እርሷና ፍራንቾይዝ ልቦቻቸው እየጋለቡባቸው በጠባቦቹ ታኮ ጫማዎቻቸው ያንን የተረገመ ሰላይ ለማምለጥ ሲያደርጉት የነበረውን የሚያዋርድ ጊዜ መልሳ መላልሳ በዓይነ ህሊናዋ ሥዕሉን ተመለከተችው። የአደን ትርዒት ነበር። ልክ ነው፣ አባቷ እንዲያድኗትና እንዲያሳድዷት እንደ አደን እንስሳ ይቆጥራት ነበር።

ይህ ደግሞ እውነተኛውን የሃይል ሚዛን የሚያንፀባርቅ ነበር። እርሷና ጆን ባፕቲስት የሚያንፈንፏቸውንና የሚያድኗቸውን ውሾች ለማምለጥ በበቆሎ ማሳ ውስጥ እንደሚደበቁና እንደሚሸሹ ጥንቸሎች አይነት ነበሩ።

እንደለውዝ ቅርፊት ልቧን ከሰበረባት ከዚህ ትዕይንት ተነስታ፣ አሊስ የሕፃንነት ዘመንዋን በሙሉና በትምህርቷ ላይ ስላለፈው ጊዜ መልሳ አሰበች። በርግጥ ያ ዘመንዋ በዚያን ጊዜ በአጠቃላይ ለሴት ልጆች ከተወሰነው የበዛም፣ ያነሰም አልነበረም። በሕፃንነትዋ፣ አብይ ሃላፊነትዋና ተግባርዋ በነበረው በምግዚቷ እጅ፣ እልፎ እልፎ ወላጅ እናትዋ በምትገኝበት ቦታ በሳምንት መጨረሻዎች ላይ እንድትገኝ ትደረግ ነበር። ከዚያ በኋላ አሊስ ወደ እመምኔቶች ትምህርት ቤት ገባች።ይህ ያደገችበት ቦታ በዙሪያዋ እንዳሉት እንደሌሎቹ፣ በሩ ለዓለም ክፍት የሆነ፣ ቅልጥፍናና አዲስነት የነበረው አልነበረም። ከዚህ ይልቅ በባላገር ጨለማ ሕይወት ውስጥ ከሥልጣኔ ርቃ እንድታድግ ነበር የተደረገው።

እንዲህ ዓይነቶቹ የተገለሉ ሕፃናት የነበራቸው ብቸኛው ተስፋ፣በተቻለ ፍጥነት ወደሌላ የጥገኝነት ግንኙነት ማለፍ ነበር። ይህ ማለት ወደ ማያውቁትና ወዳልመረጡት ባል ቤት ገብተው የቤት እመቤቶች መሆን ነው። ተጀምሮ እስኪጨረስ ድረስ ለዚሁ ፅጣ ፈንታ የሚያዘጋጃቸው ይመስል፣ ሕብረተሰቡ በፈረስ ጭራና በብረት ኮቴዎች የታጨቁ ትራሶችን በክብረ በዓላት ጊዜ እንዲለብሷቸው በማስገደድ ትምህርት ይሰጣቸዋል። ካይሮ በሚገኘው በቆንሲሉ መኖሪያ ቤት፣ እነዚህ የአለባበስ ወጎች የተለመዱ መሆናቸውን እንድታውቅ የሚያደርጋት ሰው በዙሪያዋ አልነበረም። እርሷ ግን ከልምድ በመነሣት ትፈፅማቸው ነበር። ነገር ግን ያጠለቀችውን ታኮ ጫማ እንዳደረገች በታደነችበት ምሽት ይህ ልምድ ተበጠሰ። ከዚህ በኋላ ተፈጥሯዊ የሆነው ምን እንደሆነ በብልሃት ግንዛቤ አገኘችበት። ያለችበት የመረብ ድር እንዴት እንደሆነ አወቀች።

ፍቅረኛዋ በመጀመሪያ ባደረገው ጉዞ ወቅት ስሜቷን በጥንቃቄ በመደበቅ አባቷን ዋሽታው ነበር። ይህን በማድረጓ አዝናለች። ለወላጆችዋ የነበራት የአክብሮት ስሜትም በምንም ዓይነት አልቀነሰም ነበር። የሆነ ሆኖ፣ በአሁኑ ሰዓት ግን ሁሉም ነገር ተለውጧል። አባቷ፣ በሚያስነውር ሁኔታ ስላሣደጋት ከዚህ በኋላ ጠንካራ የማመፅ አዝማሚያ ታሰባት። ምንም ዓይነት አግባብነት ያለው የጨዋታ አስተሣሰብ ስልቷን ሊያውክባት አይችልም።



ከእንግዲህ በኋላ ዋጋ ቢስ በሆነ መሣሪያም እንኳ ቢሆን ራስዋን ትከላከላለች። እንዲያውም አዲስና ይብልጥ ሃያል የሆኑ መከላከያዎችንም ለማግኘት ጥረት ታደርጋለች።

ከአባቷ ጥሪ እስኪደርሳት ጠበቀች።

ፖንሴ ከሄደ ከሁለት ቀናት በኋላ አባቷ ወደ ቢሮው ጠራት። ቆንሲሉ፣ በሴት ልጁ ላይ አንዳችም ጥርጣሬ የለውም። ራሱን እጅግ የሚወድድ ሰው ስለነበረ፣ በዙሪያው ስላሉት ሰዎች እምብዛም ፍቅር አልነበረውም። የጥላቻ ባህርይም አልነበረውም። በርግጥም በዙሪያው ስላሉት ሰዎች በነፃነት ለማሰብ ችሎታውም አልነበረውም። ሙሴ ዴ ማይሴ፣ ወጣቷን ልጁን፣ ፀሐፊው በማድባት እንዲጠጋት ትዕዛዝ አልሰጠም። ነገር ግን፣ የሙሴ ማቼ በቆንሲሉ ስሜት ላይ ተፅዕኖ ማሣደር መቻልና የፖንሴ የብልግና የጋብቻ ጥያቄ፣ ለሴት ልጁ አንዳች ነገር እንዲያውቅና በጥበቃ ውስጥ እንድትሆን ገፋፋው።

«ለመሆኑ ሰር ፖንሴ ስለሚባለው መድሃኒት ቀማሚ ያስተዋልሽው ነገር ነበረሽ?» ሲል የጥላቻ ምልክት ሣያሣይ ጠየቃት። ሴት ልጁን ያነጋገረበት የማይለዋወጠው ጨዋነቱ፣ እንደሚያፈቅራት ራሱን አሣመነው።

«በርግጥ፣ አዎን አባባ፤ አንተው ነበርክ እኮ ያስተዋወቅኸኝ» አለችው ምንም የተለየ ስሜት በማይታይበት ሁኔታ

በአዳኙ የመጀመሪያ ርምጃ፣ ቆቋ በርግጋ እንድትበርር ማድረግን ካሰበ ተሳስቷል ስትል አሰበች።

«እንግዲህ አሁን ሄዷል። ከዚህ በኋላም ጨርሶ እንደማናየው ተስፋ አደርጋለሁ። ግን እንድትመልሺልኝ የምፈልገው ጥያቄ አለኝ። ምናልባት፣ ከቶም ወደዚህ አካባቢ የመመለስ ጥረት ቢያደርግ ልወስዳቸው የሚገቡኝ እርምጃዎች ይኖራሉ። ለመሆኑ ተገቢነት የሌለው አቀራረብ ቀርቦሽ ያውቅ ነበር?»

አሊስ፣ ጥቁር ሰማያዊ ቀሚሷ ላይ የነበረውን እጥፋት፣ የሆነ አስጠሊታ ነገር የምታስወግድበት ይመስል በጭኗ ላይ አስተካከለችው። ምናልባት፣ ከቶም ወደዚህ አካባቢ

የመመስስ ጥረት ቢያደረግ? ስትል አሰበች። አባቴ እንዳይመስስ ለማድረግ ይሞክራል። ነገ ግን ንጉሡ ቢሸልሙት፣ ጆን ባፕቲስት ይህን አባባልም እንዲሁ ያሸንፋል . . .

«ታቅማሚያለሽ?» አላት ቆንሲሉ

«ያለፈውን እያሰብኩ ነው። እውነቱን ነው፣ አባባ፣ እንዲህ ያለ ነገር ማለ አልችልም። ሰውዬውን ያየሁት ለጥቂት ጊዜያት ብቻ ነበር። እርሱም ቢሆን በነዚህ ጊዜያ ሁሉ በከፍተኛ ስነስርዓት ነበር ራሱን ሲመራ የነበረው።»

አያምነኝም፣ ስትል ለራስዋ አሰበች። ካጂ፣ ካጂ፣ ካጂ፣

«የሚያጠራጥር ቃል ድንገት አፈትልኮብሽ እንዳልተናገርሽ እርግጠኛ ነሽ። አንዳን ባሰኘ ግለሰብ፣ በትህትናሽ ላይ ፍንጭ ያገኘ መስሎት ሥርዐት ይጥስ ይሆናል»

«እኔን፣ አባባ?» አለች ሰማያዊ አይኖችዋን በልጥጣ

የዓይኖችዋ ብሌኖች በቋጥኝ መሃል ያለ ኩሬ ወይም ሐይቅ ያህል ሊሰፉ እንደሚችሉ በዚያም ባለው ኩል የመሰለ የጠራ ውሃ፣ ጠጣሩ ልቧ የምት ሃይሉን እንዲጨምር ማድረ እንደምትችል ራስዋን በሚገባ ታውቀዋለች።

አባቴም ምንም ካላወቀ፣ በአይኖቼ ውስጥ ከንፅህና በስተቀር ምንም አያይባቸውም፡ ማየት ከቻለ ደግሞ፣ የሚያየው ፖቤ ነው ስትል አሰበች።

ሙሴ ዴ ማይሌ፣ ተንጠራራና ወደ አሊስ ቀርቦ፣ አንድ ትንሽ እንሰሳን እንደሚያሻ አይነት እጆችዋን ይዞ ያሻሽ ጀመር።

«እርግጥ ነው፣ ጥያቄዎቼ በጣም ግርድፍ ናቸው። ነገር ግን ይህ ግለሰብ የተናገራቸው ነገሮች ስላሉና ምናልባት የሰሚ ሰሚ ትሰሚያለሽ ብዬ ስለምፈራ፣ በተቻለኝ መጠን ሁሉ ልከላከልሽ እሞክራለሁ።?» አላት።

«ምን ነገሮች፣ አባባ?» አለችው እጆችዋን ከእጆቹ እያላቀቀች



«ምንም አይደል። የሰካራም ንግግር ነበር። ሰውዬው እዚህ ማህበረሰብ ውስጥ እንደተጠራቀሙት ጆብደኞች ሁሉ ወሮበላ ነገር ነው። ማንንም እንዳታይ በተቻለኝ መጠን የምከላከለውም ለዚሁ ነው»

«አመሠግንሃለሁ፣ አባባ» በማለት የመጀመሪያውን ድንገተኛ ጥቃት መፈረካከሷን ርግጠኛ ሆንችና፣ ለመልሶ ማጥቃት ጊዜው የደረሰ መሆኑን አመነች። «ሳንተ ባለኝ ውሲታ፣ ክብሬ እስከዛሬ ድረስ አንዲትም ስጋት ተደርጕበት አያውቅም። የሚያሣዝነው . . . »

«እሺ?»

« . . . እዚህ ፍፁም ተሰላችቼ መኖሬ ነው»

«አውቃለሁ» አለ ሙሴ ዴ ማይሌ

ከአገጠንብዋ ሄድ አለና፣ እንደገና በተረከዙ ላይ እንደመሽከርከር ብሎ ወደ ልጁ ተመለሰ

«እስከአሁን ድረስ ዜናውን ለመናገር አላቀድኩም ነበረ። እንግዲያውስ ልናገረው። በበኩሌ አስፈላጊውን ዝግጅት ስላደረግሁ በአጭር ጊዜ ውስጥ፣ አዎን፣ በአጭር ጊዜ ውስጥ ከመሰላቸት ትገላገያለሽ»

«እንዴት፣ አባባ?»

«አደርሻለሁ»

አፍቃሪዎች ልብ የላቸውም። አባቷ፣ ወዲያውኑ ለጆን ባፕቲስት እንደሚድራት ሊነግራት እንደሆነ አሰበች።

«ዜናው አስቸጋሪ እንደሚሆንብሽ መረዳት እችላለሁ» አለ ቆንሲሉ። «ሆኖም ግን ይህን ለማከናወን አለመፍጠናችንን ግን ተገንዘቢው»

«ለማን እንዳሰብከኝ ማወቅ እችላለሁ?» ስትል አሊስ በትህትና ጠየቀች

«በቅርቡ ከምታገኚው ሰው ጋር ነው። ስውዬው፣ ሳንቼ ሲል ከፈረንሣይ ድረስ ተጉዟ ብዬ ሙሉ በሙሉ ባልናገርም፣ ግን እውነት ነው። ሰውዬው፣ ሲበዛ ከታላቅ ዘር የተወ ነው። የአጐታችን ልጅ ፖንቻርትሬይን ራሱ፣ ስለሰውዬው ስለተናገረ ይህ በጣም ጥሩ እው ነው»

አሊስ፣ በድጋሚ እጅ ነሣችና ተጨማሪ ጥያቄ ሳታቀርብ ቀረች። ይህ አባ እንዳስደነቀውና እፎይታም የሰጠው መሰለ። እምቢታ ይኖራል ብሎ በርግጥ አልፈራ ለዚህ፣ ለዚህ፣ ሥልጣኑ እጅግ ታላቅ ነው። ይሁን እንጂ፣ አንዳችም የማቋረጥ ካልተፈጠረ፣ ጥያቄዎችና የውስጣዊ ስሜት ሁኔታ ካልታወቀ፣ ውስብስብ ነገር ሳይኖር እንደማይቀር ማስጠንቀቂያ ነው። ማንም ሰው ቢሆን፣ የወጣት ልጃገረድ ልብ፣ መሀ ከሚገባው በላይ ረቂቅ ነው ብሎ ሁልጊዜም ሊገምት ይችላል። ሆኖም ግን፣ ማንም ሰው ልጁን በሚገባና በትክክል ካሣደገ፣ ይህ ሁሉ ቀላል ነው ሲል አሰበ። ሙሴ ዱ ማይሌ፣ እንክ በሌለው የቤተሰብ ሥርዓትና ስምምነት አሊስን በፍቅር አያት።

«አባባ፣ አሁን የተናገርከውን ሰው ለማየት ጓጉቻለሁ። ሆኖም፣ ላንተም ይህን ያህ ጠንክር ተደርጐ የተሰጠህን ሃሣብ፣ በዚሁ ሰው ውስጥ ጥሩነቱን አገኝዋለሁ ብዬ ለማሰብ ትን እጠራጠራለሁ።»

ሙሴ ዱ ማይሌ በፍቅር ፈገግ

«ይሁን እንጂ፣ ጋብቻዬ ነገውኑ ይፈፀማል ብዬ አላስብምና እስከዚያው ድረስ አንድ ነገ እንድትፈቅድልኝ እለምንሃለሁ»

«ንገረኝ» አላት ቆንሲሉ

«እንዲህ ነው። የካይሮ የአየር ጠባይ አያፈነኝ ነው። እሱቲ እንዴት እንደገረጣሁ ተመልከት። ሌላው ቀርቶ እጮኛ የሚሆነኝን ሰው ለመማረክ . . »

«ምን ማለትሽ ነው። ስመለከተሽ ሙሉ በሙሉ ታንፀባርቂያለሽ»



«አዎን፣ ፊቴን ተቀባብቼዋለኋ። ደግሞ ማንም ሰው ስለሰርጉ ያለውን ስጋት በየዕለቱ አይማረውም። በአሁኑ ጊዜ ጉንጮቼ በተፈጥሮ ይቀላሉ። ግን አባባ፣ እመነኝ ጊዜ እያጠፋሁ ነው»

«ካይሮ ውስጥ ገና ብዙ አመታት እንኖራለንና ልትለማመጂው ይገባሻል» አላት ሙሴ ዱ ማይሌ በማይጣስ የትዕዛዝ ቅላፄ። «እኛ የመረጥንልሽን ሰው ካገባሽ፣ ተከትለሽው ወደሌሎች ቦታዎች ልትሄጂ ትችያለሽ። ሰውዬው፣ በምስራቅ ሜዲቴራኒያን እንዲያገለግል የተወሰነ ዲፕሎማት ነውና፣ አንድ ቀን ከዚህ የባሰ ቦታ ራስሽን ልታገኚው እንደምትችይ ላስጠነቅቅሽ ይገባኛል። ለምሣሌ ደማስቆስ ወይም ባግዳድ፣ በሌጋሲዮኑ ውስጥ ብቻሽን ተዘግቶብሽ እንደምትቀመጪ ማሰብ ትችያለሽ? እነዚህ ከተሞች ምን እንደሚመስሉ በርግጥ ምንም ዕውቀቱ የለሽም! እዚህ እኮ ቢያንስ የአባይ ለስላሣ ነፋስ አለ»

«ትክክል ነው አባባ። የምፈልገውም በትክክል ያንን ነው። እዚህ ካይሮ ውስጥ ያለውን ማህበራዊ ህይወት ስለማልፈልገው አልወደውም። የምፈልገው ከተፈጥሮ ጋር ብቻ ንክኪ እንዲኖረኝ እና ንፁህ አየር እንዳገኝ ነው። አንተ አምስት ኪሎ ሜትር ያህል ርቀት ላይ የባላገር ቤት አለህ። እዚያ ከእናቴና ከጥቂት አገልጋዮች ጋር እንድሰነብት ፍቀድልኝ»

«ያ ቤት ለጤና ጥሩ አይደለም። በወንዙም ላይ መርዛም ቢምቢዎች ስላሉ ትታመሚያለሽ» አላት ቆንሲሉ ተናድዶ።

«በበጋው ጊዜ አምን። በክረምቱ ግን ጤናማ ቦታ ነው። ካንተ በፊት የነበረው ቆንሲል በየዓመቱ ሁለት ወሮችን እዚያ ያሣልፍ ነበር»

እንደ እውነቱ ከሆነ፣ በጣም ዋናው ነገር ስለጋብቻው ምንም ተቃውሞ አለማንሳቷ ነው ሲል፣ ቆንሲሉ ለራሱ ተናገረ። በዚህ ጉዳይ ላይ ውለታ ሊዋልላት ተገቢ ነው። እስከ አሁን ድረስ መልካም ፈቃድ ስለሚታይ፣ በዚህ ላይ ተቃውሞን የሚያነሣሣ ነገር አለመስራት ጥሩ ነው።

«እናትሽ ከካይሮ ወጥታ እንድትሄድ አልፈቅድም። ቆንስላውም፣ እርሷን ለረዥም ጊዜ ማጣት አይችልም»

ይህ ግራ የሚያጋባ ቢሆንም እውነተኛ ሃሣብ ነው።

«ቆንስላው» ብሎ ሲናገር ስለቆንሲሉ እያሰበ መሆኑ ግልፅ ነው።

«እንግዲያው ከአገልጋዮቼ ጋር ብቻ እሄዳለሁ» አለች አሊስ

«የትኞቹ አገልጋዮች? ያች ሁልጊዜም ከጉንሽ የማትለየውና መጥፎ ሪፖርት የሰማሁባት ልብስ አጣቢ ነች?»

የሙሴ ማቼ መራራ ሃሞት በርስዋም ላይ ተደፍቶባታል፤ ስትል አሊስ አሰበች።

«ለመሆኑ እስከዛሬ ምን ጥፋት ፈፀመች፣ አባባ?» አለች ትልልቆቹን ዓይኖችዋን በቆንሲሉ ፊት ላይ በዝግታ እንዲሽከረከሩ በማድረግ።

«ያም ሆነ ይህ» አለ ዓይኖችዋን እየሸሸ « ሁለት ሴቶች አብረው ብቻቸውን እዚያ መቆየት አይችሉም። ከቆንስላው ሁለት ዘበኞች ያስፈልጉሻል፤ ከመናፈሻው ራቅ ካለው ዳርቻ ላይ የጥበቃ አዛዡ ጥቂት ሚሊሺያዎችን እንዲመድብልኝ ጠይቀዋለሁ።

«ኦ! እንዲህ ከሆነ ፈቃድህን አግኝቻለሁ?»

«ለመልካም ባህሪሽ ስል ነው» አለ በሻካራ ድምፅ። «እናም እንደቀድመ ሁኔታ፣ እኔ እንድትመጪ ስጠራሽ ወዲያውኑ ለመመለስ ቃል ስትገቢ ነው። ምክንያቱም ስለማንነቱ የተናገርኩለት ሰው ብዙም አይቆይም»

አሊስ፣ በዚህ ቅድመ ሁኔታ ተስማማችና በጦርነት ድል እንዳደረገች ያህል ራሷን አሣምና ሄደች።

ሙሴ ዴ ማይሌ በገባው ቃል ኪዳን መሠረት ትዕዛዙን ሰጠ። ከዚያም፣ እርሱ ራሱ በውይይቱ የረካ ስለሆነ ቀሪውን የማለዳ ሰዓት ለሚያውቃቸው ሰዎች ሦስት ደብዳቤዎችን ሲፅፍ ቆየ። ከነዚህ አንዱ በፖንሴ ላይ የጥቃት በትሩን እንዲያሣርፍለት የመረጠው፣ ሚኒስትሩ ፖንቻርትሬይን ነው። ቆንሲሉ፣ ፖንሴን ሲገልፀው ሁካራም እንደሆነ፣ አንዳችም የእውነት ጠብታ የሌለባቸውን ታሪኮች እንደሚፈጥር፣ በምኞት የሚነዳና የባለጌነት ባህርይ ያለው ነው ይለዋል። ቆንሲሉ፣ ፖንሴ ወደ አቢሲኒያ መጓዙን በሚገልፀው ትረካውም ላይ፣ ትልቅ ጥርጣሬ አለው። እንዲያውም ይህ የማጋነንና የመዋሸት አባዜና ዝንባሌ ያለው ግለሰብ ምናልባት ከሲናር አልፎ እንዳልሄደም ሲል ሃሳቡን አስፍሯል። ሙሴ ዴ ማይሌ፣ ይደግፋኛልና ማሸነፊያም ይሆኑኛል ያላቸው የመከራከሪያ ነጥቦች ደካሞች ቢሆኑም፣ እግዚአብሔር ፈቃዱ ከሆነ በሚቀጥሉት ተጨማሪ ቀናት የሚደርሱት ሌሎች መረጃዎች ቢኖሩ እንደሚያክል ገልጿል።

የመጀመሪያው የመልዕክተኛ ቡድን ከሄደ በኋላ እንደ ሆነው ሁሉ፣ የካፑቺኖች አለቃ የሆኑት ኢማሙና ግዙፉ መነኩሴ ወንድም ፖስኳል፣ ቅሬታቸውን በቁጣ ሊገልፁ ወደ ቆንሲሉ መጡ። መነኩሴው አባ ፕላንቴይን፣ ከአቢሲኒያውያን ጋር ወደ ቬርሣይለስ መጓዛቸውን አውቀው ስለነበር «ፈረንሣይ፣ በተለየ ላሉት የስብከት ሥርዓት አራማጆች የምታሣየው አድልዎ» በማለት፣ በሚጠቅሱት ጉዳይ ላይ ተቃውሞአቸውን ያቀርባሉ። ለዚህ ቅሬታ ሙሴ ዶ ማይሌ ደስ በሚልና በወዳጃዊ መንፈስ ማንንም በተለይ እንደማይደግፍና እንዲያውም በሌላ ምክንያት ሳይሆን በወንድም ፖስኳል ወዳጅነት ሣቢያ የርሣቸውን የእምነት ሥርዓት ጥረት፣ አቅሙ በፈቀደው መጠን እንደሚደግፍ መለሰላቸው።

«ስለትም የደረሰው በጥሩ ሰዐት ነው። አሁን በቅርቡ ወደ አቢሲኒያ አንድ የጉዞ ዘመቻ ለማድረግ አቅደናል» አሉ ኢጣሊያዊው ካህን

«ሌላ ዘመቻ ልታደርጉ?»

«ለጊዜው ሲናር እንሰነብታለን። ከዚያም አልፎ የሄደ ሰው የለም» ካሉ በኋላ በአታላይ ፈገግታ «ሌላው ቀርቶ የርስዎ ተረጂና ተመፅዋችም ቢሆን አላለፈም»

«የኔ ተረጂና ተመፅዋች?»

«አዎን፣ ሲኞር ፖንሴ!»

ቆንሲሉ፣ ይህን ዜና ለመስማት የመጓጓት ስሜት አሣየ። ወንድም ፖስኳል የተናገሩትን እንዲደግሙለትም ጠየቃቸው።

እጅግ በሚታመኑትና፣ ሲናር ከሚኖሩት ወንድሞች በደረሣቸው መረጃ መሠረት፣ ፖንሴ፣ ከሲናር፣ ከሸሸ በኋላ አንድ ሃምሣ ኪሎ ሜትር ያህል ርቀት ድረስ ከወሰኑ አልፎ እንደተጓዘና በአንድ የአቢሲኒያውያን መንደር ውስጥ በቀረጥ ኬላ ላይ ሲያገለግል እንደቆየ፣ ከዚያም አልፎ መጓዝ እንዳልተፈቀደለት፣ በዚያው መንደር ውስጥ ብዙ ወራት ሲጠብቅ እንደከረመ፣ በአገሩ ባህል መሠረት በቀላሉ ሲያደርገው የሚችለውን፣ እንዲት የአካባቢውን ተወላጅ ሴት አግብቶ እንደነበረና ጨርሶ ስላላገኘው ንጉሥ ነገስት ብዙ ታሪኮችን ሰብስቦ እንደተመለሰ በማረጋገጥ ቄሱ ተናገሩ።

በዚህ ንግግር ቆንሲሉ ከመጠን በላይ ተደሰተ። እንዲያውም ይህን ሁሉ ከሰሙ በኋላ ለምን ፈጥነው መጥተው እንዳልነገሩት ካፑቺኑን ጠየቃቸው። እርሣቸውም በበኩላቸው፣ ፈረንሣውያን፣ አንድ አርመናዊ የቀድሞ የወጥ ቤት ሠራተኛ የነበረን ሰው፣ እንደ አምባሣደር አድርገው ተቀብለው ራሣቸውን ሲያዋርዱ፣ በዚህ ጉዳይ ላይ እርሣቸው ጣልቃ የሚገቡበት ሰበብ ስለሌላቸው እንደሆነ በሽሙጥ ተናገሩ። ይሁን እንጂ ዝርዝር ታሪኩን ወደ ሮም እንደላኩና ሁሉም ካፑቺኖች ሌላው ቀርቶ ፖሪስ የሚገኙትም ጭምር እውነቱን እንደሚያውቁ አብራሩ።

«የሚነግሩኝ ሁሉ ታላቅ ጉዳይ ነው» አለ ቆንሲሉ። «ሲናር ከሚገኙት አባቶች ሪፖሬት ማግኘት ይችላሉ? ሪፖርቱስ በጽሁፍ ነው?»

«ሲናር ከሚገኙት የመነኮሣት አለቃ የተፃፈ ረዥም ደብዳቤ በገዳሙ ውስጥ አለኝ»

«የደብዳቤውን ቅጅ እንዲሰጡኝ በማክበር እጠይቅዎታለሁ። ሁሉንም ነገር እንዲቋረጥ ለማድረግ አሁንም በቂ ጊዜ አለ»

ካፑቺኑ ምንም ሣይናገሩ ረዘም ላለ ጊዜ ጠበቁ።

ቆንሲሉ ወጥመዱ ውስጥ ከገባ በኋላ፣ ቁጣውንና ብስጭቱን በወረቀት ላይ ማስፈር ጀመረ።

«የተስማማን ስለሆነ ፈቃዴን ሰጥቼዎታለሁ። ያቀዱትን ተልዕኮ ለማገዝ የምችለውን ሁሉ አደርጋለሁ»



«ቃል ነው?»

«ቃል ነው»

«ጥሩ። ደብዳቤው ዛሬ ማታ በእጅዎ ውስጥ ይገባል» አሉ፣ የመጡበት ጉዳይ የተሣካላቸው አባ ፖስኳል። «በሚቀጥሉት ጥቂት ቀናት ውስጥ በእቅዳችን ላይ እንዴት ሊረዱን እንደሚችሉ ላነጋግርዎ እመጣለሁ»

ይህን ከተናገሩ በኋላ፣ ኢጣሊያዊው ካህን፣ ሳይታሰብ በድንገት እንደመጡ ሁሉ ወዲያውኑ ቆንስላውን ለቀው ሄዱ ። ሙሴ ዴ ማይሌ፣ የካህኑን አጠቃላይ ግልፅነት፣ ጨዋ መስለው በምስጢርና በድብቅ ከሚሠሩት ከአግኖጢዮሣውያን ጋር በማነፃፀር በጣም አደነቃቸው።

***

ጊዛ ውስጥ ኦና ሆኖ የከረመውን ቤት ለማደስና ለማዘጋጀት፣ አገልጋዮች የጥቂት ሣምንት ጊዜ ወሰደባቸው። መስኮቶቹን ሁሉ ከፍተው ንፁህ አየር በየማረፊያው እንዲገባ አደረጉ። ከዚያም በመቀጠል ሁሉንም ክፍሎች ከትኩሣት ሕመም ነፃ ለማድረግ በመድሃኒት አጠኑ። በመጨረሻም በሁለት ሠረገላዎች ጭነው ያመጧቸውን ዝርግና ጉድጓዳ ሳህኖች፣ኩባያዎችና ሌሎችም ከሸክላ የተሠሩ የቤት ቁሳቁሶችን በክፍሎቹ ውስጥሞሏቸው። በአልጋዎቹም ላይ አዳዲስ አንሶላዎችን አንጥፈው አስጌጧቸው።

ቤቱ ተስተካክሎ ካበቃ ከአንድ ቀን በኋላ፣ አሊስ ከፍራንቾይዝ ጋር መጣች። እንደተገመተው፣ የአሊስ እናት ካይሮ ለመሰንበት ወሰነች። የተከተሏቸው ሦስት አገልጋዮች፣ ሙሉ በሙሉ ሁለቱን ሴቶች ለማገልገል የሚታመንባቸው ናቸው። በርግጥ፣ ሁለቱን ሴቶች ተከትለው ለመምጣት መመረጥ የሚችሉ ብዙ ነበሩ። ምክንያቱም በአጠቃላይ የቤት አገልጋዮች በቆንሲሉ ንፉግነትና ለበታቾቹ ባለው ጥላቻ ላይ አቋም ወስደው ነበር። የሚሊሺያዎች አዛዥ የመደባቸውን ጥቂት ቱርካውያን ጠባቂዎችን በተመለከተ የተሰጣቸው መመሪያ፣ ከመኖሪያ ቤቱ ራቅ ባለ ሥፍራ ላይ እንዲሰፍሩና ንብረቱን ብቻ ከውጭ ሆነው እንዲጠብቁ የሚል ነበር።

ማዳሞዜል ዴ ማይሌ፣ በሠረገላ ተሣፍራ ከቀትር በኋላ በዘጠኝ ሰዓት ላይ ደረሰች። የለበሰችው ተራ ሰማያዊ ጥብቅ የሚያደርግ ልብስና ጥቁር ከፋይ ቀሚስ ሲሆን፣ ጥቅል ፀጉርዋንም በአንድ ነጠላ ሪበን ሽብ አድርጋዋለች። ስለቤቱ ገለፃ ሲደረግ ከመስማቷ በስተቀር በአይኗ አይታው አታውቅም። አሁን ስትመለከተው በውሃ ሙላት ጊዜ ዙሪያውን በውሃ በሚከበብ ከፍ ያለ ቦታ ላይ የተሠራ መሰላት። ሕንፃው ራሱ የቱርካውያን ቤተመንግስት የነበረ ሲሆን፣ በእንጨት ቅስቶች በሹል ቅርፅ የተሠራ ነው። መስኮቶችም የእንጨት ርብራብ መከላከያ ያላቸው ክፍት የጥድ ጣውላዎች ናቸው። ባለስምንት ማዕዘን ረዥም ጉልላት ሆኖ፣ የኦቶማኖችን የራስ ቁር የመሰለ ጣሪያ አለው። በአሁኑ ጊዜ የማይታይበት በጣሪያው አናት ላይ የነበረው የእስልምና ግማሽ ጨረቃ ነው። ይህ ምልክት በአንድ ዘመን ነበረ። በኋላ ግን ገዥው ፓሻ ቤቱን ለፈረንሣይ ቆንሲል ከአንድ ሃምሳ ዓመት በፊት ሲሰጥ፣ ይህን ምልክት አስነሣው።

ሕንፃው፣ የአባይ የተለመደ ሙላት ከማይደርስበት ከፍ ብሎ በጉብታ ላይ የተሠራ በመሆኑ፣ የወንዙን ግራና ቀኝ ዳርቻዎች ቁልቁል ወለል አድርጐ ያሣያል። በሦስቱም ማዕዘንና ቤቱን ከብቦ የሚታየው የደለል አፈር ሜዳ፣ ለም መሆኑ ባያጠራጥርም ቆንሲሉ ስራ ላይ አላዋለውም። በዚህ የተነሣ ሰፊ የሣር ምድር ግቢ በመሆኑ፣ ቤቱ፣ ባልተቆራረጠና እጅግ ሠፊ የሣር መስክ ተከብቧል። የቤቱ አራተኛው ጐኑ ወደ ወንዙ የሚያቆለቁል ሲሆን በትላልቅ ዛፎች ተክል የተሸፈነ ነው። የነዚህ ዛፎች ቅርንጫፎቻቸው የተጠጋጉና የተቀራረቡ በመሆናቸው ሌሎች ተክሎች ከስራቸው እንዳይበቅሉ ያግዳሉ። ከዚህ ይልቅ የደረቁ ቅጠሎች እንደ ስጋጃ በጥላው ውስጥ ተነጥፈው እስከ ወንዙ ጠርዝ ድረስ እስካሉት የቁጢማ ተክሎች ተዘርግተዋል። በአባይ ላይ የሚንሳፈፉት ነጫጮቹ ትናንሽ የጠረፍ ጀልባዎች፣ ከቆንሲሉ ንብረት አካባቢ እንዳይቀርቡ የሚከለክለው ቃል፣ ለጀልባ ቀዛፊዎች ሁሉ የተላለፈ ይመስል በርቀት ናቸው። አንድ የእንጨት የመዝናኛና የመሸጋገሪያ ድልድይ፣ ያረጀና ጥቅም የሌለው ተንሣፋፊ ጀልባ ወዳለበት ሃያ ጫማ ያህል ወደ ውሃው መሃል ተዘርግቷል።

አሊስ፣ ቤቱን ተዘዋውራ አየች። በእንግዳ መቀበያ የእንጨት በረንዳ ላይ ቆም ብላ፣ የወንዙን መረር የሚል ነፋስ ወደ ውስጥ በሃይል ሣበች። ይሁንና በዚህ ደስታ ውስጥ ራሷን ብዙም አላቆየችውም።

ፍራንቸይዝን «ነይ» አለቻት። «እቅዳችንን ለመጀመር ሴኮንድ ማባከን የለብንም»



# 3

የህዳር ወር ቀዝቃዛ ነበር። እጆቹን በተቻለው መጠን በፈረሱቹ ጫንቃ ላይ በማሸሸት ያሟሟቀው ጆን ባፕቲስት፣ ኬላው ላይ ሲደርስ በረዶ ሆኖ ነበር። በራሱ ፍጥነት እየጋለበ ሊሄድና በያንዳንዱ ታላቅ ከተማ መግቢያ ላይ ለመገናኘት ከጉዞ ጓደኞቹ ጋር ተስማምተው ነበር። በመጨረሻም፣ ነፃነትና በራሱ የመመራት ስሜት አድሮበት መንዝ ጀመረ። ወደ መንደሮች እየገባ ከባላገሮች ጋር ይነጋገራል። በየመስኩም፣ ሥራ ፈትተው ከተቀመጡ አዛውንቶች የሚነገረውን ይሰማል። ሊዮንስ ከተማ ውስጥ፣ አንድ የፖስታ ቤት ሰራተኛ መለዮና ቀይ ላባ ያለበት ሰፊ ባርኔጣ ገዛ። እግረ መንገዱንም የእስፖኝ ንጉስ መሞታቸውን ተረዳ።

ከሶስት ቀናት ጉዞ በኋላ፣ ባለሰረገላዎችና ባለፈረሶች፣ የጀስዊቶች መኖሪያ ቤት ወደሚገኝበት ፎንቴይን ብሉ፣ በውድቀት ሌሊት ደረሰ። ሃይለኛ ነፋስ የሠረገላውን የነሃስ ፋኖስ መብራት በተደጋጋሚ ያጠፋው ነበር። በመንገዱ ግራና ቀኝ በመደዳ የተተከሉት ጥቋቁር ዛፎችም ወደፊትና ወደ ኋላ በሃይል ይወዛወዛሉ። ጆን ባፕቲስት፣ የሚወርደውን ቀዝቃዛ ዝናብ ለመጉረስ በሚል አፉን ሲከፍት፣ ከት ብሎ ሣቀ። የተለየ በሆነው በሁናር አውራጃ ምድር ለአመታት በመቆየቱ፣ እዚህ ያለውን የአየር ጠባይ መዘንጋቱን ተገነዘበ። በሚቀጥለው ቀን የቀረጥ ተቀባዮችን የኬላ ዳስ በደቡባዊ መግቢያ በር አልፈው ፓሪስ ደረሱ። ከዚያም ወደ ዮብሬ አቀኑ። በጉናቸው በኩል ዝናቡ እንደገና ከመጣሉ በፊት መጠለያ ወዳለበት ለመድረስ ሲገሰግሱ ጥቋቁር ጥላዎችም እንዲሁ ይጣደፋሉ።

የሉዊስ ሌ ግራንዴ ትምህርት ቤት በሆነው የተለየ ሕንፃ ውስጥ ሠፈሩ። በአቅራቢያው በሚገኘው የአውቴኡል መንደር ቤተሰብ ያለው ፍሌሃው፣ በመጀመሪያው ዕለት ተለያቸው።

ዲፕሎማቱ፣ ያሳደዱት ያህል በጋሪው ተጣድፎ ከሄደ በኋላ፣ «ለፖንቻርትሬይን ራፖርቱን ሊሰጥ ነው» አሉ አባ ፕላንቴይን ክፋት በተሞላበት አነጋገር።

በዚያን ጊዜ ይነገር የነበረው ታላቅ ዜና፣ የስፔይን ንጉሥ ያደረጉትን የኑዛዜ ቃል ሉዊስ 14ኛ የመቀበላቸው ጉዳይ ነበር። ከአብራካቸው የተገኘ ልጅ የሌላቸው የእስፔይኑ ነጋሲ፣ ዘውዳቸውን ለሉዊስ የልጅ ልጅ፣ ለአንጁ ዱክ ተናዘውለታል። በዚህም የተነሣ ታዋቂው የንጉሡ የልጅ ልጅ፣ የማድሪድን ዙፋን ሊይዝ ስለሆነ፣ የፈረንሣይ ንጉሥ ሁለቱንም ግዛት

ዘውዶች ሲገዙና፣ በአውሮፖና በመላውም ዓለም እጅግ ሃያሉ ሰው ሲሆኑ ነው። ስለዚህም ጦርነት የማይቀር ነገር ነው። ጄስዊቶቹ ይህን ታላቅ ጉዳይ በደስታ ተወያዩበት። በክርስቲያኑ ዓለም ውስጥ እጅግ ታላቁ የሆነው ንጉሥ፣ ከዚህ በፊት ሲያከናውነው ከነበረው ባላነሰ፣ የካቶሊክ ተልዕኮውን፣ በተለይም በምስራቁ ዓለምና በአቢሲኒያም ውስጥ የጠባቂነት ሚናውን በግድ ይወጣዋል ሲሉ አባ ፕላንቴይን ያስባሉ። ምንም አዲስ ነገር ባይፈፀምም፣ አባ ፕላንቴይን በሕይወታቸው ውስጥ እጅግ ታላቅ ከሚሉት ተግባር ጋር ይህን ሃሣብ አቆራኙት። ይህ ታላቅ ተግባር ደግሞ፣ የተዳከመውን የቅዱስ ሮማና የሃዋርያትን ቤተክርስቲያን እርሳቸው ወደማያውቋትና ከርሣቸውም ምንም ወዳልጠየቀችው አገር ማምጣት ነበር።

ጆን ባፕቲስት፣ ከዚህ ቀደም ጨርሶ ፖሪስ መጥቶ አያውቅም። እዚያ በገባ በመጀመሪያው ምሽት ወደ ሲየን ወረደ። ፈረሱንም በመርከቦች ማቆሚያ ዳር፣ በተቀዛፊ ጀልባዎችና በማጠቢያ ቤቶች መካከል ውሃ እንዲጠጣ አደረገው። በመጀመሪያ ላይ አዲስ የሕንፃ ግንባታ በሚከናወንበት ሰፊ ሜዳ ላይ ቆየ። ከዚያም ኢንቫሊድን አቋርጦ፣ በመርከብ ማቆሚያው አድርጐ፣ ራቅ ብሎ እስካለው እስከ ፖንትኑዩፍ ተጓዘ። ከዚያም በሰሜናዊው ሰፊ የከተማው ጉዳና ረዥም ዙሪያ ክብ መንገድ ላይ እስከ ባስቲል ድረስ ተጓዘ። እርሱ አገሩን ለቅቆ ከሄደ ወዲህ! ሰዎች በልብስ ፋሽናቸው ላይ በጣም ትልቅ ለውጥ እንዳደረጉም ተገነዘበ። ይህን በተመለከተ፣ ካይሮ የሚገኙት ፈረንሣውያን በጣም ኋላ ቀር ሆነዋል። የለበሰውን ምርጥ ሙሉ ልብስ ከዋና ከተማው ነዋሪዎች አለባበስ ጋር ሲያነፃፅረው፣ የሚያሣፍር ሆነበት። በሚቀጥለው ቀን ወደ ሴንት ጃክዴስ ሄዶ የብር ጉንጉን ጌጥ ያለበት አረንጓዴ ከፋይ ኮት፣ የሃር ሰደርያ፣ ጥቁር በላሴና የእግር ሹራቦችን ገዛ። ይህን የአዘቦት የሥራ ልብስ ለብሶ፣ የከተማዋን እምብርት ዘልቆ ለመግባት ወኔ ተሰማው። ይህን ለብሶ በከተማዋ መሃል ባሉ ጠባብ መንገዶች ላይ የሚንቀሳቀስ ሰው፣ ሌሎች ተንገሮችና ባለሱቆች የሚናገሩትን እርቲ ቡርቲ አስተያየቶች ሁሉ ሊሰማ ይችላል። አቋሙ ደስ የሚል ነው። ጐራዴ ታጥቋል። አይኖቹም የሚያባብሉ ናቸው። አንድም ሰው አንዳችም ማጉረምረም አያደርግበትም።

በከተማው ውስጥ በራሱ ወጭ ማረፊያ ቦታ ለማግኘት ቁርጠኛ ውሣኔ አደረገ። ጄስዊቶቹ፣ እዚህ ድረስ አምጥተውት በቤተመንግስት ሰብሰባ ላይ እንዲገኝም ሁኔታዎችን እያመቻቹ ነው። ይህ ደግሞ በቂ ነው። ከዚህ ባሻገር የነርሱ ሽክምና ዕዳ መሆን አልፈለገም። ይሁን እንጂ ራሱን ለመቻል ሃብታም አልነበረም። የዋና ከተማው ኑሮም ከፍተኛና ውድ ነው።



የያዝኩትን የወርቅ ዱቄት ለንጉሡ በገፀበረከትነት ከማቀርብላቸው ይልቅ፣ የራሴን ነፃነት የማውጅበት ይሆነኛል ሲል ጆን ባፕቲስት አሰበ። ንጉሡ ነገስቱም ይህችን ታህል ትንሽ ነገር በስጦታ ስትቀርብላቸው እንደስድብ ሊቆጥሯት ይችላሉ።

ወርቁንም ወደ አንድ በገንዘብ ሊለውጥለት ወደሚችል ሰው ዘንድ አመጣው። ምንም እንኳ ከረዥም ርቀት ቦታ የመጣ ወርቅ ቢሆንም በዚያን ጊዜ ሊለወጥ ከሚችለው በላይ አያወጣም። ባለገንዘቡም በጥርጣሬ ካየውና ከረዥም ዝምታ በኋላ ቀለል ያለ የኢኩስ ክረጢት ሰጠው። ይህ መጠን ከምንም የተሻለ ነው። ለጥሩ ማረፊያም በቂ ነው ሲል ጆን ባፕቲስት አሰበ።

የማረፊያ ክፍል ለማግኘት ባደረገው እንቅስቃሴ፣ በመጀመሪያ በኢል ዴ ላ ሲቲ ዙሪያና ቀጥሎም በሆቴል ዴ ቪሌ አካባቢ ተዟዟረ። በመጨረሻም የሚፈልገውና የሚስማማውን በቅዱስ ኢዩስታች ቤተክርስቲያን አጠገብ አገኘ። ዓይኖቹን የማረከው የመጠጥ ቤት ምልክት ሰርሱ ሁኔታ ፍፁም የሚስማማ ነበር። ምልክቱም በአንድ የብረት ንጣፍ ላይ ከወገቡ በታች ግልድም ታጥቆ ጦር የያዘ የግዙፍ አፍሪካዊ ቅርፅ የተሣለበት ነበር። ጆን ባፕቲስት፣ ወደዚህ ሉ ቢዩ ኖይር ተብሎ ወደሚታወቀው ቤት ገባ። አስተናጋጁ ባለቤት፣ ረዥም፣ ጕንጮቹ ወደ ውስጥ የተጣበቁበትና እመዳም ፊት ያለው ሲሆን፣ ከራሱ ይልቅ ለደንበኞቹ የተሻለ ጥንቃቄ የሚያደርግላቸው ይመስላል። ወደ መንገዱ አቅጣጫ ካለው ክፍል ውስጥ ሞቅ ያለ እውነተኛ የሣቅ ድምፅ ይሰማል።

«መጋዘኑን የገዛሁት ከአንድ ልብስ አቅላሚ ላይ ነበር» ሲል ሰውዬው ሞቅ ባለ ፈገግታ ይናገራል፡ «እርሱ የፈለገው ያንን ያልተለመደ ምልክት ሲሆን እኔም ልጠብቅለት ወሰንኩ»

ጆን ባፕቲስት ወደ ውስጥ ዘልቆ አንድ የተለቀቀ ክፍል ያገኝ እንደሆነና ዋጋውም ምን ያህል እንደሚሆን ጠየቀ። ሊገኝ የቻለው ከጉረኖ የማይሻል ትንሽ ክፍል ነው። ለዚያውም ኪራዩ ውድ ነው። ይሁንና የራሱ የሆነ የእሣት ማንደጃ ቦታ ያለው ሲሆን፣ ባለቤቱም፣ እንግዳው የሚፈልገውን ያህል ማገዶ ሊያቀርብለት እንደሚችል አረጋገጠለት። ወጣቱ ሰው ከምሽት እስከ ንጋት ድረስ በቁር ሲቆራመድ የቆየ በመሆኑ፣ የትኩሳት ስሜቱም እየዘቀዘቀ ስለነበረ፣ የተነገረውን ዋጋ ተስማምቶ የአራት ቀን ሂሣብ በቅድሚያ ከፈለ። ባለሁለት ክፍል የሆነውን ሻንጣውንና የመድሃኒት ሳጥኑን ለመውሰድ ወደ ጄስዊቶች መኖሪያ ተመልሶ ሄደ። እዚያም፣ ከነርሱ ዘንድ እንደሚወጣ፣ ነገር ግን ፈረሱን ብቻ እንዲጠብቁለት ነገራቸው። አባ

ፕላንቴይን፣ እንዳይወጣና እንዳይሄድ አጅግ አጥብቀው ሞከሩ። ፖንሴ ግን በየዕለቱ ማለዳ በትምህርት ቤቱ አካባቢ በመቆየት ከንጉሡ ጋር ለሚኖራቸው ስብሰባ ይጠሩ እንደሆነ ወሬ እያዳመጠ እንደሚቆይ ቃል በመግባት ጥያቄአቸውን ሳይቀበለው ቀረ። ከዚያም ወደ ሌ ብዩ ኖይሬ በመመለስ እስኪጠግብ ድረስ በቂ እራት በልቶ ውስጥ አካሉን በጣም በሚደነቀው የባርጋንዲ ወይን አሞቀው። የማወቅ ጉጉት ያለው የሆቴሉ ባለቤት፣ ጨዋታ ፈልጐ ቀረበው። ጆን ባፕቲስትም፣ ከካይሮ እንደመጣና የፈውስ ሃይል ባላቸው እፅዋት እየተጠቀመ ሰዎችን የማዳን ሥራ እንደሚሠራ ነገረው።

«ሐኪም ነሃ፣ እንግዲያው!» አለ የመጠጥ ቤቱ ባለቤት በአክብሮት ጉንበስ እያለ።

«ከሞላ ጐደል።» አለ ፖንሴ፣ ሕጋዊ የምስክር ወረቀት ጥያቄን ጉዳይ ላለመቀስቀስ አስቦ

«ኦ! ጌታዬ ሙሉ በሙሉ እንጂ፣ ያለ ስህተት ሙሉ በሙሉ። ከሕክምና ትምህርት ቤት የሚወጡትን እነዚያን ጨካኞችማ አውቃቸዋለሁ። ሊገድሉን እንኳ ባለ በሌሰን ላይ ይደራደሩናል። ወዳጄ፣ እኔ በዕፅዋት ተአምራዊ ሃይል በተለይም ከምስራቅ በሚመጡት ላይ እምነት አለኝ»

ጆን ባፕቲስት ነገሩ እንዳይሰፋ ወይም ሰውዬውም ወሬውን እንዳይቀጥል ለማድረግ ተጠንቅቆ፣ ጨዋታውን አልቀጠለም። ወደ ፎቁ እየወጣ ሳለ፣ የሆቴል ቤቱ ባለቤት ሙያውን ከአንዱ ጠረጴዛ ወደ ሌላው እያደነቀ ሲነዛ ሰማው። የአክብሮት አይኖችም ዱካውን ተከተሉት።

ይህ ሥራ ደንበኞችን ይስባል ብለን ተስፋ እናድርግ፣ ሲል አሰበ። እዚህ ከተማ በሚታየው የገንዘብ አወጣጥ፣ የያዝኩት ክረጢት ሙሉ የወርቅ ብናኝ በአጭር ጊዜ ውስጥ ቀልጦ ይጠፋል። ለዚያውስ እዚህ ምን ያህል እንደምንቆይ ማን ያውቃል? ሲል አሰበ።

ይህ ሁሉ ሲሆን ጄስዊቶች እጆቻቸውን አጣጥፈው አልተቀመጡም። እስፔይን ውስጥ ያጋጠመው ታላቅ ጉዳይ ቤተመንግስቱን ግርግር ውስጥ ስለከተተው፣ የንጉሡን ስሜት ሙሉ በሙሉ ይዞባታል። ይሁን እንጂ ቀሣውስቱ፣ የኢትዮጵያን ጉዳይ በከፍተኛዎቹ መሪዎቻቸው በኩል የማሰማት ዕድል ለማግኘት ጊዜአቸውን ሁሉ በማሣወቅ ስራ ላይ እያዋሉት ነበር። በፈረንሣይ ውስጥ ለሚገኙት ለብዙዎቹ ታላላቅ ሰዎች የንስሃ አባቶች የሚሆኑት የእየሱስ ማህበረሰቦች ንጉሡንም ይጠቀልላሉ። በዚህም የተነሣ፣ በተረት የተለበጠው የአቢሲኒያ የተልዕኮ ቡድን የጀግንነት ጉዞና ዘመቻ ወሬ፣ በመቶዎች በሚቆጠሩ ታላላቅ ቤቶች ውስጥ



እንዲሰራጭ አደረጉ። ለነዚህ ታማኞች ብዙ የእራት ግብዣዎች በየታላላቁ ሰው ቤት ተዘጋጅቶላቸዋል። ፖንሴ ግን፣ የራሱን ታሪክ ከሁሉ በፊት ለንጉሡ ማሰማት አለብኝ በሚል አቋም የእራት ግብዣዎችን ሣይቀበል ቀረ። ይህን ጠባዩን፣ አባ ፕላንቴይን ደከም ባለ ወቀሣ ይነግሩታል። እንደ እውነቱ ከሆነ ግን፣ ቄሱ፣ ወደነዚህ ስመጥር ቤቶች ብቻቸውን በመሄዳቸው ታላቅ ክብር ይሰማቸው ነበር። በተመስጦ በሚያዳምጧቸው ሃብታሞች፣ ባለማዕረግ ሰዎችና በውብ ወይዛዝርት መሃል፣ በአጭሩ በሚያንፀባርቁ የሕብረተሰቡ አባላት መሃል መገኘታቸውን፣እንዲህ ባልተቋረጠ ሁኔታ ሲጋበዙ፣ ፈረስ ነጋዴዎች የነበሩት ቅድመ አያቶቻቸው ቢያዩዋቸው ኖሮ እጅግ ይኮሩ ነበር። ቀሣውስት በአጠቃላይ የሚደነቁበት ነገር ቢኖር፣ በተአምር ላይ ብዙ ማለት መቻላቸው ነው። ከፖንሴና ከአባ ዱ ብሬቬደንት የጉዞ ታሪክ ከሚያውቁት ትናንሽ የታሪክ ቃርሚያዎች፣ አባ ፕላንቴይን የሚያቁነጠንጥ ታሪክ ይሰሩበታል። በትረካቸው ጊዜ የሚዘልሏቸው ጉዳዮች የራሣቸው ሌላ ድንቅ ተአምር ይሆኑና በድል አድራጊነት ሃሣብ ሲቋጥ፣ሐቀኛ እማንያን ከሆኑ መላው መኳንንት ጋር ያቆራኙታል። ታሪኩ፣ ደግመውና ተደጋግመው በመሣፍንቱ ዙሪያ በመነገራቸው የተአምርነትን ክብር ሲይዙ፣ ፖንሴ ከዕይታ ውጭ ሆኖ ቆየ።

ይህ ሁሉ ሲከናወን ጆን ባፕቲስት፣ ሌ ቢዩ ኖይሬ ሆቴል ውስጥ አብረውት እራት ከሚበሉ ሰዎች ጋር እግሮቹን በእሣት ማንደጃው አጠገብ አድርጐ ካርታ ይጫወታል። ይህም ካልሆነ፣ በቱ ኢሌሪየስ መናፈሻ ውስጥ ለመንሸራሸር ፀሐይዋ ብልጭ ስትልለት ይወጣል። ከዚያም መስኮቱ ላይ ያለውንና የዘራውን የቆንጥር ፍሬ ውሃ ለማጠጣት ይመለሳል። ወደዚህ ሆቴል የገባ ዕለት የመጀመሪያው ታካሚ ህመምተኛ መጣለት። ሕመምተኛው፣ የአንዲት ምግብ አሣላፊ ሴት ልጅ ሲሆን፣ ያመጣውም የሆቴሉ ባለቤት ሙሴ ራኦል ራሱ ነበር። ሕፃኑ ከባድ የጉረሮ ምርቀዛ አለበት። ጆን ባፕቲስት፣ ትንሽ መድሃኒት ሰጥቶት ካከመው በኋላ ክፍያ ሳይቀበል ቀረ። ከሁለት ቀን በኋላ፣ ሕመምተኛው ህፃን፣ ተፈጥሮ በራስዋ መስመር ያለድጋፍ እንደምታደርገው ሁሉ፣ በእግሮቹ ቆመ። ሐኪሙ፣ ይህን ጉዳይ ለራሱ ውለታ እንዲሆንለት ለማድረግ ቻለ። ዝናው ወዲያውኑ ናኘና ከዚህ ሥራ ጥቂት ትርፍ ማግኘት ጀመረ።

በዚህ ዓይነት በዋና ከተማው ውስጥ በቆየበት በመጀመሪያው ሣምንት ውስጥ፣ ጆን ባፕቲስት ሁለት በጣም የተራራቁ ዝናዎችን አተረፈ። በማያውቁት መሣፍንትና መኳንንት አካባቢ አምባሣደር ነው ተብሎ ተመሰገነ። ሁለተኛም፣ ጊዜውን በሚያሣልፍበት የድሆች

መኖሪያ አካባቢ ፈዋሽ ተባለ። እንደ እውነቱ ከሆነ ሦስተኛም የሚገባው ዝና ነበረው። ይሀኛውን ግን እርሱም አያውቀውም ነበር። ቢያውቀው ኖሮ ግን ቅር ይሰኝበት ነበር። የቤተመንግስቱ ስብሰባ በመዘግየቱ የተነሣ በሙሴ ዴ ማይሴና በካፑቺኖዎች የተፃፈው ደብዳቤ፣ የመንገደኞችን እግር ተከትሎ በመድረሱ የነርሱን ዝና መናድ ጀመረ። ሚኒስትሩ ዴ ፖንቻርትሬይን፣ እዚህን ሰዎች በተመለከተ ጠንካራ ማስጠንቀቂያ ስለደረሰውና ግንኙነታቸውን ከጀስዊቶች ይልቅ ለሮማ በሆኑ ካህናት፣ እስካሁን የተከናወነው የኤምባሲ ጉዳይ የፈጠራ ሥራ እንደሆነና ፖንሴም አስመሣይ አጭበርባሪ ነው የሚል ወሬ አናፈሰ።

ምንም እንኳ እስከአሁን በጣም ጠንካራ መሠረት ባይዝም፣ ይህ አስከፊ እንቅስቃሴ መቀጨት ይገባዋል ሲሉ አባ ፕላንቴይን አሰቡ። ከንጉሡ ጋር ሊኖር የሚችለው የስብሰባ ግንኙነት ለጥቂት ጊዜ ሊከናወን ባይችል፣ እስከዚያው ድረስ መጠበቁ ግን ጅልነት ይሆናል። ግርማዊ ንጉሥ ነገስት፣ የልጅ ልጃቸው ወደ እስፔይን እንዲጓዝ ዝግጅት እያደረጉ ሲሆን ምናልባትም ጥቂት መሠረታዊ የአገዛዝ ሐሣቦችንም እየመዘኑት ይሆናል። ስለዚህም አባ ፕላንቴይን በትምህርት ቤቱ አጠገብ ወደ ሚገኘው መኖሪያቸው ፖንሴን ጠሩት። ሐኪሙም፣ በአንድ ማለዳ ሁለት ህመምተኞች ትቶ ደረሰ። ጉንጮቹ በቅዝቃዜው የተነሣ ገርጥተዋል።

«ውድ ወዳጄ» አሉ አባ ፕላንቴይን ከአንገት በላይ በሆነ አነጋገር፣ «የሆኑ ቅናት ያንገበገባቸው ቡድኖች፣ አንተ ወደ አቢሲኒያ ያደረግኸው ጉዞሙሉ በሙሉ የፈጠራ ነው ብለው ለመናገር ወኔ አግኝተዋል። እኛ እንኳ በጥላቻ የተሞላውን ትችታቸውን በሃይማኖታዊ መስመራችን በሚገባ እናውቃቸዋለን። ይህን ስሁተታቸውን አሁኑኑና በማያጨቃጭቅ መልኩ ማጋለጥ ይኖርብናል። ስለሆነም መልካም ፈቃድህ ከሆነ እንግዲህ እዚህ ደርሰናልና ንጉሡ የሰጡህን ደብዳቤ ስጠኝ፣ በአስቸኳይ ሳስተረጉመውና የተረጋገጠ ሳስደርገው። ከዚያም በኋላ በጋዜጦች ላይ እንዲታተም በማድረግ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ የዓላማችን እውነተኛነት እንዲሰራጭ እናድርገው»

የፖሪስ ግርግርና ሁካታ፣ ጆን ባፕቲስትን ሁሉም እንዲምታታበት አድርጎታል። ለመገናኘት ወደተቃጠረበት ወደ ቅዱስ ዣኩይስ ሲያመራ በፍጥነት እየሰገሩ የሚያልፋትን ሰረገላዎች፣ ግራጫ የለበሱ የንጉሡ የክበር ዘበኞች ስኳድሮንና ተኳኩሰው የወጡ ወይዛዝርትን ፈዝዞ ሲመለከት፣ ከጀስዊቶች ጋር ያለውን ተልዕኮ፣ በተለይም ሊይዘው ይገባው የነበረውን ደብዳቤ ፊፅም ረስቶታል። በርግጥ ይህ ደብዳቤ የሚባለው ከአንድ ቁራጭ ወረቀት



የማይበልጥ፣ ለዚያውም እርሱ ራሱ የፃፈው ሆኖ በእሣት መቀስቀሻ ሰም አቅልጦ እንደማህተም የሠራው ነው።

«የንጉሡ ደብዳቤ?» አለ አይኖቹ ቡዝዝ እንዳሉ። ከዚያም ትዝ አለው። «እ! አዎን። ይቅርታ ያድርጉልኝ። ይህ ቅዝቃዜ አዕምሮዬንም አደንዝዞታል። አዩ አባቴ፣ ይህ የማይቻል ነው»

«ለምን ቢሉ?»

«ጠፍቶብኛል»

መብረቅ ወርዶ ክፍሉን ቢመታውና ኮርኒሱንም ለሁለት ቢከፍለው ኖሮ ይህን ያህል አባ ፕላንቴይን የሚናገሩትና የሚሉት አያጡም ነበር።

«እንዲህ በቀላሉ! ጠፋ ነው የምትለው። ለመሆኑ የምትናገረው ምን ሊሆን እንደሚችል ትገነዘባለህ?»

ከዚያም፣ ጥቁር ዘርፋፋ ቀሚስ የለበሱት ሰው፣ ራሣቸውን ከተቆጣጠሩ በኋላ ከፍ ባለ ድምፅ ተናገሩ። «ና፣ ና፣ ና! ልታገኘው ይገባሃል። የምትለው ሁሉ ሊሆን አይችልም፣ በቃ ሊሆን አይችልም። በሁሉም ዕቃ ውስጥ ፈልገው። መመለስ ካለብህም አይኖችህን መሬቱ ላይ ተክለህ እስከማርሴይ ድረስ ትሄዳለህ»

«አይሆንም» አለ ፖንሴ፣ በትንሿ ታሪኩ ላይ ጉዳዩን ሊዘጋ ፈልጎ። «ይመኑኝ፣ ምንም አያደርግልንም። የጠፋብኝ ደግሞ በጀልባው ላይ ነው»

«ወደ ማርሴይ አንድ መልዕክተኛ እንላክ። ጀልባው እስከአሁን ድረስም ምናልባት እዚያው ሊሆን ይችላል። ወይም እንዲያቆመው ሊያደርግ የሚችል ሌላ ፈጣን ጀልባ ልንልክ እንችላለን»

ጆን ባፕቲስት ጭንቅላቱን አነቃነቀ

«እየነገርኩዎት፣ ጥቅም የለውም»

አንድ ወንበር ሳብ አደረገና በጉን በኩል አንዱን ክርኑን በጀርባው በኩል አሣርፎ፣ መጠጥ ቤት ውስጥ ያለችግር እንደሚዝናና ሰው ተቀመጠበትና የሚከተለውን ታሪክ ነገራቸው

«ሣርዲኒያን ዞረን ልንጨርስ ስንል ነበር። እርስዎ እንደተለመደው በመርከቡ ፊት ባለው ክፍል ውስጥ እንደነበሩ በሚገባ አስታውሣለሁ። እንደሚመስለኝ ይፀልዩ ነበር።

የለም፣ ምሣሌዎችን ያነብቡ ነበር። አዎን ልክ ነኝ። ምሣሌዎችን ያነብቡ ነበር። የባህሩ ወሰል ቢያንስ ሦስት ጫማ ርዝመት ያህል ባለው ትልቅ አሣ እንቅስቃሴ መስመር ያበጃል፡ ስንመለከታቸው የሚከተሉን ይመስል ነበር። ወደ ምግብ ማብሰያው ክፍል ወርጄ የደራረቁ የዳቦ ቅርፊቶች በማምጣት አቅጣጫቸውን ሳስለውጣቸው እችል እንደሆን ለማየት ወረወርኩላቸው»

«እናስ?» ሲሉ ጀስዊቱ ይበልጥ እየከፋቸው

«እንደገመትኩት ሠራልኝ! አሦቹ አቅጣጫቸውን ለወጡ! ወደ ዳቦው ቀጥ ያለ መስመ ሰሩ»

«ከአሣህ ጋር ዲያብሎስ ይውሰድህ» አሉ አባ ፕላንቴይን «እና ደብዳቤው ምን ሆነ»

«ከኪሴ ወደቀብኝ»

«መርከቡ ወለል ላይ»

«አይደለም ውሃው ውስጥ»

ካህኑ ራሣቸውን ለማረጋጋት እጆቻቸውን በሾላው ጣውላ ጠረጴዛ ላይ አሣረፉ

«እናም ከነዚያ ውስጥ ሶስት የሚሆኑ ጭራቆች ወረቀቱ ላይ ሲራኮቱና ወረቀቱ ብጭቅጭቅ ሲያደርጉት አየሁኝ ብልዎ ያምኑኛል፣ አባቴ» አላቸው ፖንሴ እየተሟሟቀ

ጀስዊቱ እጃቸውን ልባቸው ላይ አሣረፉ። የሚተነፍሱ አይመስሉም።

«እና ምን ገጠመዎት አባቴ፣ እመምዎት እንዴ» ሲል ጆን ባፕቲስት ጠየቃቸው።

ጀስዊቱን በራሱ ወንበር ላይ እንዲቀመጡ ካደረጋቸው በኋላ፣ አንድ አገልጋይ ከስኳር የሚዘጋጅ አንድ ብርጭቆ ጠንካራ የአልኮል መጠጥ እንዲያመጣ አዘዘ።

አባ ፕላንቴን፣ ወዲያውኑ ጠንካራ ጣውላ ሆነው ከድንገተኛው ሕመማቸው ተሻላቸው። ፕላንቴይንን ሊረዷቸው የመጡ ሌላ ቄስ፣ ሕመምተኛው እርሱን ሲያዩት የስሜት መረበሽና ቁጣ የሚፈጠርባቸው መስሏቸው፣ ፖንሴ ለቅቆ እንዲወጣ ምልክት ሰጡት።



እስከዚህ ጊዜ ድረስ፣ ጆን ባፕቲስት የሚመርጣቸው ታካሚዎቹ ቤት የለሾችና ሥራ አጥ በመሆን በሴ ቢዩ ኖይሬ ውስጥ አባቢዎች ከሆኑት መካከል ነበር። የሆቴሉ ጥቂት ክፍሎች የተከራዩት ለአነስተኛ ነጋዴዎችና በማይታወቅ ሥራ ላይ ለሚዞሩ የውጭ አገር ሰዎች ነው። መጠጥ ቤቱ በጋሪ ነጂዎች፣ በወታደሮችና በአቅራቢያው ባለው ቦታ ላይ የሚሠሩ ወዝ አደሮች ባለማቋረጥ እንደተሞላ ነው። ሙሴ ራኦል፣ በወዳጃዊ ሁኔታ ሰላምታ ያቀርብላቸዋል። ጆን ባፕቲስት፣ ከፕላንቴይን ጋር ከነበረው ግንኙነት በተመለሰ ምሽት፣ የሆቴሉ ባለቤት ይጠብቀው ነበር። ወደ አንድ ተአምረኛ የሆነ ሕመምተኛ ቤት ሊወስደው ስለፈለገ ስለህመምተኛው ሲናገር እንኳ በአክብሮት እሸሽ ይላል።

የሰውዬው መኖሪያ በዚያው መንገድ ላይ ነበር። እንዲያውም ከመጠጥ ቤቱ በቀጥታ ባሻገር ነው። የመኖሪያ ቤቱ ፊት ለፊት የድንጋይ ሕንፃ ከፍታ፣ ግልብጥ የሚል ከሚመስለው ግማሽ የጣውላ ስሪት ከሆነው ከሴ ቢዩ ኖይሬና በዙሪያው ካሉ ደሣሣ ጉጆዎች ጋር ተቃራኒ ነው።

«ከግማሽ ምዕተ አመት በፊት» ሲል ባለ ሆቴሉ ቀጠለ «ንጉሡ በጠመንጃም ይሁን በጉራዴ መፋለምን ህገወጥ ከማድረጋቸው በፊት፣አሁን የምወስድህ ቤት ፖሪስ ውስጥ ታላቅ የሻቦላ ግጥሚያ ማዕከል ነበር።»

«ኧረ! እንዲህ ከሆነማ ጉራዴዬን ማምጣት ነበረብኝ!»

«በዛሬው ዘመን እንዳችም የሚያስፈራ ነገር የለም» አለ ሙሴ ራውል ወደ ሕመምተኛው ቤት ከመድረሳቸው በፊት፣ ለፖንሴ ጥቂት መረጃዎች ለመስጠት እያስቀመው፣ «ቤቱ እጅግ ለተከበረና በፖርላማው ውስጥ ለረዥም ዘመናት ሕግ አውጭ ሆኖ ይሠራ ለነበረ ክበርቴ ነበር የተሸጠው። ባለቤቱ፣ ከሃያ ዓመቶች በፊት በወረርሽኝ ሳቢያ ሞታበታለች። ይህ አጋጣሚ ሰውዬውን በእግዚአብሔር እንዳያምን አድርጐታል ብለው ያወሩበታል፣እኔ ግን አላምንም። በጣም እርግጠኛ የሆነው ግን ሁለቱን ልጆቹን በሚገባ ማሣደጉ ነው። ልጆቹ በአሁኑ ጊዜ ያደጉ ስለሆኑ እዚህ የሚመጡት አልፎ አልፎ ነው። ሴት ልጁ፣ የውጭ ተወላጅ ስላገባች፣ የምትኖረውም ውጭ አገር ነው። ወንድ ልጁ በኢስት ኢንዲስ ክፍለ ጦር ውስጥ በማገልገል ላይ ነው። ሰውዬው አሁን የሚኖረው ብቻውን ቢሆንም፣ ፍልቅልቅ ፀባይ ስላለው በመኖሪያ ቤቱ ውስጥና አልፎ አልፎም ወጣ እያለ መዝናናት ይወዳል። ባለፉት ስድስት

ወሮች ግን ብዙውን ጊዜ ታማሚ ሆኖ ቆይቷል። የሕመሙ ስቃይ በጣም ከባድ ስለሆነ አንዳንድ ጊዜ ስቃዩ ያስጮኸዋል። የስቃይ ድምፁ ሌሎች እላፊ አግዳሚዎችን እንዳይረብሽ በማለት በቤቱ ሌላኛው በኩል መኝታውን እስከለወጠበት ጊዜ ድረስ እስከ ሆቴሉ ይሰማ ነበር። ሐኪሞች፣ እርሱንም ገንዘቡንም በሚያሳፍር ሁኔታ ነው የያዟቸው። በእውነቱ ገድለው ገንዘቡን ሊወስዱበት የሚንቀሣቀሱ ይመስላሉ። ሕጋዊውን መንገድ ተከትለው አስቀድመው ሊያጠፉት እንደሆኑ ርግጠኛ መሆን ትችላለህ። በአሁኑ ጊዜ የምትጠብቀው አንዲት የቤት ሠራተኛ ብቻ አለችው። እንደ ዕድል ሆኖ ሴትዮዋ ደህንነቱን የምትከታተልለት ቅድስት ሰው ነች። ስላንተ ነግሬው ነበር። ባለፈው ምሽት በጣም አስፈሪ ድንገተኛ ሕመም ገጥሞት ነበር። ዛሬ ጧት ይህችው የቤት ሠራተኛው መጥታ አንተ እንድታክመው የሚፈልግ መሆኑን ተናገረች።»

ይህን ተናግሮ፣ ሙሴ ራኦል ወደ በሩ ተጠግቶ የብረት ሰንሰለት ሣበ። በጣም በርቀት፣ ከኦናው አዳራሽ ባሻገር ደወል ሲንቃጨል ሰሙ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ሠራተኛይቱ መጣች። ፊትዋ ሙሉ በሙሉ የተሸበሸበ ሲሆን አይኖችዋ ግን እንደወጣት ይንቦገቦጋሉ። ወገቧ ላይ የታሠረ ሽርጥ ለብሳ ፀጉርዋ ላይም ሻሽ ሸብ አድርጋለች።

«ፍራንቾይዝ፣ እሱ አሳዳሪሽን ለማየት መጥቷል» አላት ባለ ሆቴሉ

ስሟ ሲጠራ፣ ጆን ባፕቲስት ደነገጠ። የእሊስ ሣጣብም መላ አካሉን እንደ ፖቤ ሰነጠቀው። ወዲያውኑ ግን መለስ አለ። ሠራተኛዋ፣በሸላ ጣውላ የተሠሩ ሣጥኖች በተደረደሩበት ረዥም ጨለማ መተላለፊያ እየመራች ወሰደቻቸው። በአሁኑ ጊዜ እና ቢሆኑም፣ አዳራሾቹ በሙሉ አንድ ዘመን ላይ በቤተሰብ የተሞሉና በሕፃናት ጫጫታ የደመቁ እንደነበሩ ለመገመት የሚቻልባቸው ናቸው። የሚንሣጠጥ ደረጃ ወጥተው፣ ሣምራዊ የቀለም ንድፍ የተጌጠበትና ቀይ ከፋይ መጋረጃ የተጋረደበት መኝታ ክፍል ውስጥ ገቡ።

ሰውዬው፣ የናይለን አንሶላ በተነጠፈበት አልጋ ላይ ተጋድመው ይጠብቋቸዋል። ረጅም ሰው ናቸው። ፊታቸው ክብና ፀጉራቸውም በአጭሩ የተቆረጠ ሽበቶ ነው። በሕመም ስቃይ በተጨማደደ ፊታቸው ላይ ደካማ ፈገግታቸውን በግድ አሣዩ።

ባለሆቴሉና ሠራተኛዋ ሴት ወጣ እንዳሉለት፣ ፖንሴ ጠየቃቸው። ሕመምተኛውን መረመራቸው። ታማሚው ስቃዩ የት ላይ እንደሚበረታ ሳለመጮህ ጥረት እያደረጉ ያመለክቱት ጀመር። ረዘም ላለ ጊዜ አዎን ወይም አይደለም በማለት በጭንቅላት ማወዛወዝ



ብቻ እንዲነግሩት በማድረግ ጠየቃቸው። በመጨረሻም የሕመሙን ምንነት የተገነዘበ መሆኑን በሃሣቡ ካረጋገጠ በኋላ፣ በሚቀጥለው ማለዳ እንደሚመለስ ቃል ገብቶ ተሰናብቷቸው ወጣ።

የሌሊቱን እኩሌታ በላይ፣ በሚቀጥለው ቀን ለህመምተኛው የሚሰጣቸውን መድሃኒት ሲያዘጋጅ አመሸ። ይሁን እንጂ የህመምተኛው ስቃይ አልነቀሰም። በዚህም የተነሣ ቀጣዩን ከሰዓት በኋላ ሁሉ ሌላ አዲስ መድሃኒት ሲያዘጋጅ ቆይቶ አመጣ። ይህኛውም መድሃኒት ከመጀመሪያው የተሻለ ውጤት አላመጣም። በሚቀጥለው ምሽት ጥረቱን ወደ ሌላ አቅጣጫ አዞረ። ሜትር ዠረሚ እዚህ ሆኖ፣ ግሩም መድሃኒት በማዘጋጀት ሊያግዘው ባለመቻሉ አዘነ። በመጨረሻም፣ በሚቀጥለው ማለዳ ለህመምተኛው ከሲስተስ ቁጥቋጦ ወተት የተዘጋጀውን ሦስተኛውን መድሃኒት አመጣላቸው። ይህ መድሃኒት ከግማሽ ሰዓት ባነሰ ጊዜ ውስጥ የማረጋጋት ውጤት አሣየ። የስቃዩ መቀነስ በሕመምተኛው አይኖች ውስጥ በሚስተዋሉት መርካቶች ፊታቸው ላይ ሲነበቡ ይስተዋላሉ። እፎይታው፣ በፈንታው ሕመምተኛው እንዲያንቀላፉ ረዳቸው። የዚያን እለት ማታ ሕመምተኛው ጆን ባፕቲስትን እንደገና አስጠሩት። ወጣቱ ሰው ሲደርስ ሕመምተኛው ልብሶቻቸውን ለብሰውና ተቀምጠው አገኛቸው።

«እባክህ ተቀመጥ» አሉት ሰውዬው፣ በወዳጃዊ አነጋገር። «ራሴን እንዳስተዋውቅህ ፍቀድልኝ። ስሜን የምታውቀው አይመስለኝም። ሮበርት ዱ ሣንግራይ እባላለሁ።»

# 4

አሊስን ወደ ጊዛ ተከትለዋት ከሄዱት አሽከሮች አንዱ ሚካኤል ነበር። ይህ ከሱክሶር የመጣ ሸበቶ የኮፕቲክ አማኝ፣ ተቀያያሪዎች የፈረንሣይ ዲፕሎማት ቤተሰቦችን ላለፉት ሃያ አመታት በፈረስ አጣቢነትና በግልቢያ አስተማሪነት ቆንስላው ውስጥ ሲያገለግል የኖረ ነው። ግብፃውያን፣ ለጌቶቻቸው ያላቸውን በተለይም እመቤታቸው ሴትና የደስ ደስ ያላት ከሆነች የሚያሣዩትን የፍርሃት አድናቆት ለአሊስ ያሣያታል። በመጀመሪያ ላይ ምን እንደምትፈልግ ሊረዳት አልቻለም። በኋላ ግን የግልቢያ ትምህርት እንደምትፈልግ ጠየቀችው። እንደነመተው ሁለቱንም እግሮችዋን በፈረሱ አንድ ጐን በማድረግ በአጥር ግቢው ዙሪያ ለመዟዟር የፈለገች መሰለው። ለዚህም የሚስማማውን ከቤቱ ቢታች ሣር የለበሰ ስፊ የመጋለቢያ ቅጥር ቦታን መረጠ። በሁለተኛው ቀን ልምምድዋን እንድትደግመው ፈረሱን አዘጋጀላት። አሊስ ግን ችሎታዋን በፍጥነት ማሻሻል እንደምትሻ ነገረችው። አስንጋጡን ሲያስጮህበት ፈረሱ የዝግታ ስግሪያ ጀመረ። ሶስተኛውን የልምምድ ግልቢያ ለማድረግ ዝግጅት እያደረገችና ሽማግሌው ፈረስ እጣቢ ቅጥሩን እያጠባበቀ ሣለ አሊስ ቀረበችው። በቀጥታና በማያወላውል አይነት ተመለከተችው። ከዚያም በወጣት ሴት ልጅ ላይ ሊያስፈራ በሚችል ቁርጠኛነት ለስለስ ባለ ቋንቋ አቋሟን ገለፀችለት።

«ሚካኤል፣ እየሀ፣ ብዙ ጊዜ የለንም። አባቴ በማንኛውም ቀን ወደ ካይሮ ሊጠራኝ ይችላል። እስከዚያው ድረስ ግን ግልቢያ መማር እፈልጋለሁ። ግልፅ ነው? በኮርቻው ላይ ሁለት እግሮቼን በአንድ ላይ አድርጌ በጐን የመቀመጡንና በተወሰነው ክበብ ውስጥ የመዞሩን ነገር ከእንግዲህ እንርሣው። የወንዶችን ኮርቻና ጥንድ መኮርኮሪያዎችን ጫንልኝ። ማንኛውንም ነገር ሊቋቋም የሚችል ወፍራም ቦላሌ እለብሣለሁ። ልዩ ልዩ አይነት የፈረስ እርምጃዎችን፣ ስግሪያዎችን፣ ግልቢያዎችን፣ እንዴት እንደሚዘለል፣ እንዴት በፍጥነት ወደፈለግሁበት ቦታ መጋለብ እንደምችል አስተምረኝ።»

ሽማግሌው ሰውዬ ቢገርመውም፣ ትዕዛዝዋን ተግባር ላይ አዋለው። ከፈረስ ላይ ሳትወድቅ ግልቢያ መማር አትችልም ብሎ ሰጋ። በርሱ ስህተት የተነሣ ብትወድቅና አንድ አጥንትዋ ቢሰበርስ? ቆንሲሉን አይወደውም። ነገር ግን ይፈራዋል። ይህን የስጋት ችግሩን፣



አሊስ አስወገደችለት። ምንም አይነት አደጋ ቢገጥማት ሙሉ በሙሉ ተጠያቂነቱ የራስዋ እንደሆነና ፈረሱንም ሙሉ በሙሉ በራስዋ ፍላጐት እንደመራችው እንደምትገልፅ ነገረችው።

ርግጠኛ ቃሏን ሲቀበል፣ ሚካኤል ሥራውን በፈቃደኝነት ገባበት

በአንድ ሣምንት ውስጥ ፍርሃቱና ስጋቱ ወደ ኩራት ተለወጠ። ወጣቷ ተማሪው እጅግ ድንቅና ፈጣን አካላዊ እንቅስቀሴ ማድረግና አጀማመሯም በሚያስደስት የአቀማመጥ ችሎታ መሆኑን ተገነዘበ። ለተፈጥሯዊ ሞገስዋና ለማያጠራጥረው ድፍረትዋ ምስጋና ይግባውና፣ ፈረስዋን ጠበቅ፣ ነገር ግን ለስለስ ባለ አዛዥነት መቆጣጠር ቻለች።

በአጭር ጊዜ በእግር መንገዶች ላይ መጋለብ ጀመረች። ርዳታ የምትጠይቀው ብቻዋን ልትወጣ ስትል ብቻ ነው። ምክንያቱም ያዘጋጀላት አንድ ፈረስና አንድ ኮርቻ ብቻ ነው፣ ከዚህም ባሻገር ስጋላቢዎች ሁሉ ምክርና ትምህርት የሚሰጠው አዛውንት ባለበት የቁርጥማት ሕመም ሳቢያ እርሱ አይጋልብም። እንደ ጥንቃቄ ቤቱንና ንብረቱን ስመጠበቅ ተመድበው በመግቢያው አጠገብ የሠፈሩት ሚሊሺያዎች፣ የአሊስን ግልቢያ በንቃት ይከታተላሉ። በየዕለቱ ማለዳ አንድ ጋላቢ ከግቢው ወጥቶ ሜዳውን ሁሉ አቋርጦ ገበሬዎች በቀይ አፈር የሰሩትን የግድብ ቦይ አልፎ ሲሄድ ይመለከታሉ። ሚሊሺያዎቹ ይህን የሚያደርገው ወንድ ሰው ነው ሲሉ ያስባሉ። ምክንያቱም፣ አሊስ ፀጉርዋን በሰፊ ባርኔጣ ስር ስለደበቀችውና ቅርፅዋን ሊደብቅላት የሚችል ሰፊ ሸሚዝ ስለለበሰች በሚገባ ሊለዩዋት አይችሉም።

የግልቢያ ልምምዱ ፍፁም ሊያደክማቸው ቢችልም፣ ወጣቷ ወይዘሪት ግን ልታቋርጠው አልፈለገችም። በርሷ ጥያቄ መሠረት እነርሱ ከደረሱ አንድ ቀን በኋላ፣ ሜትር ዠረሚ በጀልባ መጥቶ ተቀላቅሏቸዋል። ወደ ወደቡ ዳርቻ በውድቀት ለሊት ያለ አንዳች ረዳት ረዥሙ የእንጨት ሣጥን ተሸክሞ እስከቤቱ ድረስ ዘለቀ። ይህ ረዥም የእንጨት ሣጥን ከመሬቱ ጋር በተጋጨ ቁጥር የብረት ቅልጭልጭታ ድምፅ ይሰማበታል። ከዚህ ረዥም ሣጥን ውስጥ እጅግ ብዙ የተቋጠሩ ገመዶችን፣ ሁለት የደረት መከላከያ የቆዳ ጋሻዎችንና ሁለት የሻቦላ ጭምብሎችንም አወጣ።

በዚያኑ ዕለት ማታ፣ ወደ አባይ አቅጣጫ በሚወስደው የእንጨት መተላለፊያ መድረክ ላይ፣ አሊስ የመጀመሪያውን የሻቦላ ግጥሚያ ትምህርቷን ወሰደች። በዚህ አይነት ግጥሚያ ላይ ከሜትር ዠረሚ ጋር እኩል ለእኩል የሚሆንበት ነጥብ የለም። ወጣቷ ተማሪ የምትፈልገውን ከተገነዘበ በኋላ እንደ ወንድ ክስተርና ጠበቅ ባለ ሁኔታ ያዛት።

ከዚህ በመቀጠል፣ ፍራንቾይዝንም እንዲያስተምራት አሊስ ጠየቀችው፡፡ እንዲህ ከሆነና እርሱ ከዚያ ቦታ እንዲለቅቅ የሚገደድ እንኳ ቢሆን፣ ሁለቱ ሴቶች ልምምዳቸውን በጋራ ሊቀጥሉ ይችላሉ፡፡ በሁለተኛው ትምህርቷ ላይ ባጋጠማት ግራ መጋባት የተነሳ፣ አሊስ በውስጧ ፈገግ አለች፡፡ ፍራንቾይዝም፣ የአጀማመርዋን ገልጃጃነት አጋነነችባት፡፡ እኔ የለሁበትም፣ የሚል ማስተባበያ ለማቅረብ የማይችለው ሜትር ዠረሚ ስሜቱን ሰርቆበት በነበረ ጉዳይ ሣቢያ ሁለት ጊዜ በሻቦላው ተነካ፡፡

ሁሉንም ከፈፀሙ በኋላ፣ የሻቦላውን ጠቢብ፣ ፎቅ ላይ ወደ ሚገኘው ክፍሉ፣ አሊስ ራሷ መብራት አብርታለት መራችው፡፡ ፍራንቾይዝ፣ ከልብ በመነጨ ስሜት ውስጣዊ ምስጢሯን ለዚህች ወጣት ጓደኛዋ ልትገልፅላት ፈለገች፡፡ ወጣቷ ግን ሁለመናዋን ድካም ሙጥጥ ስላደረገው፣ እንደደረሰች አልጋዋ ላይ ወድቃ እንቅልፍ ወሰዳት፡፡

ያልተቋረጠውን አካላዊ የልምምድ ሥርዓት በማከናወን ቀናት አለፉ፡፡ አንድ ጊዜ በአካባቢው ያሉትን ተልከስካሽ ተዘዋዋሪ ውሾችን፣ አሽከሮች ለማደን እቅድ አውጥተዋል ተብሎ ለሚሊሺያዎች ማስጠንቀቂያ ተሰጣቸውና ምሽቱን የሽጉጥ ተኩስ ልምምድ ሲያደርጉ አደሩ፡፡ አሊስ መሣሪያውን ጥይት ማጉረስ ካወቀች በኋላ፣ ሣትንቀጠቀጥ አንድ ደርዘን ጥይት ተኮሰች፡፡

ምሽቱ ክብዷቸዋል፡፡ ሦስቱም፣ በበረንዳው ላይ አብረው እራታቸውን በሉ፡፡ የጨዋታው ሞቅ ማለት ያሣደረባትን ውስጣዊ መቃጠል፣ አሊሰ መቻል ነበረባት፡፡ ሁለቱ ደግሞ፣ እንዲህ ፊት ለፊት መገናኘት መቻላቸው አሣፍሯቸዋል፡፡ ምግባቸውን በሚመገቡበት ጊዜ በመካከላቸው ረዘም ላለ ጊዜ የቆየው ፀጥታ በወንዙ ዳርቻ ባሉት ቀጤማዎች ውስጥ በሚኖሩት እንቁራሪቶች ማንቋረር በአንድ አፍታ ተሞላ፡፡

ስለአረም እጅግ ብዙ ተሞክሮ ያላቸውን ይህንን ሰውዬና ይህችን ሴት በማየት ልጃገረዲቱ ተደሰተች፡፡ ሁለቱም ሰዎች በተፈጥሯቸው ፍልቅልቅ ፀባይ ያላቸው ቢሆኑም በሚገባ ባልተዘጋጁበት የፍቅር ጉዳይ ግራ የተጋቡ ናቸው፡፡

የምሽቱ የአየር ፀባይ ይጫጫን ጀምሯል፡፡ ለፍራንቾይዝ ምንም ባትነግራትም፣ አንዳች ነገር በተፈፀመ በማለት አሊስ ተስፋ ታደርጋለች፡፡ ከዕለታት አንድ ቀን ምሽት ላይ ለሽርሽር ከሄዱበት ሲመለሱ በሙሉ ሃይላቸው ጋልበው ነበርና ራሣቸውን ስተው ሣለ፣ ወጣቷ ሴት ሁኔታው በሙሉ መጨረሻ ላይ የተለወጠ ነው የሚል ግምት አደረባት፡፡ ከእራት በኋላ፣ በተለይ ፀጥ ባለበት ጊዜ ሜትር ዠረሚ ተናገረ፡፡ ወፍራሙ ድምፅ፣ ጨለማውን ሞላው፡፡



« ይቅርታ ወይዘሪት፣ እነዚያን ዕፅዋቶቻችንን አደራ የሰጠሁት ለአንድ ጐረቤት ነው፡፡ እፅዋቱ ለኛ ምን ማለት እንደሆኑም በሚገባ ታውቂያለሽ፡፡ ስለዚህ ነገ ጧት ወደ ካይሮ እንድመለስ ፈቃድሽን እጠይቃለሁ፡፡»

«እንዴ? ትምህርታችንስ . . » ካለች በኋላ፣ አሊስ በራስ ወዳድነቷ ወዲያውኑ አዘነች፡፡

«ማንም ቢሆን መጣደፍ የለበትም፡፡ መሠረታዊዎቹን ተምራችኋል፡፡ ማሻሻል የሚቻለው በልምምድ ነው፡፡ ሽምላዎቹንና ሌሎችን መሣሪያዎች እተውልሻለሁ፡፡ ስለዚህ ከፍራንቾይዝ ጋር መለማመድ ትችያለሽ፡፡ እውነቱን ለመናገር በዚህ ረገድ እኔ ከእንግዲህ አላስፈልጋችሁም፡፡

ፍራንቾይዝ፣ በተስፋ መቁረጥ ሁኔታ የታችኛው ከንፈርዋ እየተንቀጠቀጠ ሜትር ዠረሚን ተመለከተችው፡፡ ብድግ አለችና ራሷን አረጋግታ፣ የቡናውን ማቅረቢያ ይዛ ወደ ማዕድ ቤት ሄደች፡፡ የሻቦላ አለቃውም፣ ከመቀመጫው በመነሣት፣ ለአሊስ ጐንበስ ብሎ ቀዝቃዛ ሰላምታ ከሰጣት በኋላ፣ ፋኖሱን ይዞ በተቃራኒው አቅጣጫ ወጥቶ ሄደ፡፡ ጭር ባለውና በባዶው የደረጃ መወጣጫ ላይ የእርምጃው ድምፅ ሲያስተጋባ ሰማችው፡፡

ሜትር ዠረሚ በሚቀጥለው ቀን ንጋት ላይ ሄደ፡፡ ሁለቱም ሴቶች እስከወደቡ ድረስ ተከተሉት፡፡ ጀልባዋ በማዕበሉ ተገፍታ በመንሣፈፍ ነጐደች፡፡ የጉዞዋ መስመርም ጠፋ፡፡ የፀሐይዋ ቅርፅ በጭጋግ ምክንያት ተዛብቶ በርቀት በሚገኙት የውሃው ዳርቻ የተምር ዛፎች ውስጥ እራት ማዕዘን ቅርፅ ይዛ ወጥታለች፡፡ ሸራ ያልተወጠረባት ጀልባ እንጨት ተሸክማ ሳይታወቅ በውሃው ላይ አለፈች፡፡ ቀጭኑ መንጠቆዋ እንደ አንቴና መወጠሪያ ከምሰሶው ላይ ተመሣቅሎ ወርዷል፡፡ ሁለት ትላልቅ ሃምራዊ ቀለም ያላቸው ወፎች ብቅ ጥልቅ እያሉ መንቆራቸውን ወደ ፀሐይ አቅጣጫ ያመላክታሉ፡፡ ከርቀት ሲመለከቷቸው የጋመችውን ክብ ነገር ከውሃው ውስጥ ቀስ እያሉ እየሳቡ በማውጣት የያዟት ይመስላል፡፡ ፍራንቾይዝ ታለቅሣለች፡፡

«ምን ሆንሽ?» ስትል አሊስ ጠየቀቻት፣ ክንዷን ይዛ

ፍራንቾይዝ አይኖችዋን ጠራረገች፣ በአፍንጫዋም አየር ማገችና ትከሻዋን ነቀነቀች፡፡ ወዲያውም አሊስን ተመለከተቻት፡፡

«በጣም አዝናለሁ፡፡ በአጭር ጊዜ ውስጥ ይሻለኛል፣ ተመልከቺው፡፡ በቁጥጥሩ ሥር ነው፡፡ በኛ ዕድሜ እንዴት ጅሎች ነን?»

«እነጋግረሽው ነበር?» አለች አሊስ፣ ወደቡ ዳር ተቀምጣና ከጕንዋ ያለችውን ጓደኛዋን እንድትቀመጥ እያደረገቻት።

«አዎን እነጋግሬዋለሁ። ሁሉንም ነገር እስከአሁን ድረስ ገምተሽ ቢሆንም እነግርሻለሁ። እዚህ ወደብ ላይ አሣ የሚያጠምድ በመምሰል ቀኑን ሙሉ ወደኔ ለመምጣት ሳይችል እንዴት እንደሚውል ባየሽው። ትናንት ከሰዓት በኋላ ስሄድ፣ ሁልጊዜም ለቁርጥማት ሕመሙ በማለት የአባትሽን አንድ ጠርሙስ ብራንዲ ከእጁ የማያጣውን ሚካኤልን አግኝቼው ነበር። እኔም ሁለት ዋንጫ ሙሉ ጠጥቼ ወደዚሁ መጣሁ። እኔ መድረሴን እስከሰማበት ድረስ፣ ገርሬሚ ፍፁም አንድም ነገር አይሠራም ነበር። ከዚያ በኋላ የማጥመጃ ገመዱን መሣብና ከመንጠቆው ጋር መታገል ጀመረ። ሄጄ ከጐኑ ተቀመጥኩ። አጉረመረመ። እመኚኝ፣ ፈራሁ። መዋኘት ባልችልም ውሃው ውስጥ ዘልዬ ልገባ ነበር። በኋላ ተናገረ። ያ ድምፁ እንዴት እንደሆነ ታውቂው የለ? እንዴት ጭንቀት እንደተሰማኝ ቢገባሽ? አንዳች ነገር ልናገር ስል ያ ከበሮ ድምፅ ጆሮ ግንዴ ላይ ይደልቅ ጀመር።»

«እርሱስ ምን አለ?»

ፀሐይዋ ከፍ ብላለች። የወንዙ ዳርቻዎች ብሩህ መሆን ሲጀምሩ፣ ውሃውም ጠቆር ብሏል። የውሃ ዳር ወፎችም በርረው ሄደዋል።

«ፍራንቾይዝ ሲል ጀመረ። ስሜን ሲጠራው የተሰማኝን ሁኔታ ልነግርሽ አልችልም። «ፍራንቾይዝ፣ ልትነግሪኝ የመጣሽበትን ጉዳይ አውቀዋለሁ። መነጋገሩ ፋይዳ የለውም። አየሽ፣ ወላጆቼ እምነታቸውን በመለዋወጣቸው አሰቃቂ መከራ ተቀብለዋል። ይህንን አንዳችንም አላደረግንም። ይህ ደግሞ የሃይማኖት ጥያቄ ጉዳይ አልነበረም። ሐቁ ተመልሰን ያለፈውን ሕይወታችንን ለመጀመር አቅሙ አልነበረንም። አየሽ፣ እኔ በበኩሌ የራሴን ሰጥቻለሁ» ለአፍታ ያህል ንግግሩን ገታ አደረገው። የማጥመጃ ገመዱንም አስቀመጠውና እጆቼን በእጆቼን ላይ ጫናቸው። ከዚያም «ሕይወት ከቃል ኪዳኔ ልትፈታኝ ትችላለች ብዬ አስባለሁ። ያን ጊዜም ነፃ እሆናለሁ። ያን ጊዜ ቀሪውን ሕይወቴን በሙሉ አንቺ ፈቃደኛ ሆነሽ ልትቀበይኝ ከቻልሽ ቃልኪዳኔን የምሰጠው ላንቺው ነው።»

ፍራንቾይዝ ልቅሶዋን ለቀቀችው። አሊስ፣ እጆችዋን በእጆችዋ ውስጥ ይዛ ልታበረታታት ሞከረች። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ሁለቱም ተያይዘው ወደ ቤት ወጡ።



ይህ ማለት ለርስዋ ደስታ ማለት መሆን አለበት። ግን ምን አይነት ያልታደሉ ፍቅረኛሞች ናቸው፣ ስትል አሊስ አሰበች።

ከጆን ባፕቲስት ጋር ያሣለፈቻቸውን አጭር ጊዜያት መለስ ብላ ተመለከተች። እርሷም ብትሆን ባልተለመደ ሁኔታ ደካማና የማያስደስት የሚመስል ስዕል ነበራት።

ቬርሣይለስ ውስጥ በብዙ የሚወደዱ ወይዛዝርት መሃል ሆኖ፣ ክቶውንም እንዴት ሊያስታውሰኝ ይችላል ስትል አሰበች።

ይህ ሃሣብ በሌላ ጊዜ ቢሆን ኖሮ እንድትረታ ሊያደርጋት ሲችል፣ አሁን ግን ፈጣን ግልቢያ እንድታደርግ ቀሰቀሳት።

የሆቴሉ ባለቤት፣ ስለምክር ቤቱ አባል ሮበት ፖሞት ዱ ሣንግራይ የሰጠው አጭር መግለጫ ትክክል ነው። ሰውዬው በተፈጥሯቸው ፍልቅልቅ ከመሆናቸውም በላይ ከሌሎች ሰዎች ጋር ሲሆኑ ደስተኛ ናቸው። በተለይም ሕመሙ ከለቀቃቸው በኋላ የርሣቸው መገለጫ የሆኑት መልካም ባህርያቶች ሁሉ ጐልተው መውጣት ጀምረዋል። ለጆን ባፕቲስት ምስጋና ይግባውና ይኸው ለመጀመሪያ ጊዜ የሕመማችውን ስቃይ የሚከላከሉበት መሣሪያ አግኝተዋል። ይህም ሳይሆን ቢቀርና የአጭር ጊዜ ከስቃይ የመዳን ዕድል ቢሆንላቸውም እንኳ፣ ለጆን ባፕቲስት ታላቅ ውለታ አለባቸው። የተሰጣቸው ሕክምና የሕመሙን ምልክቶች ረዘም ላለ ጊዜ አስታገሰላቸው። ጊዜ ባለፈ ቁጥር የመዳን ስሜታቸው እርግጠኛ እየሆነ መጣ። በዚህ ምክንያት ለምስጋናቸውም ወሰን አልነበራቸውም። ከዚያም፣ መድሃኒት ቀማሚው፣ ፖሪስ ውስጥ ረዘም ላለ ጊዜ መክረሙ እንደማይቀር በማሰብ፣ የዚህን ቆይታውን ወጭ በሙሉ እንደሚሸፍኑለት አረጋግጠው ሠላሣ የወርቅ ኤኩስ ሰጡት።

አንዳንድ ጊዜ፣ ታላቅ ርህራሄ በሰዎች ውስጥ ያለውን ጥርጣሬ ሁሉ ያስወግዳል። የሃብታሙ ሰውዬ ወዳጅነት፣ በጆን ባፕቲስት አይኖች ሲታይ ለአገልግሎቱ በቂ ክፍያ ነበር። ያንሰኛል ብሎ ቢጠይቅ እንኳ የራሱ ስሜት ይጐዳበታል። በዚህ ሳቢያ የተሰጠውን የገንዘብ ቦርሣ ተቀብሎ ከዚህ በኋላ ምንም እንደማይቀበል አረጋገጠ።

ጆን ባፕቲስት፣ በየዕለቱ ከሰዓት በኋላ እየመጣ ሕመምተኛውን ይጎበኛቸዋል፡ የመንቀሣቀስ ነፃነታቸው የተመለሰላቸው ዱ ሣንግሬይ፣ በከተማው ውስጥ ሲዞሩ እየዋሉ ወደ ቤት የሚመለሱት በየዕለቱ ላላቸው ውይይት ሲሉ ብቻ ሆነ፡፡ በዚህ ሳቢያ እንደእውነቱ ከሆነ ማን ማንን እንደሚጎበኘም ግልፅ አልነበረም ማለት ይቻላል፡፡ አንዳንዴ ሐኪሙና ሕመምተኛው ከተለያየ አቅጣጫ በመምጣት በሩ ላይ የሚገናኙበትም ጊዜ ነበረ፡፡ ውይይታቸውና ጭውውታቸውም ከሕመም ጉዳይ አልፎ፣ በሁለት ጓደኞች መካከል እንደሚኖር ነፃና የፈለጉትን ጉዳይ እያነሱ ወደ መነጋገር ደረጃ ዓይነት ደረሰ፡፡

«እንዲያው ልጠይቅህና፣ ለምን እዚህ ቤት ውስጥ አትኖርም? ሌ ቢዩ ኖይር ጥሩ መጠጥ ቤት ቢሆንም፣ ከሁሉም አቅጣጫ እንደሚሰማው ደስ የማይል ሆቴል ነው» ሲሉ በአንድ የሣምንት ማብቂያ ዕለት አማካሪው ጠየቁት፡፡

«በመጀመሪያ ነገር ሁለታችን እንድንገናኝ ያደረገንን የሆቴሉን ባለቤት ውለታ መርሣት ይሆናል»

«ከርሱ ጋር ያለውን እኔ አስተካክለዋለሁ፡፡ በርግጥ ምግብህን ማቅረቡን ይቀጥላል፡፡ እኔም ብሆን፣ የፍራንቾይዝን መረቅ የመፈለጌና የመጋቤ ነገር እያበቃ ስለሆነ፣ ለኔም ጭምር ምግብ እንዲያመጣ እነግረዋለሁ፡፡ በዚህ ሳቢያ ጥሩ ደንበኞቹ ሆነን እንቀጥላለን፡፡ በሌላ በኩል፣ በዚህ ወቅት ባሉት ትርኢቶች ሳቢያ ያንተን ክፍል ወዲያውኑ ያከራየዋል፡፡» .

ጆን ባፕቲስት ተስማማ፡፡ አማካሪውም፣ አንድ የመኝታ ክፍል በፎቁ ላይ እንዲዘጋጅለት አዘዙ፡፡ ክፍሉ፣ ሙሉ ዕቃ የተሟላና ቀለል የሚል ነበር፡፡ በፊት ለፊቱ በኩል፣ ሥራ ብዙ ወደሆነው መንገድ የሚያሣዩ ሁለት ረዣዥም መስኮቶች አሉት፡፡ ከዚህም በላይ፣ አማኒያን በየበረንዳው ስር ወደ ቅዱስ ኢዩስታች ቤተክርስቲያን ሲመጡና ሲመለሱ ይታይበታል፡፡ በኢጣሊያ እምነበረድ የተሰራው ትልቅ የጢስ ማውጫ ባለመደፈኑ፣ እሣት ግር አድርጎ በማንደድ ራሱን ማሞቅ እንደሚችል በማወቁ ጆን ባፕቲስት ተደሰተ፡፡ ቤቱ በጀርባ በኩል የመኝታ ክፍል፣ ሁለት ትንንሽ ክፍሎችና ለስሙ ያለውን ሻንጣውን፣ የመድሃኒት ቦርሣውንና የገዛቸውን ጀሮዎች የያዘበትን ሳጥን ሊያስቀምጥ የሚችል ቁምሣጥን አለው፡፡

«ይህን የከተማ ቤት ስገዛው፣ ለአስር ዓመት ያህል ተዘግቶ የኖረና ለባለቤቶቹም እጅግ የሚጠላ ነገር ሆኖባቸው የነበረ ቤት ነበር፡፡» ሲሉ እንግዳቸውን ለማየት የመጡት ሳንግሬይ ተናገሩ፡፡



«ሰዎች እዚህ ይፋለሙ ነበር መሰለኝ?»

«ክፍለ ዘመኑ መጀመሪያ ላይ የጠራ ክብር አለን ለሚሉ ሰዎች የመገናኛ ቦታቸው ነበረ፡፡ በክብሯቸው ላይ ማንም ሰው ጥርጣሬ አልነበረውም፡፡ ነገር ግን የጥራቱ ጉዳይ፣ የማያላውሱ ሕጎች ነበሩበት፡፡ ሕጎቹንም እነርሱ ለሚያከናውኑት የግፍ ግድያ ሲሉ ራሣቸው ያወጡት ነበር፡፡ እዚህ ያለውን ተራ ጭሰኛ አስበው፡፡ ዶ ሞንት ሞሬንቺያ ቦቴቪል የተባለው ባለስልጣን፣ በሃያ ሰባት ዓመት ዕድሜው ሃያ ሁለት ጊዜ ፍልሚያ አድርጎ ነበር፡፡ የመጨረሻው ፍልሚያውን ያደረገው በሪቼሊዩ የከተማ ትልቅ ቤት ውስጥ ነበር፡፡ በዚህ ዕለት ማለትም ልክ በበጋው አጋማሽ ዕለት ሐምሌ 24 ቀን በዚሁ ፍልሚያ ላይ ታረደ»

«አኩሪ ገድል ነው» ሲል ፖንሴ ተቁነጠነጠ

«እንደዚያ ታስባለህ?»

«አምን፣እነዚያ ሰዎች በዕውነት የኖሩ ነበሩ? ብዬ አስባለሁ»

«ብዙ ጊዜ ግን ይሞታሉ፡፡ ሌሎችንም ይገድላሉ፡፡ ሁሉንም ነገር እስከዛሬ ድረስ በሚገባ አስታውሣለሁ፡፡ የፍሮንዴ አሰቃቂ ግድያ ትዝ ይለኛል፡፡ በሕዝባዊው ንቅናቄ ጊዜ ገና ሕፃን ነበርኩ፡፡ ሆኖም ግን፣ በወቅቱ፣ ሃይል ሕዝቦችን ይገዛ የነበረበትን ትርምስ ፈፅሞ አልረሣውም፡፡ የለም፣ አየህ ዶክተር፣ እኔ የሕግ ሰው ነኝ፡፡ የሚዛን ሰው ነኝ፡፡ ራሴን ሳስበው የነዚያ አውሬ መናፍስት ጠባቂያቸው ሳልሆን አሣሪያቸው እንደሆንኩ ነው»

ከመጀመሪያ ጀምሮ እነኚህን በትዕግስት የተሞሉና ሁሉንም ነገር በነፃ አዕምሮ የሚቀበሉ ጨዋ ሰው፣ ጆን ባፕቲስት ትልቅ እምነት አሣድሮባቸዋል፡፡ ወደ አቢሲኒያ ያደረገውን የጉዞ ታሪክ ነግሯቸዋል፡፡ ትረካውን ሁለቱም ሰዎች የድመት የመሰለ የእግር ቅርፅ ባለው ባለመደገፊያ ወንበር ላይ ሆነው፣ እግሮቻቸውን ወደ ነሐሱ የእሣት ማንደጃ ዘርግተው ለብዙ አስደሳች ምሽቶች ዘልቋል፡፡

እነዚህ ምሽቶች ካበቁ በኋላ ራሣቸውን በፅሁፍ ሥራ ላይ ለማሰማራት ወሰኑ፡፡ ሣንግሬይ ጀምረውት የነበረውን የተለያዩ የሰው ልጆች ሕጎችን ለማጠናቀቅ ተዘጋጁ፡፡ በሣንግሬይ ማግባባት፣ ጆን ባፕቲስትም የጉዞውን ታሪክ በጽሁፍ ለማስፈር ወሰነ፡፡ ሥራቸውንም በሁለተኛው ቀን ጀመሩ፡፡

አማካሪው፣ ከመፅሐፍት አጥኚ በላይ ናቸው። ሕመማቸው ፈፅሞ ከተዋቸው በኋላ ሕይወትን ሁሉ መፈተሽ ጀመሩ። በዚህም ያልዳሰሱት የደስታ መስመር አልነበራቸውም። በፖላስ ሮያሌ በተዘጋጀው የደመራ ምሽት ላይ የቻርትሬሱ መስፍን ያውቋቸው ስለነበረ ተጋብዘዋል። ማንግራይ ይህን የደስታ ምሽት ለመካፈል በጣም ደስ ስላላቸው፣ ጆን ባፕቲስትም አብሯቸው እንዲሆን በፈንታቸው ጋበዙት።

ሁለቱ ሰዎች በሰውነታቸው አቋም ቢለያዩም፣ ቁመታቸው ተመሣሣይ ነበር። አማካሪው፣ ለእንግዳው፣ በወርቅ ጥልፍ ያማረ ሙሉ ልብስና ያሸበረቀ የአንገት ፎጣ አዋሱት። ጋሪ ጭምር የሚያከራየው የሆቴሉ ባለቤት ሙሴ ራኦል፣ አንድ ሠረገላ ከነነጂው ላከላቸው። በጊዜ ለዕራት ለመድረስ ሄዱ።



# 5

በዚያን ዘመን የቤተመንግስቱን ሕይወት የሚያሣየውና፣ ፖሪስ ውስጥ በብቸኝነት የቀረው ፖላስ ሮያሌ ነበር። የተቀሩት የቤተመንግስት ተግባራት ሁሉ፣ በንጉሡ ዙሪያ እንዲሆኑ ተብሎ ወደ ቬርሣይለስ ተዛውረዋል። ፖላስ ሮያሌ ውስጥ እጅግ የደመቀ በዓል ቢደረግም፣ የሚያስፈራ አምባገነን የሌለበት ስነስርዓት ነበር። የቻርትሬሱ መስፍን፣ የንጉሡ የእኅት ልጅ ሲሆኑ በዙሪያቸው ለሚገኙት ሰዎች ሁሉ ፍቅርና ወዳጅነትን የሚያሣዩ ሰው ነበሩ። በዚህም የተነሣ በበዓሉ ላይ የነፃነት መንፈስ ሰፍኖ ነበር። እንዲህ ባለው ሞቅ ያለ የወዳጅነት ቦታ፣ እጅግ ውብ የሆኑ ዕፀዋት ከቬርሣይለስ ይልቅ እዚህ ይበልጥ ይደምቃሉ። እንደልብ በአንድ ላይ ሆነው የሚገኙት ውበት፣ ወጣትነትና ሰዛ በዚያ ቦታ በብዙ ድንቅ ሰዎች ዘንድ፣ በተለይም በሴቶች ውስጥ ተዋህደው ይገኛሉ። ማንግራይ፣ አጃቢውን ከቻርትሬሷ ልዕልት ጋር አስተዋወቁት። ባለቤታቸው የቻርትሬሱ መስፍን ግን፣ የዚያኑ ዕለት ጥቂት ቀደም ብሎ፣ እነርሱ ከመድረሳቸው በፊት ወደ ቬርሣይለስ ተጠርተው ስለሄዱ ሊያስተዋውቋቸው አልቻሉም።

በአራት ሰዓትና ከዕራት በኋላ የነበሩት ጥቂት እንግዶች፣ በሣሉን ውስጥ ተሰብስበው በነበረበት ጊዜ፣ ፖንሴ ጥንቃቄውን በመጠኑም ቢሆን ላላ አደረገው። ውብ ሴቶች ያሉበት አንድ ቡድን በጥግ በኩል በዙሪያው ተከለከለ። ስለነዚህ ወይዛዝርት ማንነት የሚያውቀው አንዳችም ነገር ባይኖርም፣ ከሁሉም ታላቅ የሚሆኑትን አንዷን ሴት ግን፣ ማዳም ማርኩስ ብለው ሌሎች ሲጠሯቸው ሰማ። የጆን ባፕቲስት ድንቅ አቀራረብና የትንግርቶች መፍለቂያ ስለሆነው ስለዚህ ቦታ ማስረዳት በመቻሉ፣ አንዳች ተአምር የሆነ ነገር የተደበቀበትን ማሽተት የሚችሉበትን ልዩ ተሰጥኦና፣ ባላቸው የማወቅ ጉጉት የተነሣ ይህን አዲስና ያልተደመደ ነገር ሰብረው ለመውጣት ስለጓጉ፣ ሴቶቹ ፖንሴን መሃላቸው አስገቡት። እርሱም፣ እውነቱን ተናጋሪው እርሱ ብቻ ስለሆነ እነዚህ ድንቅ የቤተመንግስት ሰዎች ባሉበት፣ አክብሮታዊ ፍርሃትን ለማስወገድ ሲል በወጥመዳቸው ውስጥ ሆን ብሎ ገባላቸው። አቢሲኒያን ሲገልፃት ለራሱ ፍፁም ሥልጣን ሰጠው። የተነገረውም ነገር ብዙ ሺህ የአግራሞት ጥያቄዎችን አስነሣ። አንዱን እያነሣ ሌላውን እየጣለ በሚገለባበጠው ማህበራዊ ጭውውት፣ ጆን ባፕቲስት ይህን ውብና ማራኪ ነገር ከሚያስፈልገው በላይ በማስፋት ስህተት ሠራ። አቢሲኒያውያን

እጅግ ታላቅ በሚሆነው ግብዣቸው ላይ፣ በሬ በቁሙ እንዴት እንደሚበሉ፣ በበዓሉ ቦታ የሚስተናገዱ እንግዶችም በበሬው አከርካሪ በኩል ጣቶቻቸውን እያሳለፉ የሚንዘፈዘፈውን ሥጋ እየቦጨቁ የሚወስዱ አድርጐ ያከማቸውን ዝርዝር ተረከላቸው።

የትረካው መጨረሻ የቀዘቀዘ የዝምታ ስንብት ገጠመው። አሮጊቷ ማርኩስ፣ የነፋስ ማራገቢያቸውን በትንሹ እያማቱ የቁጣ ግልምጫ አሣረፉበትና ወደ በረንዳው ተቆናጥረው ሄዱ። በዚያ የነበሩት ፈንጠዝያ ወዳዶቹ ወጣት ወይዛዝርት በሙሉ፣ አብረቅራቂውን ከወፍ ላባ የተሠራውን ልብሳቸውን እያንሿሹ ተከትለዋቸው እብስ አሉ።

በረዥሙ መቀመጫ ላይ ብቻውን የነበረው ወጣት፣ ከሴቶቹ ሰውነት ላይ በልብሶቻቸው ውስጥ ተጀቡኖ የነበረውን ጠረን ማገው። የሴቶቹ ጡቶቻቸው፣ የዝባድ ሽቱ፣ የበርበሬና ግሩም መዓዛ ያለው ጠረን ይረጫሉ። ፊቶቻቸው በነጭ የውበት ዱቄትና በእደስ ፍሟል። ይህን የመሰለ ደስ የሚል ነገር ከዚህ በፊት አይቶ አያውቅም። ከነዚህ ሴቶች እያንዳንዷ፣ ከወጣትም ሆነ ከአሮጊት ክፉኛ የሚያስጐመጁ ነበሩ። ከአንድ ዕፅ ላይ ጥቂት የፈሣሽ ጠብታዎች ቢነበር መድሃኒቱ እንደማያድን ወይም እንደማይገድል ዓይነት፣ እነዚህም ሴቶች ሴትነታቸውን ፍፁም በንፅህና አጠንክረው የያዙ ናቸው።

ይህ ሁሉ ሆኖ የቸገረው ነገር ነበር። ይህ የሚታየው ሁሉ በርግጥ በሰው ሰራሹ አቋማቸው ይሆን? እውነት ነው፤ በነዚህ በመቶዎች በሚቆጠሩ የሻማዎች ብርሃን ውስጥ፣ የክት ልብሶቻቸው ከተዘጋጁ በኋላና መልሰውም መመንቸክ ከመጀመራቸው በፊት በነበሩት ጥቂት ሰዓታት ውስጥ፣ እንዲህ ያለ ነገር በቤተመንግስት ውስጥ ተዝቢ ሊሆን ይችላል። ይሁን እንጂ፣ እነዚህ ሴቶች ራሣቸውን በሌላው ዓለም ውስጥ፣ ማለትም በእውነተኛው ዓለም ውስጥ ቢያገኙት ምን ሊሆኑ ይችላሉ? እካላቸው ሣይፈርስ እንደሚቆዩ አስከሬኖች ደርቀው ይገኙ ይሆን? ወይስ ደግሞ በዚህ የሩዝ ዱቄት በሞላው አየር ውስጥ ብቻ ነው መተንፈስ የሚችሉት። እናም፣ አንድ ሰው ለመደሰት ሲፈልግ ተመሣሣይ ጊዜያትን መከተል፣ በተመሣሣይ አካባቢ መንቀሳቀስንና ተመሣሣይ ባህርያትን ማሣየት ይኖርበታል። እስቲ ሁሉንም ተመልከቷቸው።

ጆን ባፕቲስት፣ ትንሽ ብልግና በተቀላቀለበት ሁኔታ፣ የሣያ እሙቶቹ የሠራዊት አለቆችንና፣ ስገባው ውስጥ ያልገባ ጐራዴ የሚያስደነግጣቸውን ጨዋዎቹን ጳጳሳት ቃኛቸው። የሰው ልጅ ልብ፤ እምነቱና የመሣሪያ አጠቃቀም ዝናውም ተገርቷል። ይሁን እንጂ፣ እነዚህ



ሁሉ ደስታዎች ምርኩዛ ያደርጋሉ እንጂ ምንም ማለት አይደሉም፣ ሲል ለራሱ ተናገረ። ይህን እያውጠነጠነ ሣለ ሁለት ወጣት ቆንጆጅት በአጠገቡ እያለፉ ዐይኖቻቸውን ቢወረውሩበት ውስጡ ተረበሸበት።

በሣሣብ ጭልጥ ብሎ መንዙን የተረዱት ሣንግራይ አጠገቡ መጥተው ተቀመጡ።

«እሺ ወዳጄ፣ የምሥራች። አንተን በሚመለከት ከሁሉም አቅጣጫ ድንቅ መረጃዎች ደርሰውኛል። እዚህም ይገፍህ ስለመጣሁ ምስጋናው ለእኔም ተርፎኛል»

«ይቀልዱብኛል አይደል? እኔ ደግሞ የተነሳቢጦሽ ተንገላጅጃለሁ።»

ስላልታደለው የበሬ ታሪክ ያወራላቸውንና ሁሉም አድማጮቹ ትተውት መሄዳቸውን አከሉ ነገሯቸው።

«እርሱን እርሣው። እርባና የሌለው ነገር ነው። ይልቁንስ በእቃ ማስቀመጫ ውስጥ ድንገት የተገኘ ዕቃ ላይ ለመሻማት የሚተራመሱ እስኪመስሉ ነበር ወይዛዝርቱን ያደረግሃቸውና፣ ከሚጠበቀው በላይ ነበር የሠራኸው። እስካሁን ድረስ ይህን የምትነግረኝን ሁሉ ረስተውት፣ በልባቸው ያለው፣ ደስ የሚል ሰው ማግኘታቸው ብቻ ነው»

የሳንግራይን ንግግር ለማረጋገጥ ይመስል፣ ጥቂት ወይዛዝርትና ብዙ የማርኩስ ወጣት እሻቢዎች በአጠገባቸው ሲያልፉ ሞቅ ያለ ፈገግታ ወደነርሱ አቅጣጫ ለቀቁ።

«በነገራችን ላይ፣ ካንተ ጉዳይ ጋር የተያያዘ ወሬ ሰምቻለሁ። ወጣቱ የስፔይን ንጉሥ ነገ ወደ ቬርሣይለስ ይሄዳሉ። ንጉሠ ነገስታችን፣ እንደ ቤተመንግስት ሕግ አውጭና አስፈፃሚ መሆናቸው ከእንግዲህ አብቅቷል። ስለዚህም አሁን ተከታዮቻቸውን መቀበል ይጀምራሉና ያንተም ረዥም ጊዜ አይወስድም» አሉት፣ ጠቢቃው።

በእንግዳ መቀበያ ክፍሎች ሁሉ ውስጥ ገበጣና የመጫወቻ ጠጠሮች ባሉባቸው ጠረጴዛዎች ዙሪያ እንግዶች እጅብ ብለዋል። ጆን ባፕቲስትና ሣንግራይ፣ አስተናጋጃቸውን በተናጠል ካመሰገኗቸው በኋላ፣ ሹልክ ብለው ለመውጣት ዕድል አገኙ። ወደ ቤታቸውም በግልፅ ሠረገላ ተጓዙ። በመኝታ ክፍሎች ውስጥ ፍሪንቾይዝ የሚንተነተግ እሣት እንድዳላቸዋለች። ጆን ባፕቲስት፣ ልዕልቲቱ በዝባድ ሽቱ እጃቸው በወደጅነት ዓይን ተመልክተው የጨበጡትን የራሱን እምባር ማሰሪያ ወደፊቱ አስጠግቶ በማሽተት ወዲያውኑ ተኛ።

በማግስቱ፣ ራእል፣ ለጆን ባፕቲስት መልዕክት ይዞለት መጣ። መልዕክቱ፣ ከአባ ፕላንቴይን የተላከ ነው። ካህኑ፣ እስከአሁን ድረስ ጆን ባፕቲስት፣ ሴ ቢዩ ኖይር የሚኖር መስሏቸው በዚያ አድራሻ ነበር የፃፉለት። ሐኪሙ ግን በአሁኑ ጊዜ በአማካሪው ቤት የሚኖር መሆኑን እንዲያውቁ ማድረግ ሞኝነት ይሆናል በሚል አላስታወቃቸውም ነበር። የደብዳቤው መልዕክት እንዲህ ይላል።

*ተዘጋጅ። ተነገ ወዲያ ወደ ቬርሣይለስ እንሄዳለን። እኛ እንድንቀርብ ፕሮግራም የተያዘልን ረቡዕ ዕለት ከሰዓት በኋላ በአስር ሰዓት ላይ ነው ።*

*አባ ጂ ፕላንቴይን ሰኾ*

ከምሣ በኋላ፣ ጆን ባፕቲስት ስለአቀራረባቸው ጉዳይ በዝርዝር ለመወያየት፣ ወደ ሉዊስ ሌ ግራንዴ ትምህርት ቤት ሄደ።

ወደ ቤት ሲመለሱ በሎው ብሬ በኩል ዞሮ ሄደ። በጭምጭምታ እንደሚናፈሰው ከሆነ በቅርቡ የእንጆው መስፍን ተብለው ሹመት የተቀበሉት የስፖኙ ንጉሥ ፊሊፕ አምስተኛ ፈረሰኞች፣ በሚቀጥለው ቀን ለሚደረገው ደማቅ ሰልፍ በዚያ በኩል ልምምድ ያደርጋሉ። በመርከብ ማቆሚያው ስፍራ ላይ፣ ጆን ባፕቲስት፣ የንጉሡን አንደኛና ሁለተኛ ፈረስ አጣቢዎች ውብ ልብሣቸውን ለብሰውና ሽክ ብለው በድንገት አያቸው። እነርሱን ተከትለው ሃያ አራት ረድፍ የሚሆኑ ከሃር የተሠራ ጠባቃ ጃኬትና የእግር ሹራብ የለበሱ፣ በብርማ ጌጥ ተሠርተው የሚያብለጨልፖ ተንጠልጣይ አበባዎችን ያሠሩ፣የአንገት ፎጣዎችን የጠመጠሙ ፈረሰኞች፣ የአበባ ጉንጉን በተደረገላቸው ፈረሶች ላይ ተቀምጠዋል። እነዚህን ተከትለው በእጅ የሚጉተቱ አሥራ ሁለት የስፔይን ፈረሶች አሉ። እነዚህኞቹ፣ የሰውነታቸውን ውበትና የጋማቸውን መዘናፈል፣ የተሸለሟቸው የወርቅ ልብሶች፣ በማዕከላዊው የሰውነታቸው ክፍሎች ላይ የተበጃጁላቸው ጌጣጌጦችን፣እርካቦቻቸውን፣ በወርቅና በብር የተጠለፉትን ግላሶቻቸውን ለማሣየት የወጡ ናቸው። ጆን ባፕቲስት፣ ከዚህ የበለጠ ሊመለከት አልቻለም። ምክንያቱም፣ ግራጫ ልብስ የለበሱና መስኬቶ ጠመንጃቸውን የያዙ ወታደሮች፣ የጎን ሰዎች ወደ ሎውብሬ ቤተመንግስት በጣም እንዳይቀርቡ ይከላከሉ ነበር።

ወደ አማካሪው ቤት ተመልሶ ሲመጣ፣ እኒህ አስተናጋጁ፣ ሣሎኑ ውስጥ እሣቱ አጠገብ ተቀመጠው አገኛቸው። ጆን ባፕቲስትም እጆቹን ወደ ሙቀቱ እያቀረበ እዚያው ተቀመጠ። ጊዜው ከምሽቱ ሶስት ሰዓት ሆኗል። ፍራንቾይዝ፣ እራታቸውን በዚያው በእሣቱ ዳር



አቀረበችላቸው። ስለ ቤተመንግስቱ ሰልፍና ፖንሴን ስለሚጠብቀው የቤተመንግስት አዳማቂ አወሩ።

«ለመሆኑ ምን ለማድረግ አቅደሃል?»

«መቼም እውነቱን እናገራለሁ» አለ ጆን ባፕቲስት በቀላሉ።

«ይህማ ደካማ አጀማመር ሊሆን ነው። ለንጉስ እኮ እውነት ማለት በቀላሉ እርሱ ሊሰማው የሚወደውን መንገር ማለት እኮ ነው። ታዲያ ይህን አታውቅም ማለት ነው?»

«ንጉሡ ሊሰሙት የሚወዱትና የሚያስደስታቸው ምን እንደሆነ አላውቅም። ነገር ግን ጥቂቶች ምን ሊነግሯቸው እንደሚፈልጉ አውቃለሁ። ያ ደግሞ ሐሰት ነው»

«ይህን ስትል ማንን እየጠቀስክ ነው?»

«ጀስዊቶችን»

«ይህን፣ ወደ ቤተመንግስት መቅረብህን ያዘጋጁልህ ጀስዊቶች አይደሉም እንዴ?»

«እነርሱ ናቸው። ነገር ግን ይህ ማለት እነርሱና እኔ፣ ለንጉሡ በምንነግራቸው ጉዳይ ላይ የተለያየ አመለካከት ያለን መሆኑን አያግደውም»

አማካሪው፣ በጣቶቻቸው ይዘው ሲቆረጥሟት የነበረችውን ትንሽ አጥንት ትሪው ላይ አስቀመጡና ከሚያብረቀርቀው ወይን በረጅሙ ተጎንጭተው፣ ጆን ባፕቲስትን በአግራሞት ተመለከቱት።

«ጀስዊቶቹን የሚቃረን ነገር በንጉሡ ፊት ለማቅረብ ማቀድህን ነው የምትነግረኝ? መቼም የመጨረሻችን ይሆናል ብዬ ስለምፈራ እራት አብሬህ መብላት በመቻሌ ደስ ብሎኛል። ነገር ግን በትክክል ፍላጐትህና ግብህ ምንድን ነው?»

«እርግጠኛ ንገረኝ ካሉኝ ሁለት ናቸው»

«ይህ ጥሩ አቋም አይደለም።»

«ይሁን እንጂ በኔ አዕምሮ ውስጥ ሁለቱ አንድ ነገር ይሆናሉ»

ፖንሴ፣ በንግግሩ ሞቅ እያለ ቀጠለ□ «ንጉሡ፣ ወደ አቢሲኒያ አምባሣደራቸው አድርገው ሾመው እንዲልኩኝ፣ ይህን ሃላፊነት ለመወጣት ማንኛውንም የአጋጣሚ መብት ሳይቀር እንድጠቀም እንዲሰጡኝና የመኳንንትነት ማዕረግም እንዲያጐናፅፉኝ እፈልጋለሁ»

«እነጋገርህ በጣም የምኞታም ቢሆንም፣ አይደረግም ሊባል እንኳ የሚችል አይደለም»

«እርስዎም ታይቶዎታል»

«ይሁን እንጂ፣ ለምንድን ነው ወደዚያ ተመልሰህ መሄድ የምትፈልገው?»

«ለመሄድ እንኳ በጣም ቁርጠኛ ከመሆኔ የተነሣ አይደለም። ነገር ግን፣ ንጉሡ እነዚህን ሁሉ ሊሰጡኝ ፍላጐቱ ካላቸው፣ የፈፀምኳቸውን ሁለት ቃልኪዳኖችን ሳሟላ እንድችል ዕድል አገኛለሁ።»

«ደጉ ክርስቶስ! ለማን ነው ቃል የገባኸው?»

«የመጀመሪያው ለአንዲት ወጣት ሴት ነው። በዘርዋ ከኔ ይልቅ ከፍተኛ ማዕረግ ካላቸው የምትወለድ ነች። ላገባት ቃል ኪዳን ገብቼላታለሁ። ይህን ማድረግ የምችለው ደግሞ፣ ንጉሡ የመኳንንት አባል ሲያደርጉኝ ብቻ ነው»

«ይገባኛል። እንዲህ ያሉ ነገሮችን ባንተ ዕድሜ የሚገኝ ሰው የሚያደርጋቸው ናቸው። እሺ፣ ሌላው ቃል ኪዳንስ?»

«ሌላው ቃልኪዳን፣ ለአቢሲኒያው ንጉሠ ነገስት የገባሁላቸው ነው። ለንጉሠ ነገስቱ፣ ጀስዊቶች ወደ አገራቸው እንደማይመለሱና፣ እርሣቸው፣ ፈረንሣይ አምባሣደር እንድትልክ የሚጠይቁ ከሆነ ቦታውን እኔው ተሹሜበት እንደምመለስ ምዬላቸዋለሁ።»

«ይህ ማለት የምትጠይቀው ወደዚያው እንድትላክና ጀስዊቶች የማይወደዱ መሆናቸውን ንጉሡ እንዲረዱት ማድረግ ነው። የሚገርመው እስከዚህ ድረስ ያመጡህ ግን ጀስዊቶች መሆናቸው ነው»

«ሌላ አማራጭ አልነበረኝም። ያለነርሱ፣ ለዘለዓለም ከካይሮ አልፍ እንኳ ማለት አልችልም ነበር»

«እኔም የምነግርህ ይህንኑ እኮ ነው»

«ቢሆንም እነርሱ ስለዕቅዱ የሚያውቁት ነገር የለም»

«ልቀበለው እችላለሁ። ማለትም በመጨረሻም ሰዓት ላይ በንጉሡ ፊት ትቀርባቸዋለህ። ምን ልታደርግ እንደሚገባህስ አስበህበታል? ደግሞ ትስቃለህ እንዴ?»

«የምስቅበት ምክንያትማ፣ ካለኝ ማስረጃ ባሻገር ልበ ሙሉነት ይሰማኛል»



«እንዲህ ግልብልብ የሚያደርግህ ወጣትነትህ ነው። የቤተመንግስቱ ግቢ የሴራ ቦታ ነው። ትንሿ ነገር በወኔና በጀግንነት የምትቀጣጠልበት ነው። ስለዚህ፣ አንዳችም ነገር እንዲህ በቀላሉ ድል የሚደረግበት ቦታ አይደለም። አንደኛ ብዛት አላቸው። ከየተሸጐጡበት ሆነው ከኋላህ ይወጉሃል። ያን ጊዜም ያሸንፉሃል»

«በጭራሽ፣ ክቡር አማካሪ» አለ ጆን ባፕቲስት በጨዋነት «ራሴን እብድ ነኝ ብዬ አላስብም። ልበ ሙሉነቴ የሚመነጨው ግዴለሽ በመሆን ሳይሆን፣ ይልቁንም በተቃራኒው ካየሁት ሁሉ የሚነሣ ነው። ይህን የት እንዳየሁት ያውቃሉ? ፈረስ እየጋለብኩ ወደ ፖሪስ ስመጣ፣ በንጉሡ ግዛቶች አቋርጬ ስንዝ፣በገጠርና በከተማ ውስጥ ያሉ ሰዎችን ሳነጋግር ነው። ይህን ሁሉ አገር የሚገዙት ሰው ታላቅ ንጉሥ ናቸው» እያልኩ ለራሴ አወራ ነበር።

«ይመስልሃል?»

«ቆይ፣ አይደለም። ሰውዬው ታላቅ ንጉሥ ናቸው። ምክንያቱም በዚህ አገር እኖር በነበረበት ዘመን፣ ስለፍሮንዴ ይነገሩ የነበሩትን የጥንት አፈታሪኮች፣ ስለ አስፈሪው የሕዝብ ሁከት፣ ስለ ሃይማኖት ጦርነቶች፣ ደርሶ ስለነበረው ስለታላቁ የወረርሽኝና የረሃብ መቅሰፍት የሰማኋቸውን አስታውሣቸዋለሁ። እናም በአባቶቻቸውና በአያቶቻቸው አልጋ የተተኩት እኒህ ንጉስ ይህን ሁሉ መከራ ከፍፃሜ አድርሰዋል። ታላላቆቹን ሁሉ አሸንፈው፣ መኳንንቱም እጅ እንዲሰጡ አድርገዋቸዋል። መኳንንቱ፣ ወደ ቤተመንግስት ግቢ በመምጣታቸው የተነሣ በአገር ቤት የነበሯቸው ታላላቆቹ ግንቦቻቸው ዛሬ አና ናቸው። በዚህ ሳቢያ፣ በአገር ቤት የቀሩት ሁሉ የንጉሡ ታማኞች ናቸው። ቤተክርስቲያንን በተመለከተ ከሆነ እርሷም ፕሮቴስታንቶችን በምትዋጋበት ጊዜ፣ ንጉሡ ስላደረጉላት ድጋፍ ውለታ ስትል ሥልጣናቸውን አሜን ብላ ተቀብላለች። ንጉሡ፣ የፈረንሣይን ወታደራዊ ሃይል አጠናክረዋል። በውጭ አገር የሚገኙ ጠላቶቻቸውንም ድል አድርገው መልሰዋቸዋል። በነዚህ ሁሉ ምክንያቶች ወደር የለሹን ስልጣንና ሃይል በእጃቸው አስገብተዋል»

«እነዚህ ሁሉ ያስከፈሉትን ዋጋ አትረሣም አይደል? የአውሮፖ ህብረት የተፈፀመው የኛን ተቃውሞ ጥሶ ነው። ሕዝቡ በግብር ጫና ተደቆሰ። ፕሮቴስታንቶችና ጃንሴናውያን እንደተባይ ነበረ የታደኑት። እኔ በፖርላማ ውስጥ ሰላሣ ዓመት ነበር የቆየሁት። እናም በፖለቲካ ውስጥ ከንጉሡ ከራሳቸው በስተቀር የሌሎች ድምፅ አይሰማም። ይህን ደግሞ እመነኝ።»

«ነጥቡ እሱ አይደለም» ሲል የጨዋታውን መስመር ለመቆጣጠር በመፈለግ፣ ጆን ባፕቲስት እጁን አወዛውዞ ቀጠለ። «አሁን እያደረግሁት ያለሁት፣ ታሪካዊ ፍርድ እየሰጠሁ አይደለም። የገለፅኩት ታላቅ ንጉሥ መሆን ፈልገው፣ መሆን የተቻላቸውን ሰው ሥራ ነው። እናም እንዲህ ያለ ሌላ ሰው ደግሞ የአቢሲኒያው ንጉሥ ነው»

«እያወዳደርክ እንዳይሆን . . . »

«አዎን። አንድ አይነት ፍላጐት አላቸው። ሁሉንም በስልጣናቸው ሥር ለማድረግ አንድ አይነት ቁርጠኝነት አሏቸው። አንድ አይነት ወደር የለሽ ሥልጣንና ሃይል እዚያም አይቻለሁ። እያሱ፣ የሚያከናውኑት ተመሣሣዩን ተግባር ነበር። በዚህ ዓለም ላይ ሁለት ሰዎች ኖረው አንዱ ሌላውን መረዳት ይችላል ከተባለ እነዚህ ሁለት ሰዎች ይሆናሉ።»

«እናም ለፈረንሣይ ንጉስ በዚህ ዓይነት ስሜት ልትናገር ነው የምታስበው?»

«እንደሚረዱኝ በጣም እርግጠኛ ነኝ። ጀስዊቶች ሊነግሯቸው የሚችሉት 'አቢሲኒያውያን ወደ ካቶሊክ እምነት ሊቀየሩ ይፈልጋሉ' ብለው ነው። እኔ የምነግራቸው ደግሞ፣ ግርማዊ ሆይ የምስራቁን ታላቅ ንጉስ ወዳጅነት ይቀበሉ። ወደርሣቸውም ዘንድ ኤምባሲ ይላኩ። ከርሣቸውም ጋር ይነግዱ። ወርቃቸውን ይግዙ። በርስዎ በኩል የፋብሪካ ውጤቶችዎን ይሸጡላቸው። ነገር ግን፣ ግርማዊ ሆይ፣ የአገራቸውን አቋም፣ሃይማኖት በመለወጥ ፍላጐት ለማወክ ፍላጐት አይደርብዎ። ልክ እርስዎ በዚህ መልክ የራስዎ መንግስት አቋም እንዲታወክ እንደማይፈቅዱ ሁሉ፣ የአቢሲኒያውንም አይንኩ»

«ጆን ባፕቲስት፣አንተ እብድ ሰው ነህ» አሉት ሣንግራይ፣ ከተቀመጡበት እየተነሱ። «ለራስህ ባዘጋጀኸው እንዲህ ባለ ወጥመድ ውስጥ ገብተህ እንዳትወድቅ ኀደኝነታችን ያሳስበኛል»

በክፍሉ ውስጥ ሁለት ረገጥ፣ም ርምጃዎችን ተራመዱና ተመልሰው ወደ እሣት ማንደጃው በመፃጣት ከዶክተሩ ፊት ለፊት ቆሙ።

«ፖንሴ፣ ለመሆኑ አቢሲኒያ ምንድነው?»

«አገር ነው»



«የለም። አቢሲኒያ ምንም ነገር አይደለም። ይልቁንስ በአፍሪካ ቀንድ ዳርቻ ያልሰለጠኑ አረማውያን ያሉበት ነው። ምንም ነገር አይደለም። ትሰማኛለህ? እና ፈረንሣይ ማለትስ ምንድ ነው? ፈረንሣይ ማለት ሁሉም ነገር ነው»

«ይህ በርስዎ አስተሣሰብ ነው፣ ክቡር አማካሪ? ስለአቢሲኒያ ብዙ ጉዳዮችን ሰምተዋል። ነገር ግን በአኳያው ደግሞ ስለነርሱ እንድፅፍ የገፋፉኝና የነገሩኝ እርስዎ ሲሆኑ፣ በሁለት የተለያዩ አገሮች ባህሎች መካከል ንፅፅር ይጀምራሉ። ገና ከመታወቃቸው በፊትም ይፈርጇቸዋል።»

«እንድትፅፍ፣ አዎን ነግሬሃለሁ። ነገር ግን ስለነርሱ እንድትናገር አላልኩም። ይባስ ብሎም በርግጠኝነት ስለነርሱ ለንጉሡ እንድትነግራቸው አላልኩም። የኔ እምነት የሚገባቸውና የሚሰማቸው ሰዎች ጥቂቶች ናቸው። ለዚህም ስል ነው ሃሣቤን በታላቁ የፅሁፍ ጅረት ውስጥ እንዲፈስስ የምሻው። ይህን በማድረጌም ምናልባት አንድ ቀን አንድ እንደእኔው የሚያስብና መስማትም የሚፈልግ ሌላ ሰው በራስ መተማመንና ወኔ ኖሮት፣ ይህን አስቸጋሪና አስፈሪ ነገር ይፋ ያደርገው ይሆናል። አሁን ግን ማናችንም ልናረጋግጥ የሚገባን፣ሁሉም ሰዎች የሚያስቡትን ነው። ሁሉም ሰዎች የሚያስቡት ደግሞ ንጉሡ የሚያስቡትን ነው። ንጉሡ፣ ሃያል መሆናቸውን በሕይወታቸው ውስጥ የሚያስቡት ከሌሎች ጋር በማወዳደር አይደለም። በርግጥም ደግሞ እርሣቸው ሥልጣኔ ፈፅሞ አልደረሰባቸውም ከሚሏቸው ሰዎች ጋር ራሣቸውን እንዲወዳደሩም አይፈቅዱም። ፖንሴ፣ በወዳጅነታችን አምላክ፣ ላንተ ያለኝ ፍቅር፣ አባት ለልጁ ያለውን ፍቅር ዓይነት ነው። እናም በንጉሡ ፊት ስትቀርብ፣ በርሣቸው ሥልጣንና በአንድ ተራ የአገሬው ተወላጅ መስፍን መካከል፣ ሌላው ቀርቶ ክርስቲያን እንኳ ቢሆን፣ አንዳች የሆነ ማወዳደር ብታደርግ እንደስድብ ወንጀል ይቆጠርብሃል። በዚህም የተነሣ የምትፈልገውን ነገር ወዲያውኑ በቅጣት ካሣ መልክ፣ ሌላው ቀርቶ ከዚህ አገር በነፃነት መውጣትንም እንድታጣ ትደረጋለህ።»

ወዳጁ በሃቀኝነትና በታማኝነት አጠንክረው በነገሩት ማስጠንቀቂያ፣ ጆን ባፕቲስት መብረቅ የመታው ያህል ሆነ።

«እንግዲያውስ ምን ማድረግ አለብኝ» ሲል እየከፋው ጠየቃቸው።

«ሃሣብህን በፅሁፍ አስፍረው። እኔ እስከአሁን አጥብቄ እየሠራሁ ነኝ። ጽፈህ ስትጨርስ እንዴት እንደምናሣትመውና ለየትኞቹ እርቆ ተመልካች ግለሰቦች እንደምናሣይ የራሣችንን

ሥራ እንሰራለን። አሁን ለጊዜው ግን በንጉሡ ፊት በጀስዊቶቹ ላይ አንዳችም የተቃውሞ ነገር እንዳታሰማ። ምንም የሚያግዳቸው ነገር ሊኖር ባይችልም፣ ጉዟቸው ሊያጋጥመው የሚችለውን አደጋና ችግር አጋንነህ ታቀርብባቸው ይሆናል። እነርሱ በራሣቸው አነጋገር፣ ንጉሡ ሃይማኖታቸውን መለወጥ ይፈልጋሉ ካሉም አትቃወማቸው። እንዲያውም፣ እንዳላቸሁ ብለህ ተቀበላቸው። ለንጉሡ አስተሣሰብ ካልተሸነፍክ በስተቀር፣ ከርሣቸው አንዳችም ድጋፍ አገኛለሁ ብለህ አትገምት። መኳንንት መሆን ትፈልጋለህ? ይህ ሙሉ በሙሉ ሊሆን የሚችል ስለሆነ እኔ ልረዳህ እችላለሁ። ነገር ግን አስቀድመህ ሰዎችን ማስደሰትን ማወቅ ይኖርብሃል። ለንጉሡ ታማኝነትህን አረጋግጥላቸው። የርሣቸውን ታላቅነት እስከ መሬት ዳርቻ፣ እስከምስራቅ አገር ነገስታት ዘንድ ዜናቸውን ማሠራጨትህንና ማስደንገጥህን ንገራቸው። ይህን የሰሙት ሁሉ ዝቅ ብለው አክብሮታቸውን ያቀረቡ መሆናቸውን ንገራቸው። እውነተኛው እምነት ግን፣ ለርሣቸው ምስጋና ይግባቸውና ይህንኑ ማበልፀግ ሲቻል መሆኑን አስረዳቸው። እናም ወደዚያ አገር አንድ ጀስዊት ይዘህ ሄደህ እንደነበረና የእግዚአብሔር ፈቃድ ሳይሆን ቀርቶ ካህኑ በመንገድ ላይ ማረፋቸውን፣ አሁን ግን ሌሎች ብዙዎችን መርተህ ለመውሰድ ተስፋ እንዳለህ ንገራቸው»

«ወደዚያ አገር ሌሎች ብዙዎችን መርቼ ልሄድ?» ሲል ጆን ባፕቲስት ተቆጣ። «እነዚህ ሰዎች ለዘለዓለም ተመልሰው እንዳይመጡ አደርጋቸዋለሁ ብዬ ለንጉሡ ነገስቱ ቃል ገብቼላቸዋለሁ።»

«ለቃል ኪዳን ክብርህ ልጓም አብጅለት፣ ወጣቱ ወዳጄ። ጀስዊቶች፣ እምነታቸውን የሚከተል እጅግ ታላቅ የክርስቲያን ግዛት ንጉሥ እያላቸው፣ ብቻህን በነርሱ ላይ አንዳችም የማገጃ ግድግዳ መሥራት አትችልም። ይህ ቃል ኪዳንህ በጣም መጥፎ ነው። በአሁኑ ጊዜ የጠራ ክብር በሚባለው ዘመን ውስጥ አይደለንም። አንዳንዶች ይህ በመቅረቱ ያዝኑ ይሆናል። ከዚያ ታች ያሉት ባዶ ግርግምና ባዶ የእንጨት ገንዳዎችን አይተሃቸዋል? ለለምንህና፣ ስለምንኖርበት ዘመን ሣታውቅ አትሣሣት»

ጆን ባፕቲስት ወደ እሣቱ አቅጣጫ ተሽከረከረና ክንዶቹን አመሣቀላቸው

«እስቲ እናያለና» ሲል በጥርሶቹ መሃል ተናገረ።



# 6

በዚህ ሁሉ መሃል፣ ሙሴ ሌ ኖይር ዱ ሮውሌ፣ ካይሮ ውስጥ ብቅ ሊል አልቻለም። ቆንሲሉ፣ ሌላ የመርከብ መስመጥ ደርሶ እንደሆነ በሚል ፈራ። በአንድ የዛፍ ግንድ ላይ ተጣብቀው እንደቀሩት እንደ አባ ቬርሣው፣ የወደፊቱ አማቹም በአንድ የባህር ዳርቻ ውሃው ተፍቶት ይሆናል። እውነታው ይህን ያህል የሚያሳዝን አይደለም። ወጣቱ ዲፕሎማት በጉዞው ላይ ጊዜውን እየተዝናናበት ነው። ሌ ቪታቬቺያ ውስጥ ሰንብቶ፣ ወደሮም በሠረገላ ተጉዞ፣ ከተማዋንም እስኪደሰትባት ጐብኝቶ፣ በሮማውያን ማህበረሰብ ውስጥ ከአንድ ወይም ሁለት ሴቶች ጋር ግንኙነት ፈጥሮ ቆይቷል። ከዚያም ወደባሪ በመሄድ ወደ ኮሪንዝ ተሻግሯል። በመጨረሻም አሌክሣንደሪያ ውስጥ ከታየ በኋላ ብዙም ሣይቆይ ካይሮ ደርሷል።

ምንም እንኳ ዱ ሮውሌ የበታቹ ቢሆንም፣ በቆንስላው ውስጥ እንዲሰነብት ለማድረግ ሙሴ ዴ ማይሌ ወስኗል። ደረጃውንም እንደጨዋ ሰው ለማክበርና ይበልጥም የቤተሰቡ አካል አድርጐ እንዲሰማው ለማድረግ ፈልጓል። የልጁን የእሽታ ቃል በማግኘቱ እፎይታ የተሰማው ቆንሲል፣ የእጮኛዋን ሃሣብ ለማወቅ ጓጓ። አሊስን የምትፈቅር ሆና ያገኛት ይሆን? ቆንሲሉ፣ ለልጁ ልቡ እስኪጠፋ ድረስ ፍቅር ያለው አባት አይነት አልነበረም። ልጁን የሚፈርጃትም በአቋሟ ሣይሆን ተቀባይነት ባለው ልማድ መሠረት ስለሆነ፣ ያስፈልጋታል ሲል ገመተ። በትዕዛዙ መሠረት ባለፈው ሣምንት ከጊዛ አልተመለሰችም። ስለዚህም በፀሐይ ምክንያት ፊትዋ ይጠቁራል። የትም ቦታ በባዶ እግሯ ስለምትጓዝ ያልሰለጠነች ሴት ትመስላለች። የተለሣለሰ ፍላጐት ያለውና የፖሪስ የውበት አዳራሾችን የለመደ ሰው እንዲህች ካለች ሴት ጋር ለድርድር መቅረብ አይፈልግም ይሆናል።

ዱ ሮውሌ በመጣበት ዕለትና ሻንጣ ወደ ግቢው በሚገባበት ጊዜ፣ አሊስ በአዳራሹ መግቢያ ላይ ብቅ ብላ ስለነበረ፣ ልብሷን እንድትለውጥ ወደ ፎቅ መልሶ ለመላክ እንኳ በጣም የዘገየ ነበር። ሙሴ ዴ ማይሌ፣ ጉንጮችዋ ምንም መጋጊያጪያ እንዳልተደረገባቸውና ፀጉርዋም እንደ ዝቅተኛዋ የቤት አገልጋይ ወደ ኋላዋ ተንጨፋርሮ መውረዱን በድንጋጤ አስተዋለ። ለርስዋ በጣም ትልቅ የሚሆንባትን የእናትዋን ቀሚስ ለብሳለች። ልብሱ አስቂኝ መሆኑ ብቻ ሣይሆን፣ የተቀዳደደና ጥቁር ቡኒ ቀለሙም፣ ካይሮ ውስጥ እንኳ ከአስራ አምስት አመት በፊት የቀረ ፋሽን ነው። በቆንስላው ውስጥ የነበሩት አገልጋዮች በሙሉ በአዳራሹ

መግቢያ ላይ ከማይሴዎች ኋላ ተሰልፈው ቆመው ስለነበረ በዚህ ሁሉ ሰው ፊት ለመገርመም አስቸጋሪ ነበር። ከዚህም ባሻገር፣ እንግዳ ደራሹ የሠረገላውን በር እየከፈተና አንድ አረባዊ አግረኛ ተከታይ መውረጃውን እያዘጋጀለት ነበር። ቆንሲሉ፣ ደረጃውን ጠብቆ መድረኩ ድረስ ሊቆይ አቀደ። ይህ የፕሮቶኮል ጉዳይ ስለሆነ ባለፈው ምሽት ከሙሴ ማቼ ጋር ተነጋግሮበታል። ይሁን እንጂ በወቅቱ በነበረው ሙቀት ተቻኩሉ ደረጃዎቹን በመውረድ እንግዳውን ከሰረገላው ግርጌ ቀርቦ ሰላምታ ሰጠው።

ሙሴ ሌ ኖይር ዱ ሮውሌ፣ ረዥምና ጥሩ ቁመና፣ ሸንቀጥ ያለ ወገብና ቀጥ ያሉ እግሮች ያሉት ነው። ይህ ቁመናው የሚያሳድረውን ተፅዕኖ በሚገባ ስለሚያውቅ፣ በዚያው ሁኔታ መውረዱ በግልፅ ያስታውቅ ነበር። ቀጥሎ ሊያገኘው የሚችለው ጠቀሜታ ካልታየው በስተቀር ፣ክንዶቹን ንቅንቅ አያደርግም። በተቻለው መጠን ተፈጥሮአዊ ሞገስን ጠብቋል። አንገቱን አቅንቷል፣ ተረከዞቹን እኩል ወጥሯቸዋል፣ ትከሻውን አስተካክሏል። ሲያዩት እጥፍ ዘርጋ የሚል ሰው ይመስላል። እንዲያውም የዳንሰኛ ቅርፅ ያለው ያስመስለዋል። ነገር ግን በውስጡ አንዳችም ሃይል የሌለውና ጭራውን የሚቆላ፣ በትልቁ ቁመናው ትልቅ ጭካኔውን የደበቀ፣ ትልቅ አዳኝ አውሬ ይመስላል።

አሊስ ፊቱን ስትመለከተው ተንቀጠቀጠች። ፊቱ እንደምላጭ ስል ነው። ጠባብ ቀዳዳዎች ያሉት ረጅሙ አፍንጫው፣ በወፍራሙ ከተጣጠፈው ግንባሩ ሥር ይነሣል። ጉንጮቹ የሰረጉዱ ናቸው። ከንፈሮቹ ስስ መስመር ሲመስሉ አገጯ ሹል ነው። ቆንሲሉ እያቀረበለት ለነበረው ትህትና የተመላ አቀባበል ምላሹን እየሠጠ፣ ሌ ኖይር ዱ ሮውሌ አይኖቹን ሆን ብሎ በተሰበሰቡት ተቀባዮቹ ላይ ወረወረ። አንደኛው የአይን ሽፋሽፍቱ፣ ወገቡ ላይ የተሰበረ ደጋን መስሎ በስላች ይታያል። ከሌሎች ሰዎች ሁሉ ሲረዝም፣ ቅንድቦቹ እንደ መጋረጃ ባሉበት ድርቅ ብለው ስለሚቆዩ፣ ጥቋቁር ዓይኖቹን ይከላከሉስታል። በዚያ ከነበሩት ሁሉ ይልቅ እዚያው የነበረችውን ወጣት ሴት አጥብቆ አተኩሮና ልብ ብሎ አስተውሏታል። እርስዋም ብትሆን፣ እንዲህ ካለ ሰው፣ ውበቷን ፈፅሞ በቀላሉ ቸለል ብላ ልትደብቅ እንደማትችል ወዲያውኑ አወቀች።

እንግዳ ደራሹ፣ በቤተመንግስት ወግ መሠረት ለወይዛዝርቱ ሰላምታ አቀረበላቸው። ይህ የሠላምታ አቀራረብ ለነርሱ እንግዳ ቢሆንም አዲሉ ባህል ይሆናል በሚል ሁሉም ተቀበሉት። ከዚያም፣ እንግዳው ከቆንሲሉና ከሙሴ ማቼ ጋር ወደ ሕንፃው ውስጥ ገቡ። ለጥቂት ጊዜ ከተነጋገሩ በኋላ መንገደኛው ወደተዘጋጀለት ክፍል ሄደ። ለዕራት ተመልሶ



ሲመጣ፣ ከቅድሙ ይልቅ በጣም ሽክ ብሎ ለብሶ መጣ። ረቂቅ ብሩህ ሰማያዊ መስመሮች ያሉበትና በወርቅ የተጠለፈ ሰማያዊ ሰማይ የመሰለ ከፋይ ኮትና ከሱሪው ጋር የሚመሳሰል ነጣ ያለ ሃምራዊ ሰደርያ ለብሷል። በእራት ክፍሉ ውስጥ እርሱን የሚመስል አልነበረም። እንግዳውም፣ አሁን በቅርቡ ከቬርሣይለስ የመጣ ተራ ሰው ለመምሰል ይጥራል። ሌሎቹ፣ ከሁሉም በላይ ቆንሲሉ፣ ያረጀ ቡትት የለበሰ ይመስላል። ከአባቷ በስተግራ የተቀመጠችው አሊስ፣ የሚማርክ ቀሚስ ለብሳለች። ቀደም ሲል እንደማሳሳቻ ለብሳው፣ አባቷን ያናደደውን አይነት ግን አልነበረም። በማንኛውም ሁኔታ ግን፣ የዚህን ሰው እይታ ከርሷ ላይ ሊነቅልላት የሚችል ነገር እንደሌለ ተሰምቷታል። አንድ ነብር፣ ጥቅጥቅ ባለ ደን ውስጥ ድኩላ ያለችበትን ቦታ መለየት እንደሚችል ሁሉ፣ ይህም ሰው ውበቷን በትክክል አውቋል። የሌ ኖይር ዱ ሮውሌ አስተሣሰብ የሚጠቁመው፣ እርሱ ለርሷ የመሆን መብት እንዳለው ሲሆን፣ እርስዋ ግን በዚህ ዓይነት አልገመተችም ነበር። ይሁንና፣ አባቷና ፖንቻርትሬይን ስለጋብቻው እቅድ ሳይነጋገሩበት እንዳልቀሩ አያጠራጥርም። እርሷም ይህንኑ ገምታለች። በራሱ ርግጠኛ የሆነ፣ በውበቱና በጮሌነቱ የሚተማመንና ምንም ይሁን ምን፣ ሌላው ቀርቶ በተገቢው መንገድ ከተሰጠችውም በታላቅ ደስታ፣ በተገቢው መንገድ ባትሰጠውም እንኳ ሊወስዳት እንደሚችል የሚያመለክት የባለጌ አተያይ አለው።

ሙሴ ሌ ኖይር ዱ ሮውሌ፣ በሚጥም ጨዋታው ገበታውን አደመቀው። የሥነ ጥበብ ሥራዎችን ያፈቅራል። ገና ያላያቸውን፣ ነገር ግን ብዙ የሚያውቁ ሰዎች የፃፏትን አንብቦ፣ ስለግብፃውያን ሃውልቶች አስረዳቸው። እንደሞተር እየተንጣጣ ስለሚናገር የፊቱ ገፅታ ከአንድ ዓይነት መልክ ወደ ሌላው ይለዋወጣል። የጊታር ተጫዋች የግራ እጅ፣ ከአንድ ክር ወደ ሌላው በፍጥነት ዘልሎ ሲንቀሣቀስ እንደማይታይ ሁሉ፣ በሚለዋወጠው የፊቱ ገፅታ መካከል ልዩነቱን ለመገንዘብ የለውጥ ሽግግር ጊዜ እንኳ የለውም። የአይኑ ሽፋኖች ብቻ አይንቀሣቀሱም። ፍራፍሬ በቀረበ ጊዜ ግን በቀጥታ ወደ አሊስ ተመለከተ።

«እናም አንቺስ ማዳሞዜል፣ ለመሆኑ ስፊኒክስን አይተሽው ታውቂያለሽ?»

«የለም» አለችው ቆጣ ብላ

ገና በቅርቡ ከጊዛ ተመልሳ መምጣቷን አባቷ ሊናገር ሲል፣ የቃለ አጋኖ ድምፅ ሰማ። አሊስ ከገበታው ብድግ ብላ ገና አንድ ርምጃ እንደተራመደች አቅሏን ስታ ወለሉ ላይ ወደቀች።

ማዳም ዴ ማይሌ፣ ደውላ የጠራቻቸው ፍራንቾይዝና አንዲት የወጥ ቤት ሠራተኛ፣ ወጣቷን ሴት ተሸክመዋት ወደ ክፍሏ ወሰዷት። ወላጆችዋ በጣም ግራ ተጋብተው ተከተሏት።

«አየሽ፣ እዚያ ቤት ውስጥ የትኩሣት ሕመም ሊይዛት እንደሚችል እርግጠኛ ነበርኩ።» አሳት ቆንሲሉ ለባለቤቱ፣ የፎቁን ደረጃ በመውጣት ላይ እያሉ።

«አታተኩስም» አለች ማዳም ዴ ማይሌ

«ተይው ግዴለም። ቀኑን ሙሉ ተቀምጣ በማረፍ ሃሣቧን ሁሉ በልብ ወለዶች ስታደስደንቅ ስለምትውል እንፋሎት እየወጣት ልታልቅ ተወስና ስለነበረ ነው»

ይህ በዚህ እንዳለ፣ በእንግዳ መቀበያው ክፍል ውስጥ፣ ሙሴ ማቼ የወጣቱን ዲፕሎማት ሃሣብ ለማዛባት ሲል አጋጣሚውን በይቅርታ እንዲያልፈው ይለምነው ጀመር።

«መቼም ተሳሳፊ አይደለም፣ ነው እንዴ?» ሲል አፍንጫውን በዳንቴል መሃረብ ውስጥ ቀብሮ ሌ ኖይር ዱ ሮውሌ ጠየቀ።

ጊዜው ወርሃ ታህሳስ ነበር፡ ቬርሣይለስ፣ አዲሱ ንጉስ ለቀዋት መሄዳቸውን ምክንያት በማድረግ ከተዘጋጀው ታላቅ ፌስታ በኋላ ከባድ ሃዘን አጥልቶባት ግዑዝ ሆናለች። መናፈሻዎች በቢጫ ቅጠሎች ተሞልተውና በጭጋግ ታጥረው ወደ ጭለማው ደን ውስጥ የተዘረጉ የማንጣፈፊያ በሮች መረብ ይመስላሉ። ጥቂት ቅዝቅዝ ያሉ ጥላዎች ይታያሉ። ጥቂት አትክልተኞች በአንድ ዛፍ ሥር ዙሪያ ወይም ሜዳውን ወደፊትና ወደ ኋላ እንደ አራሽ ሰው በመጥረግ ሥራ ተጠምደዋል። በቀላሉ በሚሰባበረው የቦረቦር ግራጫ ድንጋይ ጣሪያ ስር፣ ቤተመንግስቱ አሣዛኙን የፊት ለፊቱን ገፅታውን እርጥበት ወዳለው ነፋስ አቅጣጫ አሰግንል። በመስተዋት መስኮቶች ጀርባ ቀኑን ሙሉ ሲበሩ የሚውሉ የደካማ ፋናዎች ብርሃን ይታያል። ዋናውን አደባባይ ያቋረጠ ሠረገላ የለም። ነገር ግን የሠረገላውን ተሽከርካሪ ወጥሮ የሚይዘው የብረት ዘንግ በበሃ ድንጋይ ንጣፍ ላይ ሲንሳጫገጭ የሚፈጠረው ስቅጣጭ ድምፅ፣ አንድ የተጫነ ጋሪ ወደ ሰው መግደያው ቦታ እየሄደ እንደሆነ ያስታውቃል። ከየእንጨት አጥሩ በስተጀርባ፣ የሠራተኞች የእንጨት መደሻዎች ድምፅ ከማይታዩበት ሆነው ከአንድ ከፍተኛና ሰፊ የመውጣጫ መስመር ላይ ሲሰሩ ይሰማል።



ጆን ባፕቲስት፣ አባ ፕላንቴይንና አባ ፍሌኡሪአ፣ የቤተመንግስት ሹማምንት ከመሰብሰባቸው በፊት ሌሊቱን ገብተው ቬርሣይለስ ውስጥ በኢየሱስ ማህበረሰቦች በተሠራውና ወደ ራይን ወንዝ በሚያሣየው ቤት ምሽቱን አሣለፉ። በመጨረሻ ላይ፣ አባ ፍሌሃውት፣ ፓሪስ ውስጥ አልተቀላቀሏቸውም። እርሣቸው በቀጥታ በስብሰባው ቦታ ላይ እንደሚያገኟቸው ግን መልዕክት ትተዋል።

«ይህ ማለት እርሣቸው የሃይማኖት አባሎቻቸው አሉላቸው። በዚህም ላይ ፖንቻርትሬይንም ከጐኑ እንዲሆኑለት ይፈልጋል» አሉ አባ ፕላንቴይን።

ሌ ቢአው ኖይር ውስጥ፣ ጆን ባፕቲስት የለመደው የዶሮ አሮስቶ እራት ላይ በተከታታይ ቀረበ። እርሱ ግን የተከተፈ ጐመንና ንፁህ የአይብ ሾርባ ብቻ ተመገበ። ፍሌኡሪአ፣ እነዚህን አረንጓዴና የመነመኑ ነገሮች ተሰጥተውት ሲያመነኝካቸው ቆየና ሲጠግብ፣ ግብዣ ላይ የተመገበ ያህል ተደሰተ። በምድጃው ውስጥ፣ ነቀርሣ የመሰለ እሣት ለአጭር ጊዜ ቆየ። ፖንሴ፣ እራት የበላው ወፍራም ካባውን ለብሶ ነበር። ነገር ግን ጥርሶቹ ሁሉ ስለተንገጫገጮበት፣ አስቀድሞ በሚሞቀው መጥበሻ ቅዝቃዜውን እንዲሟሟ የማድረግ ጥንቃቄ ወስዶ ወደ መኝታው ሄዶ እንዲተኛ ጠየቀ። በመንቀጥቀጥ ውስጥ ፍፁም ሰጥሞ የያዘውን ሙቀት ከአንድ ጐኑ ወደ ሌላው በማሿሿር ለማቆየት ይችል እንዳሆነ ብቻ በማሰብ በበረዶ ውሃ ላይ እንደተጋደመ እንስሳ ደንዝዞ ተኛ።

ማለዳ፣ በሁለት ሰዓት ላይ፣ አንድ አጃቢ መጥቶ መጋረጃዎችን ሰበሰባቸው። እሣትም አነደደና ቁርስ እንዲበላ ካህናቱ እየጠበቁት መሆኑን ነገረው። ምግቡ እንደማታው ሁሉ የማያስደስት ነው። ከዚህም በላይ፣ በዚያን አይነት ሰዓት ላይ ለዶሮ ሾርባ ግድ የሌለው ፖንሴ፣ እየከፋውም ቢሆን በዚያ ቤት ውስጥ ሻይ፣ ቡና ወይም ቸኮሌት የሚባል ነገር እንደሌለ አወቀ። በአንድ ትልቅ ብርጭቆ ማልምሴይ እንዲሰጠው ጠይቆ፣ በአንድ ረኸርም ትንፋሽ ጨለጠው። በዚህ መሃል አባ ፍሌኡሪአ መታመማቸውንና በዚሁ ዕለት ቀኑን ሙሉ ተኝተው ስለሚውሉ ወደ ቤተመንግስቱ ስብሰባ አብረዋቸው ሊሄዱ እንደማይችሉ አባ ፕላንቴይን ገለፁ። ያመማቸው ምናልባት ከትናንት በስቲያ ማታ የበሉት በርከት ያለ እራት ውጤት ሳይሆን አይቀርም።

አራት ሰዓት ላይ፣ አባ ዴ ላ ቸይዝ የላኩላቸው ሠረገላ ሲሽከረከር በር ድረስ መጣ። የአየሩም ፀባይ ከባለፈው ቀን ይልቅ ይበልጥ ጠቆርቆር ያለ ሰማይ ይታይበታል። ቢጫ

አብረቅራቂ ያለበት ትልቅ ጥቁር ደመና፣ በረዶ ለመጣል እያንገርበበ ሲሆን ብርሃኑን ሁሉ ውጦታል:: በቤተመንግስቱ መግቢያ ግንብ የሚጠብቁት ስዊሳዊ ዘበኞች፣ ሦስት እጥፍ በሆነ ክት ተጠቅልለዋል:: በቤተመንግስቱ ጣሪያ ላይ የሚገኙት ጭስ ማውጫዎች ሁሉ ጢስ ቢትጉለጉልባቸውም፣ እነዚህ እንግዶች በቅጥር ግቢው ውስጥ ማንንም አላገኙም::

የአየሩ ጠባይ ለጆን ባፕቲስት ተስማምቶታል:: እንዲህ ባለ ውብ ቀን፣ አብረቅራቂ የወርቅ ቅቦችና ጌጣጌጦች፣ የመናፈሻ ስፍራዎች ህብር፣ የሕንፃዎች ሽብረቃ የድል ብስራታቸውን የሚጭኑበት ይሆኑ ነበር:: ቢሆንም፣ ይህ ጢስ የሞላው ዋሻ አንዳች ትህትና ያለው ይመስላል:: ንጉሡ፣ ያላቸው የሚመስላቸው ታላቅነት ሁሉ፣ እርሣቸውም ለወቅቶች ሃይል ተገዥ ስለሆኑ ራሣቸውንና በጉጆአቸው ውስጥ ያሉትን ነፍሳት ሁሉ ከዚህ ከሚለዋወጥ ባለጌ ዝናብና ቅዝቃዜ መከላከል ይኖርባቸዋል:: በክረምት የቆፈን እጅ ውስጥ ያለችው ቬርሣይለስ፣ ለደስታና ለፈንጠዝያ የምትሆን ሳትሆን፣ ዜጎችዋ ሁሉ ለዘብ ባለው እሣት ዙሪያ በተራ የድንጋይና የሸክላ መጠለያዎች ውስጥ፣ ክረምቱ እንዲያልፍ ጀርባቸውን አገብጠው የሚጠባበቁባት ከተማ ነች::

በታላቁ የእምነበረድ መውጣጫ ደረጃ በኩል ገቡ:: አድርጉ የተባሉትን ለማድረግ ፈቃደኞች የሆኑት ሰዎች፣ ቀለል ያለ ልዩ ልብስ ለብሰዋል:: እጆቻቸው በቅዝቃዜው ሰማያዊ ሆነውባቸዋል:: ትልቁና ረዥሙ የመወጣጫ ደረጃ፣ ሲራመዱበት የበረዶ ርጥበትና የሠምና የአስከሬን ሣጥን ሽታ ሲሸትት፣ ከበላዩ የታፈነ የገደል ማሚቶ ድምፅ ይመጣበታል:: ጉብኚ ዎቹ፣ ደረጃውን ጥብቅ በሆነ ሥርዓት ሽቅብ ይራመዱታል:: ከነርሱ መካከል አንድም እንኳ የወርቅ ቅብ የተቀባውንና የፅጌሬዳ ቅርፅ ያለውን የብረት መደገፊያ የደረሰ የለም:: ላይኛው ማረፊያ ላይ እንደ አጋጣሚ የሚያንሾካሹኩ አጃቢዎች አሉ:: የሚቀሰቅሣቸው ማንም ይሁን ማን፣ የጉብኚዎቹን መድረስ ግን፣ እንድም ያስተዋለው ያለ አይመስልም:: የመጨረሻውን ደረጃ ከወጡ በኋላ፣ ይህ ጥቂቶች ያሉበት ቡድን የሚቀጥለውን ደረጃ ሳያስቡት ሽቅብ ተመለከቱት:: አሁንም ገና በነርሱና በጣሪያው ኮርኒስ መካከል ብዙ ርቀት እየቀረ፣ የደረሱ የመሰላቸው ግራ የሚያጋባ ነው:: ልክ በዚህን ጊዜ፣ አባ ዴ ላ ቾይዝ እነርሱ ካስተዋሉት መጋረጃ ውጥተው ተቀላቀሏቸው:: የማይማርክ የካህን ልብስ ለብሰው፣ ከጥቁር አብረቅራቂ ሃር የተሠራ ቆብ በጭንቅላታቸው ላይ ደፍተዋል:: ሰውዬው ባለማቋረጥ ፈገግ ይላሉ:: የማይለዋወጠው የፊት ገፅታቸው በመጀመሪያ ላይ የስኬት ሁኔታ መስሏቸው ነበር:: በኋላ ላይ ግን ፍርሃት ለቀቀባቸው:: ከአኳኋናቸውና ከአግባ ንግግራቸው፣ ሰውዬው በነገሮች



የመጨረሻ ሰዓት ላይ ታላቅ መሆናቸውን ለማሣወቅ የሚጥሩ መሆናቸው ይታወቅባቸው ነበር:: ለንቋሳው ቁመናቸው ከታላቁ ሕንፃ አኳያ ሲታይ እንክትክት ማለታቸው የማይቀር መሆኑን ያጋልጥባቸዋል:: ፖንሴን በአይናቸው ቂጥ በፍርሃት ይመለከቱታል:: ከሠረገላው ውስጥ ገና የሚወርዱና የሚመጡ ሁለት ሣጥኖች መኖራቸውን አባ ፕላንቴይን ለፖንሴ ሲነግሩት፣ አባ ዴላ ቾይዝ ደግሞ ሁለት ምን ልታዘዝ የሚሉ ሰዎችን ጠሩ:: ወዲያውም ክስተርና ቁርጥ ያለ ምልክት ሰጧቸው:: ይህ ድርጊታቸው በሰውዬው ውጫዊ የርጋታ ሰውነት ስር ዘልቆ ያለውን ጥላቻና ወዳጅነት አስመፈለግን ያመለክታል:: አባ ፕላንቴይንን ወደ ዳር ወስደቸውና ወደ አንድ ትልቅ የጌጥ ቅርፅ ማውጫ በመዞር፣ በዝቅተኛ ድምፅ የሆነ ነገር ነገሯቸው::

የንጉሡን የንስሃ አባት ተከትለው፣ የዘቦች ወደ ሆነው ወደ መጀመሪያው ክፍል አመሩ:: አባ ዴ ላ ቾይዝ፣ የመስኬቶ ጠመንጃ ሳነገተው ተረኛ መኮንን ሁለት ሰዎች ተሸክመው የሚያመጡት ሣጥን አለ ብለው ሲነግሩት ሳጥኑም ወዲያውኑ ደረሰ::

በመቀጠልም ወደ መጀመሪያው የእንግዳ መቀበያ ክፍል ገቡ:: ይህ ሰፊ ክፍል፣ ንጉሱ በአብዛኛው እራት የሚበሉበት ነው:: የነሐሱ ግድግዳ ብርሃን ይተፋል:: መስኮቶቹ፣ በመስተዋቱ ውስጥ ምንም ባያንፀባርቁም፣ እየባሰ የሚጠቁር ብርቱካንማ ሰማይ ይታይባቸዋል:: ኒየርት የተባለው ድንክ፣ አጭርና ሰው ሰራሽ ፀጉር ያጠለቀው የንጉሡ ቀደማይ የልፍኝ አስከልካይ፣ እንግዶቹን ለመቀበል በሩ አጠገብ ቆሟል:: ተከትለውትም ወደ ሌላ ክፍል ሄዱ:: ይህኛው ክፍል መብራት ባይበራበትም፣ ደብዘዝ ባለ ግራጫ ብርሃን የተሞላ ነበር:: በተቃራኒው ጐን፣ ገርበብ ያለና የሠላሣ ሻማዎች ከባድ ብርሃን እየተንቦገቦገበት ያለውን ራቅ ያለ ክፍል የሚያሣይ ባለሁለት ተከፋች በር አለ:: የልፍኝ አስከልካዩ፣ ከዙፋን ፊት የሚቀርቡትን ሰዎች በስልፍ ካዘጋጃቸው በኋላ፣ በሩን ወለል አድርጐ ከፍቶ ለንጉሡ አቀረባቸው::